# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 179 የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







"እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!"

ልዩ ዕትም



ፎቶ - በዘሐይ ንጉሤ

ዶክተር ራሔል ባፌ

# የሴቶችን መብትና እኩልነት

## በተመለከተ እንደ ሀገር የተደረሰበትን ርቀት ማሰብ ያስፈልጋል

**እፀገነት አክሲሉ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ዓለም አቀፉ የሴቶች ቀን ሲከበር እንደ ሀገር የሴቶችን መብትና እኩልነት በማክበርና በማስከበር በኩል የተደረሰበት ርቀት የት መሄድ ችሏል የሚለው ሊታሰብበት እንደሚገባ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጸሐፊ ዶክተር ራሔል ባፌ ተናገሩ።

ዶክተር ራሔል ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳሉት፤ ፖለቲካ ለሴቶች አስቸጋሪ የሚሆንበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንዱ ባሕል ሲሆን ሌላው ደግሞ የሴቷ ኢኮኖሚያዊ አቅም ከወንዶቹ ጋር ሲነጻጸር ዝቅ ያለ መሆኑና የቤት እመቤቶች መብዛታቸው ነው። በመሆኑም እነዚህ ሁሉ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ሴቶች በፖለቲካው ውስጥ የት ናቸው የሚለው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

እንደ ዶክተር ራሔል ገለጻ፤ ሴቶች ከወላጆችና ከትዳር አጋራቸው ፍቃድ ውጪ መሆንም ከባድ

የሴቶችን መብትና እኩልነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ኢፕድ የሴት ሠራተኞቹን ሁለተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ እየሠራ ነው

**ስምስም መንግሥቱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት (ኢፕድ) የተቋሙን ሴት ሠራተኞች ሁለተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ። ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8) ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ በሴት ጋዜጠኞች እየተዘጋጀ የሚወጣው ጋዜጣ መጠናከሩ የሚያበረታታ መሆኑንም የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ፤ "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ" በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ 112ተኛ እንዲሁም በሀገራችን ለ47 ተኛ ጊዜ የሚከበረውን የሴቶች ቀን ምክንያት በማድረግ ባስተላለፉት መልዕክት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ ሴት ሠራተኞችን የእኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የአመራር ሚናቸው ከፍ እንዲል፣የሴቷን ሸክም የሚያቃልሉ እንደ እለት ፍጆታ



አቶ ጌትነት ታደሰ

ያሉ አገልግሎቶችን በማቅረብ፣ የሕፃናት ማቆያን ምቹ በማድረግ በአጠቃላይ ሁለተናዊ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ከማክበር ባለፈ ትክክለኛ የሆነ የሴቶች ተሳትፎ ላይ መሥራት ያስፈልጋል የሚል እምነት እንዳላቸው የጠቆሙት አቶ ጌትነት፤ በተቋም ደረጃም ሴቶች እስከ ከፍተኛው የአመራርነት ደረጃ ድረስ እንዲደርሱ በተሠራው ሥራም 35 በመቶ መድረስ መቻሉን አስረድተዋል። ይህ በቂ እንዳልሆነና በተቋሙ ውስጥ ሴት አመራሮችን 50 በመቶ ለማድረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

‹‹ሴቶች በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው። በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው በየትኛው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች አሉ። በቅርቡ የተከበረውን የዓድዋ በዓል ብንመለከት ድሉ እንዲመዘገብ ሴቶች የነበራቸው ሚና ትልቅ ነው። እቴጌ ጣይቱ ከማዋጋት እስከመዋጋት የነበራቸውን ሚና

ኢፕድ የሴት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ‹‹የሴቶች ተሳትፎ በሌለበት የሀገርን ብልጽግና ማረጋገጥ አይቻልም››

\- ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ

ገጽ 4







ልዩ ዕትም "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!"



ወይዘሮ ሚካል ማሞ

## ከ20 ሚሊዮን በላይ ሴቶች የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ አያገኙም ተባለ

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የወር አበባ ከሚያዩ ከ35 ሚሊዮን ሴቶች ውስጥ 22 ሚሊዮን ወይም 75 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ እንደማያገኙ የአደይ የሴቶች የሚታጠብ ንጽሕና መጠበቂያ መሥራች አስታወቁ።

የአደይ የሚታጠብ ንጽሕና መጠበቂያ መሥራች ወይዘሮ ሚካል ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአደይ የሴቶች የሚታጠብ ንጽሕና መጠበቂያ (ፓድ) ምርት በኢትዮጵያ ያለውን የሴቶች የወር አበባ የንጽሕና መጠበቂያ አቅርቦት እጥረት ለመፍታት ይረዳል። በዚህም ያለውን ከ20 ሚሊዮን በላይ ቁጥር ለመቀነስ እንዲሁም የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ይረዳል።

ለዚህም አደይ ፓድ አንዱ የንጽሕና መጠበቂያ በአንድ የወር አበባ ኡደት ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፣ በአጠቃላይ አንድ መቶ ጊዜ መታጠብ የሚችል መሆኑን መሥራቿ ተናግረዋል። ይህ ድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ያለውን የምርት እጥረት ከመቅረፍ ባለፈ የዋጋ ንረቱንም ሊቀንስ ይችላል ብለዋል።

ይህ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል የሴቶች የንጽሕና መጠበቂያ ለሰውነት ተስማሚ ከሆነ ግብዓት የሚሠራ ምቹ የሆነ ፣ፈሳሽ የሚችል፣ምንም የጎንዮሽ ጉዳት የሌለው መሆኑን የጠቀሱት መሥራቿ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለ5ሺ ሴቶች የሚደርስ ንጽሕና መጠበቂያ እንደሚመረት ተናግረዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ አንዲት ሴት በወር አበባ ምክንያት በአማካኝ ከሦስት እስከ አምስት ቀናት ከትምህርት ወይንም ከሥራዋ በንጽሕና በአቅርቦት እጥረት ምክንያት ትስተጓጎላለች። ለዚህም በትኩረት ሴት ተማሪዎች ላይ እየሠሩ ይገኛል። ይህም ምርት ከ18 እስከ 24 ወራት የሚያገለግል በመሆኑ በወር አበባ ምክንያት ከትምህርቷ ሳትስተጓጎል እንድትገኝ የሚያደርጋት ይሆናል።

የትኛዋም ሴት የንጽሕና መጠበቂያ በማጣት ምክንያት ከትምህርት ገበታዋ ይሁን ከአስፈላጊ ሥራዎቿ መቅረት የለባትም የሚሉት ወይዘሮ ሚካል እስካሁንም በሀገሪቱ ለሚገኙ ከ300 ሺ በላይ ሴት ተማሪዎች ንጹሕ የሆነ የንጽሕና መጠበቂያ በመሥራት ተደራሽ ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

ዋናው ችግራችን አብዛኛው ግብዓት ከውጭ የሚመጣ በመሆኑ የቀረጥና የግብር ጉዳይ መፍትሔ አለማግኘቱ ነው ሲሉም ተናግረው እንዲሁም የቦታ ጥበት እንዳለባቸው አስረድተዋል።

ሴቶችን ማብቃት ሲባል የመጀመሪያው ነጥብ የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ ማቅረብ ነው። ለዚህም መንግሥት ይህንን የሴቶች ንጽሕና መጠበቂያ ዋጋ ንረት ለመቅረፍ እንዲሁም ተደራሽነቱን ለመጨመር ምርቶቹን እንዲሁም የምርቶቹን ጥሬ እቃ ከቀረጥ ነጻ ማድረግ እንዳለበት ጠይቀዋል።

እንደ ወይዘሮ ሚካል ገለጻ፤ ያለውን የወር አበባ ድህነት ለመቅረፍ ፣ ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ እና ተደራሽ እንዲሆን የተለያዩ ንቅናቄዎች የተደረጉ ሲሆን ከነዚያም ውስጥ ‹ቀረጥ ይወሰንልን ፣ ዋጋ ይተመንልን›፣ ‹ሰብዓዊ መብቴን አትቅረጹ›፣ ‹አበባ አየሽ ወይ ትምህርት ቤት ትሄጃለሽ ወይ?› የሚጠቀሱ ሲሆን አይ ኬር ኢትዮጵያ እና ጀግኒት ኢትዮጵያ ጋር በአጋርነት እንደሚሠሩ ወ/ሮ ሚካል ገልጸዋል።

## የሴቶችን ጥቃት በተመለከተ ያሉት የሕግ ክፍተቶች በትኩረት ሊሠራባቸው ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-የሴቶችን ጥቃት በተመለከተ ያሉት የሕግ ክፍተቶች በትኩረት ሊሠራባቸው እንደሚገባ የሕግ ምሑራን ተናገሩ።

ጠበቃና የሕግ አማካሪ ወይዘሮ ትሩፋት በላይነህ፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በተመለከተ ከአፈጻጸም ጀምሮ የሕግ ክፍተቶች አሉ። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።


በሴቶች ላይ ብዙ በደሎች እየተፈጸሙ ቢሆንም ጥቃት አድራሾቹ ተገቢውን ቅጣት እያገኙ አይደለም። ለዚህም ምክንያት የሆነው አንዳንዶቹ ጥቃቶች የሕግ ማዕቀፍ ስለሌላቸው ሲሆን የሕግ ማዕቀፍ ያላቸውም ጠንካራ የሚባሉ አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

በወንጀል ሕጉ ላይ ኃይልን በመጠቀም ወይም በማስፈራራት በማንኛውም መልኩ ሴት ልጅ ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም በወንጀል እንደሚያስቀጣ ሕጉ ቢደነግግም በጋብቻ ውስጥ በግዴታ የሚፈጸምን የግብረ ሥጋ ግንኙነት አያካትትም ሲሉ ተናግረዋል።

ይህም ያለፍላጐት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳትፈልግ እንድታረግዝ ሊያደርጋት ይችላል። በተጨማሪም በጤናዋ ላይ ጉዳት ሊያመጣ ስለሚችል የሕግ ማዕቀፍ ሊኖረው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በከባድ መሣሪያ ቀላል እና ከባድ ጉዳት ማድረስን በተመለከተ አዋጁ ላይ ተደንግጓል ያሉት አማካሪዋ ቢሆንም አዋጁ ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ አሁን ላይ ሴቶች ላይ አሲድ፣ጋዝ፣የፈላ ውሃ መድፋት እና የመሳሰሉ ወንጀሎችን አላካተተም ብለዋል ።

በመሆኑም የወንጀል ሕጉ እነዚህን ነገሮች ማካተት ይገባዋል። ፍርድ ቤቶቹ ቀላል ከባድ በሚል አጠጋግተው ነው ውሳኔ የሚሰጡት ሲሉ ቅሬታቸውን ይገልጻሉ።



ወይዘሮ ትሩፋት በላይነህ



አቶ ፋሲል ስለሺ

ወይዘሮ ትሩፋት እንደተናገሩት የእርቃን ፎቶዎችን በማኅበራዊ ሚዲያዎች የለጠፈ እና ሌሎች የሞራል ጉዳቶችን ያደረሰ ወንጀለኛ 1ሺ ብር ቅጣት እንደሚቀጣ አዋጁ ላይ የተደነገገ ቢሆንም ጉዳዩ ግን ቀላል ባለመሆኑና በሴቶቹም ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ሰፊ ስለሆነ ቅጣቱ በትክክል ቢታይ ሲሉም ይናገራሉ።

እነዚንም የሕግ ክፍተቶች ለመሙላት አዳዲስ ተጨማሪ ሕጎች ያስፈልጋሉ። በመሆኑም ሕግ አውጪው፣ ተርጓሚው፣ አስፈጻሚው እና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተቀናጅተው መሥራት አለባቸው ብለዋል።

አሁን ላይ እራሱን ችሎ የሴቶችን እና የሕፃናት ጉዳይ ላይ የሚሠራ ችሎት ስለተቋቋመ ሴቶች ጥቃት ሲደርስባቸው መጀመሪያ አቅራቢያቸው ወዳለ ፖሊስ ጣቢያ ከዛም ፍርድ ቤቶች ላይ ቀርበው በደላቸውን ለማስረዳት ወደኋላ ማለት የለባቸውም። ወደኋላ በቀሩ ቁጥር ማስረጃዎች የመጥፋትና ፍርድ የመዛባት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል ብለዋል።

ጠበቃና የሕግ አማካሪ አቶ ፋሲል ስለሺ፤ በበኩላቸው በሕገ መንግሥቱ አስገድዶ መድፈርን፣ያለዕድሜ ጋብቻን፣የሴት ልጅ ግርዛትንና የመሳሰሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በተመለከተ እራሱን የቻለ ሕግ ቢኖርም ለሴቶች ተብሎ በተለየ መልኩ ሊያስቀጣ የሚችል የተደነገገ የሕግ አንቀጽ የለም ።

በመሆኑም አንድ ወንድ ሴትን ልጅ ቢመታት እና ለፍርድ ቢቀርብ የሚቀጣው ሰው በመሆኑዋ ባደረሰባት የወንጀል ድርጊት እንጂ ለሴቶች ተብሎ በተለየ መልኩ በወጣ የሕግ አግባብ አይደለም ይላሉ።

የሴቶችን ጥቃት በተመለከተ ያልተደነገጉ ሕጎች እንዲደነገጉ የሚመለከታቸው አካላት የፓርላማ ተወካዮች፣የሴቶች አደረጃጀት፣ሰብዓዊ መብት ላይ የሚሠሩ አካላት፣የሕግ ባለሙያዎች፣የግል ድርጅቶች እና ግለሰቦች መሥራት አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

## «የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ በሀሳብ የበላይነት ማመን ያስፈልጋል»

- የአውራምባ ማኅበረሰብ መሥራች የክብር ዶክተር ዙምራ ኑሩ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ጾታን ሳይሆን ሀሳብን የሚመዝን በሀሳብ የበላይነት የሚያምን ማኅበረሰብ መፍጠር እንደሚገባ የአውራምባ ማኅበረሰብ መሥራች የክብር ዶክተር ዙምራ ኑሩ ገለጹ።

የአውራምባ ማኅበረሰብ መሥራቹ የክብር ዶክተር ዙምራ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ የፆታ እኩልነት ያስፈልጋል ሲባል አንዱ አብሮ የሚነሳው ነገር የሥራ ክፍፍል ነው። አትዮጵያ ውስጥ የጾታ ልዩነት ለሥራ ክፍፍል የማይውልበት ማኅበረሰብ አለ። በደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የአውራምባ ማኅበረሰብ ወንድ ወይም ሴት መሆን አንድን ነገር ማድረግ ከመቻል ጋር ቁርኝት የለውም ብለው ያምናሉ።

በፆታ እኩልነት አምናለሁ ዘመናዊ ነኝ የሚለው ወንድ እንኳን ቀላል የሚባለውን እንጀራ ጋግር ብላችሁ ብትሰጡት እንኳን መጋገር አይፈልግም ያሉት የክብር ዶክተር ዙምራ፤ ለዚህም የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ጾታን ሳይሆን ሀሳብን የሚመዝን በሀሳብ የበላይነት የሚያምን ማኅበረሰብ መፍጠር ይገባል ይላሉ። አውራምባ ማኅበረሰብ ዘንድ ሴት ሕጻናት ከወንድ ሕጻናት ጋር አንድ አይነት ጨዋታን ይጫወታሉ፤ እድሜዋ ለሥራ የደረሰች ሴት ሞፈር ጠምዳ ታርሳለች፣ ወንድ ሊጥ አቡክቶ እንጀራ ይጋግራል፤ ወጥ ይሠራል ብለዋል።

የክብር ዶክተር ዙምራ ኑሩ ሴትን ተፈጥሮ በራሱ እኩል አድርጎ ፈጥሯታል የሚል አመለካከት አላቸው። ይህም ፈጣሪ ሴትን እናት ወንድን አባት አድርጎ ፈጥሯል፤ ከሁለት አንዱ ቢጎድል የሚኖር የለምና የማነስና የመላቅ ሳይሆን የእኩልነት ምሳሌ ነው ይላሉ። ሴቶች ከወንዶች እኩል ተፈጥረው እኩልነታቸውን ቀምተን ነበርና የአውራምባ ማኅበረሰብ እኩልነታቸውን መልሷል ብለዋል።





የወንዱን ሥራ ሴቷ የማትሠራው ከሆነ የሴቷን ወንዱ ካልሠራው መተጋገዝ፣ አንዱ አንዱ መደገፍ አይችልምና ሙሉነት አይታሰብም ያሉት የክብር ዶክተር ዙምራ፤ ከዚያ ይልቅ ሁሉም ሥራ የሁሉም ቢሆን ኑሮ ይቀላል ብለዋል።

እንደ የክብር ዶክተር ዙምራ ገለጻ፤የአውራም ማኅበረሰብ ሥራን የወንድ የሴት ሳይል ይሠራል። በዚህም ሴቶችን አይተናል የሚጎላቸውን አላገኘንም ነገር ግን የሰው ችሎታ የሚለያይ ነው እና የወንድም ሰነፍ የሴትም ሰነፍ ይኖራል ይህ ግን ሰው ከመሆን ጋር እንጂ ከጾታ ጋር አይገናኝም ብለዋል።

ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚፈጠር የወገብ ሕመም ያጋጥማቸዋል የሚሉት የክብር ዶክተር ዙምራ፤ በሀገራችንም ወገቧ አልጠናም እየተባለ የአራስነት ጊዜ የማገገሚያ ጊዜ እንደሆነ ይታሰባል። ነገር ግን ጉዳቱ ቀላል አይደለምና ለረጅም ጊዜ ሥራ መርጣ መሥራት እንዳለባት የሚያሳይ መሆኑን አመላክተዋል።

ይህ ወቅት በአንዳንድ አካባቢዎች የሴቶችን አለመቻል ተደርጎ የሚታይ ሲሆን ነገር ግን በአውራምባ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለመቻል ሳይሆን የሚበልጠውን ፣የሚያደክመውን ሥራ ሠርታለችና በዚህ አትችይም ልትባል አይገባም ሲሉ የክብር ዶክተር ዙምራ ገልጸዋል።

በአውራምባ ማኅበረሰብ ውስጥ የሰው ችሎታ በጾታ ሳይሆን በሀሳቡ ይመዘናል። ይህም በሀሳብ የበላይነት የሚያምን፣ በመተዛዘን፣ በፍቅር፣ በመተሳሰብ የሚኖር ማኅበረሰብን መፍጠር ተችሏል።

የክብር ዶክተር ዙምራ እንደሚሉት፤ የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ከሥራ ክፍፍል ባለፈ በዋንኛነት በሀሳብ የበላይነት የሚያምን ማኅበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል። ይሄን ማሳካት ከተቻለም የልጆቻችንን ሕይወት ብሩህ ማድረግ ይቻላል። ሥራና ንግግር ካልተጣጣመ ቅዠት ነውና የሚወራውን ከሚተገብር አውራምባ ማኅበረሰብ ሌላው ማኅበረሰብ ሊማር ይገባል።

**ልዩ ዕትም** “እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”


ጋዜጠኛ ርብቃ ታደሰ


ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ


መምህርት ዮርዳኖስ ግዛቸው

# ሴቶችን ያጎላው የሴት ጋዜጠኞች ማኅበር

**ስምስም መንግሥቱ**

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (ኢትመባሴማ) ከተመሰረተ ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ሆኖታል። የማኅበሩ ምሥረታ መነሻ ሴቶች በመገናኛ ብዙኃን እንዴት ሽፋን ያገኛሉ? ሴት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎችስ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በምን ሁኔታ ውስጥ ሆነው ይወጣሉ? ብቁ የሆኑ ሴት ጋዜጠኞችን ለማፍራትስ ምን መሠራት አለበት? የሚል መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ማኅበሩ እንደተመሠረተ ከማኅበሩ መሥራች መካከል አንዷ የሆኑት የቀድሞ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ ይገልጻሉ።

ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ በሙያው ውስጥ ሆነው ከሚያጋጥማቸውም በውጭው የሚነገረውንም እንደሚሰሙት ማኅበረሰቡ ለሴት የሰጠው ቦታ ደካማ ሆና እንድትታይ አድርጓታል። ተጽዕኖው በተለያየ ሙያ ውስጥ በሚገኙ ሴቶች ላይም የሚገለጽ በመሆኑ ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር ሆነው ከመከሩበትና መጠነኛ የዳሰሳ ጥናትም ካደረጉ በኋላ ማኅበሩን ለመመሥረት እንደተነሳሱ ነው የገለጹት። ማህበሩ ችግሮች ላይ ብቻ ትኩረት ለማድረግ ሳይሆን፤በአጫጭር ስልጠና፣ከሌሎች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣በአጠቃላይ በሙያው ለማብቃት፣ የጋዜጠኝነትን ሙያ ከፍ ለማድረግ፣የሴት ጋዜጠኞችንም ሚና ለማጉላትና ተተኪዎችን ለማፍራት ጭምር ታሳቢ ያደረገ ማኅበር እንደሆነ አስረድተዋል። የሴቶችን አቅም ለማጎልበት፣ ስለሴት የሚሰጠውን የተሳሳተ አስተያየት ለመቅረፍ፣ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን ኅብረት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

ማኅበሩ አያስፈልግም ብለው የተከራከሯቸውና በምሥረታው ውስጥ ሚና የነበራቸው በአንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን ውስጥ የሚሠሩ ሴት ጋዜጠኞች በሥራቸው ላይ ችግር ተፈጥሮባቸው በፈታኝ ሁኔታ መመሥረቱን ያስታወሱት ጋዜጠኛ አባይነሽ ፤ማኅበሩ ብዙ መሥራት የሚጠበቅበት ነገር እንዳለ ቢያምኑም አስፈላጊነቱ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ አግኝቶ፣ተተኪዎችም ኖረው ሥራውን ለማስቀጠል የሚያደርጉትን ጥረት ማየታቸው ደስታ እንደሚሰጣቸው ነው ያስረዱት።

ሴቶችን በተመለከተ የተሳሳቱ ነገሮች ሲንፀባረቁና ጉዳቶች ሲደርሱ መቃወም የተጀመረው መብት ለማስከበርና አቅምን ለማጎልበት የሚንቀሳቀሱ ማኅበራትን መፍጠር ከተቻለ በኋላ እንደሆነም ያምናሉ።

በመላው ዓለም ከሚከበረው የሴቶች ቀን (ማርች 8) ጋርም አያይዘው ጋዜጠኛ አባይነሽ‹‹በዓሉ መከበሩ ሴቶችን አጉልቶ በማውጣት በኩል ሚናው ጉልህ ነው። ነገር ግን ሁልጊዜ ክላራ ዚክተን እያልን መኖር የለብንም። ማርች 8ን ወደራሳችን መቀየር አለብን። ለእኔ ሁሌም የሴቶች ቀን ነው››በማለት ገልጸዋል።

ከማኅበሩ ምሥረታ ጋር የትንሽ ጊዜ ልዩነት እንዳላቸውና አባል ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ባለማቋረጥ አሁን ደግሞ የማኅበሩ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው በመሥራት እያገለገሉ እንደሆነ የነገሩን ጋዜጠኛ ርብቃ ታደሰ አባል በመሆናቸውም ተጠቃሚ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ማኅበሩ ከተቋቋመለት ዓላማ አንጻር ምን ተግባራትን እንዳከናወነና እቅዱን በተመለከተ እንዲህ ገልጸውልናል፤ማኅበሩ ከተመሠረተ 23ኛ ዓመቱ ላይ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ለአስር ዓመታት እንቅስቃሴው ተገትቶ ነበር። እርሳቸው እንዳሉት ማኅበሩ ይንቀሳቀስ የነበረው ከውጭ በሚያገኘው ከፍተኛ ድጋፍ ነበር። 90 በመቶ በሀገር ውስጥ፣10 በመቶ ደግሞ ከውጭ ድጋፍ፣(10/90) በሚል በሀገር ውስጥ በወጣው ሕግ ኢትዮጵያዊነት በሚል ተመዝግቦ መተዳደር ሲጀምር ለባለሙያዎች ይሰጣቸው የነበሩ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችን፣ከሙያው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥራዎችን ለመሥራትም ሆነ የተለያዩ ወጭዎችን ለመሸፈን አልተቻለም። የነበረው እንቅስቃሴ የማኅበሩን ሕልውና ከማቆየት ያለፈ አልሆነም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ግን ዳግም ለማንሰራራት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

እርሳቸው አባል ሆነው በገቡበት ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የጋዜጠኝነት ትምህርት የሚሰጥ ተቋም አልነበረም። መሠረታዊ የጋዜጠኝነት እውቀት ያገኙትና ሙያውንም እንዲወዱ ምክንያት የሆናቸው ኢትመባሴማ ነው። ማኅበሩ ከተለያዩ ሀገራት ጋር በፈጠረው የልምድና ተሞክሮ ልውውጥም ለአንድ ዓመት ኖርዌይ ሀገር የጋዜጠኝነት ትምህርት በሚያስተምር ዩኒቨርስቲ ውስጥ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ እድሉን አግኝተዋል። ይህም ተጨማሪ አቅም ፈጥሮላቸዋል። እርሳቸውን ጨምሮ ለብዙ ባለሙያዎች ባለውለታ የሆነ ማኅበሩ ቀድሞ የነበሩትን ተሞክሮዎች በመቀመር አሁን ላይ ወቅቱ የሚጠይቀውን ባለሙያ ለመፍጠር ፤ያሉት ሴት ጋዜጠኞችም በሥራቸው የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትመባሴማን የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆና እንደምታውቀውና አሁን ደግሞ በጅጅጋ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነትና ሥነ ተግባቦት ትምህርት ክፍል ኃላፊና መምህርት እንደሆነች የነገረችኝ መምህርት ዮርዳኖስ ግዛቸው፤ ማኅበሩ አስፈላጊ እንደሆነና መጠናከር እንዳለበት በማመኗ የበኩሏን ለማበርከት አባል እንደሆነች ትገልጻለች።

መምህርት ዮርዳኖስ በአባልነቷም በሶማሌ ክልል የጅጅጋ ተወካይ ሆና እያገዘች ሲሆን በሙያቸው የታገሉ፣ሙያውንም የሚያከብሩ በማኅበሩ ውስጥ መኖራቸውንና ተተኪዎችም አርአያነታቸውን መከተል እንዳለባቸው ትናገራለች።‹‹ሴቶች ብርቱ ሆነን ስለምንሠራ ሥራችንን የምናሳይበት እንዲህ ያለ ማኅበር ያስፈልገናል›› ስትልም ተናግራለች።

# «መሪነት ለሴት ልጅ ችሮታ ሳይሆን ችሎታ ነው»

- ዶክተር አዲስ ዓለም አባትሁን
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ካምፓስ ዲን

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- ‹‹መሪነት ለሴት ልጅ ችሮታ ሳይሆን ችሎታ ነው›› ሲሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ካምፓስ ዲን ዶክተር አዲስዓለም አባትሁን ገለጹ።

ዶክተር አዲስዓለም ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ሴት ልጅ በተለያየ የሥልጣን ደረጃ ላይ ሆና የመሪነት መንበር ላይ ብትቀመጥም ከፈተና ማምለጥ አትችልም። መሪነት ላይ መሆን እርሷን ካለችበት ከፍታ ሊያወርዳት የሚጣጣር ጥቂት አካል አይደሉም። ወድቃ እንድትታይም ብዙ የሚቆፍሩ አይጠፉም። ሆኖም ጠንካራ ለሆነች ሴት ፈተናው ልምዷ እንጂ ጎትቶ የሚጥላት አይደለምና ለሴት ልጅ መሪነት በችሮታ የሚሰጣት ሳይሆን በችሎታዋ የምታከናውነው ተግባር ነው።

እርሳቸው እንዳሉት፤ እንደሀገር ለሴቶች የሚሰጥ መሪነት ብዙ ጊዜ ችሮታ ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም መሪነት ለሴት ልጅ ችሮታ ሳይሆን ችሎታ ነው። መሪ የሆነች ሴት ለሚያጋጥሟት እነዚህን የመሰሉ ችግሮች እጅ መስጠት የለባትም። ይልቁንም ከወንዶች ከፍ ብላ የምትታይበትን ሥራ ማከናወን እንደሚጠበቅባት መረዳት አለበት።

ሴት ልጅ የመሪነት ቦታዋን ለማረጋገጥና አቅሟን በተዓማኒነት ለመገንባት ከወንዶች ሦስት እጥፍ ልትሠራ ይገባል። ውድቀቷን የምትቀንሰው ሠርታ በማሳየት ብቻ ነው። ኃላፊነትን መወጣት ደግሞ ለሴቶች አዲስ አይደለም። ቤታቸውን ብሎም ማኅበረሰቡንና ሀገራቸውን በጥበብ ጭምር የሚመሩና የሚያሻግሩ እነርሱ ናቸው። ስለሆነም


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

ይህንን ብልህነታቸውን ሠርቶ በማሳየት መገንባትና ተዓማኒነትን እንደሀገር ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

‹‹የሴቶች ፈተና የሚመጣው ከቤተሰብ ጭምር ነው። ለምሳሌ ልጆች ይበልጥ እናታቸውን ይፈልጋሉ፤ ቤቱ በራሱ ያለእናት ሙሉ አይሆንም፤ ትዳርም እንዲሁ ነው የሚሉት ዶክተሯ፣ ከዚያም ባሻገር ማኅበራዊ ሕይወት ጭምር የሚሞላው በሴት ነው ሲሉ ገልጸዋል። ስለዚህም ሴቶች ሸክም ብዙ ናቸው። ሆኖም በሥራ ግን ደከመኝ አይሉም። ለዚህም የሀገር አመራሮች ሳይቀሩ ምስክር መሆናቸውን ተናግረው፤ በብዙ እጥፍ ሠርተው ማንነታቸውን በአደባባይ ማሳየት መቻላቸውን አስረድተዋል።

‹‹ሴት የምንተኛበትን ሰዓት፣ ከማኅበራዊ ተሳትፎ በመጠኑና ከቤተሰብ ጭምር በትንሹ ጊዜን ማዋጣት የምትችል ኃላፊነት የሚሰማት የሀገር መከታ ነች።›› ያሉት ዶክተር አዲስዓለም፣ ስለሆነም ማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ምልከታ ለመቀነስ ከመቼውም በላይ መልፋት ያስፈልጋል ብለዋል። በተለይም በሴት አመራሮች በኩል ያለው ክፍተት በእጅጉ መሞላት ይኖርበታል። መንግሥት እንደመንግሥት ይህንን ሲሠራም ችሮታን ሳይሆን ችሎታን አምኖ ወደ ከፍታው ማምጣት ይኖርበታል በማለት ገልጸዋል።

ዶክተሯ እንደገለጹት፤ በሴቶች በኩልም መሪ የሆነች ሴት አርአያነቷን እያሳየች መቀጠል አለባት። ለዚህ ደግሞ ከእርሷ በታች የሆኑትን ማብቃት ይጠበቅባታል። በመተጋገዝ ማመንና አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆንም ያስፈልጋታል። ራሷንም ቢሆን ‹‹እባክሽን እዚህ ላይ ተቀመጭ›› እስኪትባል መጠበቅ የለባትም። ልክ እንደወንዶች ሁሉ ተሻምታ የሚገባትን ቦታ ማግኘት አለባት።

በሴቶች ላይ የሚመጡ ፈተናዎች መቼም አይቆሙም። መግታት ግን ይቻላል ያሉት ዶክተር አዲስዓለም፣ ለዚህ ደግሞ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል ብለዋል። ሴቶችን ማበርታትና ወደ መሪነት ማምጣት ይገባል ሲሉም ተናግረዋል። ይህ ሲባል ግን ለግብዓት ፍጆታ፣አበቃን ለማለት፣ ኮታ ለመሙላት መሆን እንደሌለበትም አመልክተው፤ እንደሚችሉ አምነው የአመራርነት ቦታውን መያዝ አለባቸው ብለዋል።

እንደ ዶክተር አዲስአለም ገለጻ፤ ለሴቶች ብዙ እድሎች አሉ። ነገር ግን መሞከር ላይ በጣም ችግር አለብን። በዚህም መልካም እድሎችን እንዳንጠቀምባቸው ሆነናል። ለዚህ መፍትሔው ደግሞ አንዳንችን ከአንዳችን የተሻልን ከሆንን ተደጋግፎ መውጣትን ማጎልበት ነው። በተጨማሪም ሴቶቹ ለሴቶቹ ያላቸውን ክብር መጨመር አለባቸው።

## ቀኑ መከበሩ ሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያከናወኗቸውን ተግባራት ለማጉላት ይረዳል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች ቀን መከበሩ ሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያከናወኗቸውን ተግባራት ለማጉላት ይረዳል ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሴቶች ማኅበራዊ አካቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ ገለጹ።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሴቶች ማኅበራዊ አካቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ እርቅነሽ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ “እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ” በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ኛ እንዲሁም በሃገራችን ለ 47ኛ ጊዜ የሚከበረው የሴቶች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሴቶች ያከናወኗቸውን ሥራዎች የማጉላት እና ሴቶች ትኩረት እንዲያገኙ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

እንደ ወይዘሮ እርቅነሽ ገለጻ ፤ የሴቶች ቀንን ከማክበር ባሻገር ሴቶችን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሚረዳ መልኩ መከበር ይኖርበታል። ሴቶችን በየጊዜው ተጠቃሚ የሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ በማሳተፍ ዘለቄታዊነት ያለው ውጤት ሊያመጣ የሚችል ሥራዎችን በማስጀመር ማክበር አስፈላጊ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀኑ ሲከበር በዋናነት ሴቶች በቴክኖሎጂ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዴት ማንቃት አለብን ተብሎ ነው የሚከበረው ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ እንደ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ በቴክኒክና ሙያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች አሉ ብለዋል ።

በተጨማሪም ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል የሚዳሰስበት ሁኔታም አመቻችተን እየሠራን እንገኛለን በማለት ገልጸው ሴቶች በጾታቸው ምክንያት ተሳትፏቸው እንዲቀንስ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም አብራርተዋል ።

በሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ በአብዛኛው ወደ ፊት የሚወጡት ወንዶች ናቸው ያሉት ወይዘሮ እርቅነሽ ሴቶችም ከወንዶች እኩል ዕድሉን እንዲያገኙ እና ወደኋላ እንዳይቀሩ ከአንድ ማዕከል ጀምሮ የማንቃት ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

በሀገሪቱ ካሉ ሴቶች እስከ አሁን 35 በመቶ ብቻ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ለምዝገባ ወደ ማዕከላት መምጣታቸውን ገልጸው በዘንድሮ ዓመት በተሠራው ሥራ ግን ቁጥሩን ወደ 36 ነጥብ አራት በመቶ ለማድረስ ተችሏል። በቀጣይም ቁጥሩ ወደ 50 በመቶ ከፍ እንዲል ለማድረግ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ሴቶች በኃላፊነት መቀመጥ እንዳለባቸው አምኖ በመወያየት ለዚህ የሚያበቃውን በአመራርነት ደረጃ ላይ እንዲቀመጡ የሚያስችል አሠራር እየተገበረ ይገኛል። ሴቶች ባሉባቸው የአመራር ቦታዎች ሃገሪቱ በሰጠቻቸውን የሥራ ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ሴት ልጅ በተፈጥሮ በአንድ ጊዜ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን እንደምትችል ተገንዝባ በተሰጣት ማንኛውም ሥራ ላይ በቁርጠኝነት መትጋት ይኖርባታል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በኦቢቻ ወረዳ ለማዋለጃ አገልግሎት የሚውል ክሊኒክ ግንባታ ሥራ መጀመሩ ተገለጸ

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በረከት ወርቁ ኢንተግሬትድ አግሮ ኢንዱስትሪ የእርሻ ሥራ በሚያከናውንበት በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን አቢቻ ወረዳ የሚስተዋለውን የእናቶች የጤና አገልግሎት መስጫ ችግር ለመፍታት የተሟላ የቤተሙከራ (ላቦራቶሪ)ያለው የወሊድ አገልግሎት መስጫ ክሊኒክ ግንባታ ሥራ መጀመሩን አስታወቀ።

‹‹ገበሬ›› በሚል ቅጽል ስም የምትታወቀው የኢንዱስትሪው ባለቤት በረከት ወርቁ ‹‹እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ›› በሚል መሪ ሐሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ኛ ጊዜ፤ በሀገራችን ደግሞ ለ47ኛ ጊዜ በዛሬው ዕለት የሚከበረውን የሴቶች ቀን አስመልክታ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጸችው፤ድርጅቷ በአካባቢው ላይ የሚስተዋለውን የጤና አገልግሎት ክፍተት ለመሙላት የተሟላ ቤተሙከራ(ላቦራቶሪ) ያለው የማዋለጃ አገልግሎት ክሊኒክ ሠርቶ ለማስረከብ የግንባታ ሥራ ጀምሯል። የግንባታ ሥራውም በዚሁ ዓመት እንደሚጠናቀቅ ገልጻለች።

እናቶች በአካባቢያቸው የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ታስቦ ግንባታው የተጀመረው ክሊኒክ ሲጠናቀቅ ነፃ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑንም በረከት ገበሬዋ ገልጻለች። ክሊኒኩ የአምቡላንስ አገልግሎትም እንደሚሰጥም ጠቁማለች። በአካባቢው ላይ ወደ 10ሺ የሚገመት ማኅበረሰብ እንደሚኖርም አመልክታለች።

በሌላ በኩልም ገበሬዋ በረከት፣ በኦሮሚያ ክልል በፍቼ ስር ባለች ዱበር አካባቢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት ቦታ መረከቧን ተናግራለች። ትምህርት ቤቱ የሚገነባው በተለይ ተፈናቃዮች ባሉበት አካባቢ እንደሆነና ግንባታውም በቅርቡ እንደሚጀመር ገልጻለች።

ትምህርት ቤት በመገንባት አቅም ያጡ የማኅበረሰቡን ልጆች እንዲማሩ በማድረግ ተሳትፎ ማድረጓን የገለጸችው በረከት ገበሬዋ፤ በቋሚነት ቢሻን ጉራቻ ላይ የምታስተምራቸውም 400 ያህል ተማሪዎች እንዳሏትና ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል በአባቷ ‹‹ወርቁ አደራ ቡታ›› ስም በገነባችው ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ የተማሪዎቹን የትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት በማስተማር ላይ እንደምትገኝም አስረድታለች። በትምህርት ቤቱ የሚማሩ 400ውም ተማሪዎች የምግብ አገልግሎት እንደሚያገኙ ተናግራለች።

የእርሻ ሥራዋን የምታከናውንበት አንዱ በሆነው አርሲ ዞን፣ ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ አንዶዴ ቀበሌ ለሚገኙ ለ680 ተማሪዎች ወደ ስምንት ሺ



በረከት ወርቁ

ደብተር፣ አንድ ሺ እስክሪብቶና አንድ ሺ እርሳስ ገዝታ መስጠቷንና በቀጣይም የተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ እንደምትሳተፍ ገልጻለች። ኅብረተሰብን የሚደግፍ ተግባር ላይ በስፋት መሰማራቷንና እስካሁን ለልማት ሥራ በተሰማራችበት አካባቢ የተለያዩ የድጋፍ ሥራ ማከናወኗን አመልክታለች።

የሴቶች ቀን ‹‹እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ ›› በሚል መሪ ሐሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ኛ ጊዜ፤ በሀገራችን ደግሞ ለ47ኛ ጊዜ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ደግሞ ለ8ኛ ጊዜ በዛሬው ዕለት የሚከበር ይሆናል።

# «የሴቶች ተሳትፎ በሌለበት የሀገርን ብልጽግና ማረጋገጥ አይቻልም»

**- ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ**

**መሠረት ገብረዮሐንስ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች ተሳትፎ በሌለበት የሀገርን ብልጽግና ማረጋገጥ አይቻልም ሲሉ በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የመሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ ገለጹ።

ወይዘሮ ልዕልቲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት ሀገር እንድትበለፅግ ሀገራዊ ሁኔታዎችን ለማረጋጋት የሴቶችን ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን አለበት ሲሉ ገልፀዋል።

የሴቶች ቀን ሲከበር በዓሉ ብቻ ማክበር ሳይሆን የሴቶችንም ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይዞት የሚመጣ አዎንታዊ ተፅዕኖ መኖር አለበት ያሉት ወይዘሮ ልዕልቲ በተለይም በመሪነት ቦታ ሴቶችን ማሳተፍ እንደ አንድ አቋም በመያዝና ወደ ተግባር በመቀየር ትልቅ ሥራ መሠራት አለበት ብለዋል።

የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከታች ካሉትን ማኅበረሰቦች መጀመር አለበት፣ሴቶች ትኩረት ይሻሉ ያሉት ወይዘሮ ልዕልቲ ይህ ለማረጋገጥ መንግሥት እየሠራ ነው ፤ የመንግሥት ጥረት ብቻ በቂ ስላልሆነ ሴቶች ለመለወጥ እራሳቸው መነሳሳትና አቅማቸውን ማውጣት አለባቸው ብለዋል።

ሴቶች ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን የማስተዋል ችሎታ በመጠቀም ውሳኔ የሚፈልጉ ቦታዎች ማስቀመጥ ውጤቱ ሰላማዊ ነው ያሉት ወይዘሮ ልዕልቲ ፣ ይህን ወደ ተግባር ለመቀየር የሁላችንም ርብርብና ተነሳሽነት ያስፈልጋል ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የተፈጠረው ጦርነት ተጎጂዎች የነበሩት ሕጻናትና እናቶች ናቸው፣የሰላም ጥቅምና አስፈላጊነት ከእናቶች በላይ የሚረዳ የለም ፣ የተፈጠረው የሰላም ስምምነት ዘላቂ እንዲሆን ሴቶች መታገል አለባቸው ሲሉ አብራርተዋል።

የሴቶች እኩልነት መረጋገጥ አለበት ይህ ደግሞ ሴቶች እራሳቸው ያለባቸውን ችግሮች በመወያየት ፣ በመመካከር ራሳቸው በራሳቸው የመፍታት አቅም ማዳበር አለባቸው ያሉት ወይዘሮ ልዕልቲ፣መንግሥት ይህን ሴቶች ወደፊት የማውጣት ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል እና ያለ ሴቶች ተሳትፎ ብልጽግና ማረጋገጥ እንደማይቻል በተለያየ መድረኮች እየገለፀ ነው ብለዋል።

# የሴቶችን መብትና ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ሁሉ ጫናዎች ተቋቁመው ወደ ፓርቲ ሲመጡ ደግሞ የሚመች ሁኔታ አይፈጠርላቸውም፤ ሞራልም የሚሰጣቸው አያገኙም። በዚህ ምክንያት ደግሞ ተሳትፏቸው የወረደ ነው ።

አሜሪካን አገር ኒዮርክ ከተማ ላይ ዓለም አቀፍ የሴቶች እንቅስቃሴ የተጀመረበት ዋናው ምክንያት ሴቶቹ እኩል ስለማይከፈላቸው፣ መብታቸው ስለታፈነ፣ በምክር ቤት መምረጥም መመረጥም አለመቻላቸው ሲሆን፣ ይህም የፈጠረው ብሶት ለራሳችን ጉዳይ ራሳችን መነሳት አለብን በማለት የጀመሩት ነው፤ ይህ እንግዲህ የሚያሳየን ማንኛዋም ሴት ብትሆን መብቷን ለማስከበር ራሷ ካልተነሳች ማንም ስለሷ የሚገደው እንደሌለ የሚያሳይ ነው።

ሴቶች በዚያን ወቅት ስለ መብታችን ብለው ባይነሱ ኖሮ እውቅናም አያገኙም፤ መብታቸውም አይከበርም ነበር ያሉት ዶክተር ራሔል፣መምረጥም መመረጥም ሳይችሉ ይቀሩ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ደግሞ በዚህ ዘመን ሴቶች የተከበሩላቸው መብቶች ቢኖሩም ብዙ የሚቀር ነገር መኖሩን ገልጸዋል። በየዓመቱ ቀኑን ከመዘከር ባለፈ ለመብታችን በመቆም የሚያስፈልገንን መብትና ነጻነት ዋጋ ከፍለን ለማግኘት ዝግጁ ካልሆንን እለቱን ማክበር ብቻውን በስጦታ የሚያሰጠን መብት አይኖርም ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹ዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን ስናከብር እንደ አገር የት ነው ያለነው? የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል ሲሉ አጽንዖት የሰጡት ዶክተሯ፣ የሴቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሞራላዊ ችግሮች ሁሉ የቱ ዘንድ ነው ያለው የሚለው መታሰብ አለበት ብለዋል። ሴቶች ለሚገጥሟት ችግሮች አይሆንም ማለት የምትችልበት አቅም ላይ ስለመሆኗም ማረጋገጥ ያስፈልጋል በማለት አመልክተዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሴቶች የምትመች አገር እየተገነባ ስለመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ተናግረዋል።

# ኢፕድ የሴት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማውሳት ይቻላል››ያሉት አቶ ጌትነት፤አሁንም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የሀገር ዳር ድንበር ለማስከበር የተሰለፉ ሴቶች ብዙ ናቸው። ከዚህ አንጻር ሴቶች ያልተሳተፉበት እንቅስቃሴ ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል በብዙ መልኩ ማረጋገጥ እንደሚቻል ገልጸዋል።

በዓሉን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ በሴት ጋዜጠኞች ተዘጋጅቶ ለንባብ የሚበቃው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጠናክሮ መቀጠሉንና የሚያበረታታም እንደሆነ የገለጹት አቶ ጌትነት፤እንዲህ ያለው ባሕል መለመዱ የበለጠ እንዲነቃቁ፣እንዲበረታቱ እንዲሁም አቅማቸውን ለማሳየት እንዲያግዝ የታሰበ እንጂ በመደበኛው የጋዜጣ ሥራ ውስጥ ከሪፖርተርነት ጀምሮ ባለው ደረጃ ውስጥ ሴቶች ስለሌሉ እንዳልሆነ አስረድተዋል።

በተቋሙ ውስጥ መሪም ፈጻሚም ሆነው የሚሠሩ፣ የሚበረታቱና የሚመሰገኑ ሴቶች መኖራቸውንም አቶ ጌትነት ተናግረዋል።

ድርጅቱ የነበሩበትን ችግሮች እየተሻገረ ቀጣይነት ያለው የለውጥ (ሪፎርም) ሥራ ላይ እንደሆነና ለውጡን በማስቀጠል ውስጥም የሴቶች ሚና ጉልህ መሆኑን በግላቸውም የሚያኮራቸው እንደሆነ ጠቁመዋል።

በመልዕክታቸውም ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን፤ሴቶች ለመብታቸው ትግል ያደረጉበት ታሪክ ያለው እንደሆነ ተናግረዋል። በመንግሥት ደረጃም ትኩረት መሰጠቱንና በተለይም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከዚህ ቀደም ከንግግር ያላለፈ የነበረውን ወደ ተግባር መቀየራቸውን አመልክተዋል። በካቢኔያቸው ውስጥ ሴቶች ወደ ሚኒስትርነት እንዲመጡ በማድረግ የሴቶች ተሳትፎ ፍትሐዊ እንዲሆን ጥረት የተደረገበትና ታሪካዊ ውሳኔ የታየበት እንደሆነ አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሴቶችን ወደ አመራርነት የማምጣቱ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥል!

ዓለም አቀፍ ይዘት ኖሮት እኤአ ከ1975 ጀምሮ በተለያዩ መሪ ሐሳቦች እየተከበረ የመጣው የሴቶች ቀን ዘንድሮም «እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ» በሚል መሪ ሐሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ኛ ጊዜ፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ47ኛ ጊዜ በዛሬው ዕለት ታስቦ ይውላል፡፡

ቀኑ በዚህ መልኩ ታስቦ በሚውልባት ኢትዮጵያ ደግሞ ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት ከግማሽ በላይ ቁጥር የያዙት ሴቶች ናቸው። ይህ ደግሞ የቁጥራቸውን ያህል ቀርቶ ሲሶውን ያህል ለመስራት የሚያስችል ዕድል ቢፈጠርላቸው ለሀገር ልማትም ሆነ እድገት ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚችሉ አመላካች ነው። በኢትዮጵያ የታሪክ ሁነቶችና ጉዞ ውስጥ ሴቶች የነበራቸውን ከፍ ያለ ሚና በዓድዋው የጦር ሜዳ ተጋድሎና ድል ጭምር አስመስክረዋል፡፡

ይህ እውነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ለሴቶች ዕድል በማቻቻቱ ረገድ፤ ባለፉት ዘመናት በተለይም ከለውጡ በፊት ሴቶች እድሉ እንደተሰጣቸው ተደርጎ ብዙ ሲባል ቢቆይም፤ በስማቸው ከመነገድ ያለፈ ስፍራ ሲሰጥ አልታየም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በየደረጃ ያለው የአመራር ተሳትፏቸው ከብዛታቸው አንጻር ሲሰላ ከወንዶች ጋር ያለው ጥግግት ሚዛን የሚደፋ ባለመሆኑ ነው።

ይሁንና ከለውጡ ማግስት የኢፌዴሪ መንግስት ሴቶችን በአቅምና ችሎታቸው እየለዩ ወደ አመራርነት መንበር በማምጣቱ ረገድ የሚያስመሰግነውን ተግባር መፈጸም ችሏል። በተለይም በመንግስት ካቢኔ እና በሌሎች ተመሳሳይ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የሴት አመራሩ ቁጥር ከወንድ ጋር ሲነጻጸር መሳ ለመሳ እንዲሄድ ማድረጉም የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

መሪነት ማለት ደግሞ የስልጣን ቦታ የመያዝ ጉዳይ ሳይሆን መምራት የመቻል ጥበብ እንደመሆኑ ስፍራ የተሰጣቸው ሴቶች በአደባባይ ጥንካሬያቸውንም ማሳየት ችለዋል። የኢፌዴሪ መንግስትም በሴቶች ችሎታ በመተማመን ወደ አመራር እርከን እንዲመጡ ያደረገበት ሂደት ለሌሎች አገራት ጭምር አርአያ እንደመሆኑ ከፍ ያለ ዓለም አቀፍ ሙገሳን ተችሯል።

በላይኛው የአመራርነት እርከን ላይ የታየው በጎ ተግባር ግን በየደረጃው እስከ ወረዳ ባሉት የአመራርነት ቦታዎች በመተግበር በኩል ሰፊ ክፍተት አለ። በመሆኑም መንግስት ሴቶችን በከፍተኛ የአመራር እርከን ለማምጣት የሄደበትን ያህል፤ ከፍተኛ ቁጥርና የኃላፊነት ሚና ባለው ብቻ ሳይሆን፤ የመንግስት የአስተዳደር ጉድለት በሚጎላባቸው የታችኛው እርከን ሴቶችን በየደረጃው ወደ ኃላፊነት ማምጣት ቢችል ሴቶች በውስጣቸው ያለውን የመምራት ጥበብ በመጠቀም በርካታ ውጤት ማስመዝገብና ትርፋማ መሆን ይቻላል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ባሉ የተለያዩ ተቋማት ውስጥ ሴቶች ስፍራ ተሰጥቷቸው ችሎታቸው የሚመዘንበት ሁኔታ እምብዛም ባለመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራ፤ ከተከለሉበት አሊያም ከተደበቁበት ወጥተው ብቃታቸውን ለማሳየት የሚያስችላቸው ድጋፍ ሊደረግላቸውም ይገባል፡፡

ሴቶች የመምራት ብቻ ሳይሆን በአመራር ጥበባቸው ፈተናዎች ሲያጋጥማቸው በጥበብ የማለፍ ትልቅ ተሰጥኦ አላቸው። ምቹ በሆነ ሁኔታ ውስጥም ሆነ ባልተመቻቸ ቦታ ስራቸውን በብቃት መውጣት የሚችሉ ሴቶች መኖራቸውም ከግምት ውስጥ ገብቶ ተገቢው ስፍራ እስካልተሰጣቸው ድረስ ሀገርን ወደተፈለገው ከፍታ ማሻገር ከባድ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ሀገራችን ከድህነትና ኋላቀርነት ተላቅቃ በኢኮኖሚ ጠንካራ ከሆኑት ተርታ ለማሰለፍ የሚደረገው ሩጫ ያለ ሴቶች ተሳትፎ እንደ «ባለህበት እርገጥ» የሚቆጠር ነውና በየደረጃው ላለው የአመራር ቦታ ሴቶችን ወደፊት ማምጣት ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም። ሴቶች በማኅበራዊው፣ ኢኮኖሚያዊውም ሆነ የሀገርን ሕልውና በማስጠበቅ ረገድ የተወጡት ከፍ ያለ ሚናም የዚህ ዐቢይ ማሳያ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የሀገራችንን ልማት ለማሳለጥ የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው በሚል መፈክር ብቻ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ብሎም የሀገራችንንም ልማት ማሳለጥ አይቻልም። ለተሳትፎ ሲባልም «ሴቶች እዚህ እና እዚያኛው ስልጣን ላይ ቢቀመጡ የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ» በሚል አስተሳሰብ ብቻም ስኬታማ ስራ መስራት አይቻልም። ሀገራችን በተያያዘችው የብልጽግና ማማ ላይ የመውጣት እቅድ ስኬታማ መሆን የሚችለው ሴቶችም ከወዲሁ መርከቡን ተሳፍረው የበኩላቸውን ማበርከት ሲችሉ ብቻ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

በማኅበረሰባችን ውስጥ አሁንም ድረስ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት፣ የማሸማቀቅና የማናናቅ እኩይ ሁነቶች መኖራቸው እሙን ነው። ዛሬም ቢሆን በተማረችም ሆነ ባልተማረች እንዲሁም በአመራር ደረጃ ባለችም ሆነ ተራ ሰራተኛ በሆነች ሴት ላይ በተለያየ መንገድና ዓይነት ጉዳት ሲደርስባቸው መታየቱ አልቀረም።

ምክንያቱም ሴቶችን ማደናቀፍ የሀገር ልማትን እንደማደናቀፍ ብሎም ሰላምን እንደማደፍረስ ይቆጠራል። በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ በየቦታውና በየደረጃው ላሉ ሴቶች ተገቢውን ስፍራ በመስጠት ክህሎታቸውን በአደባባይ አውጥተው እንዲያሳዩ የተጀመረው ማበረታታት ሊጠናከርና የታታሪነት እና የፀረ ሙስና ትግል ምሳሌ የሆኑትን ሴቶችን ወደ አመራርነት የማምጣቱም ተግባር ሊቀጥል ይገባዋል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሴትን ይዞ ወደ ብልጽግና ጉዞ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

**ሴቶች ተፈላጊና አስፈላጊነት የሰው ዘርን በመተካት ትውልድን የማስቀጠል ብቻ አይደለም። ከመውለድና ከማሳደግ ጸጋቸው ባለፈ አበርክቷቸው የትየለሌ ነው። በተፈጥሮ ከተሰጣቸውና ልዩ ከሚያደርጋቸው ተፈጥሯዊ ባህሪ በተጨማሪ ሴቶች ዕድሉ ከተሰጣቸው በየትኛውም መስክ ቀዳሚና ልዩ መሆን የሚችሉ ብርቱዎችና አገርን በበጎ የሚያስጠሩ ናቸው**

ወቅቱ እኤአ 1908 ነው። በኒዮርክ ከተማ ነዋሪ የሆኑ ጥቂት ሴቶች የተሻሻለ የሥራ ሰአትና ደመወዝ እንዲኖራቸው፣ የመምረጥ መብታቸው እንዲከበር አደባባይ በመውጣት ድምጻቸውን አሰሙ። ከአንድ ዓመት በኋላም የአሜሪካን ማህበራዊ የሴቶች ብሄራዊ ቀን በማለት ማወጁን የታሪክ ድርሳን ያስረዳል። በዚህ የአመጽ እንቅስቃሴ ስሟ ጎልቶ የሚነሳው ክላራዚክትን የተባለች ሴት በየዓመቱ በዓለም ዙሪያ የሚከበረው ዓለም አቀፍ ሴቶች ቀን (ማርች 8) ዓለምአቀፋዊ ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ጉልህ ሚና ተወጥታለች፡፡

በብዙ ትግል ድል ያጎናፀፉትን ማሰብና ቀኑን መዘከር ግድ ይላል። ታዲያ ትግሉን በማስቀጠል በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍ ጠንካራ የሆኑ ሴቶችን ማፍራት ሳይዘነጋ ነው። መብቶቻቸውን ለማስከበር፤ ከወንዶች ባልተናነሰ አምራች ሆነው እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር ብሎም በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ሚና እንዳላቸው በተግባር ያሳዩ ሴቶችንም ማፍራት ተችሏል። የሥርዓተ ፆታ እኩልነት እስኪረጋገጥ ግን ትግሉ መቀጠል አለበት። የወንድ የበላይነትና ሴቷን የበታች አድርጎ ማየት ጎልቶ በሚስተዋልባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ደግሞ ሥራዎች ይጠበቃሉ፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሴቶች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካው መስክ አበረታች የሆነ እንቅስቃሴ እያደረጉ ቢሆኑም በማህበረሰቡ የተሳሉበት ሥነልቦና ጥንካሬያቸው አጉልቶ እንዳይወጣ ተጽእኖው አድርጓል። እንዲህ በተለያየ ጫና ውስጥም ሆነው ግን ለቤተሰባቸው፣ ለአካባቢያቸውና ለአገራቸው የላቀ አበርክቶ እያደረጉ ይገኛሉ። በአርዓያነትም የሚጠቀሱ ሴቶችን ማፍራት ተችሏል፡፡

ሴቶች በተሰማሩበት ማንኛውም የሥራ ዘርፍ ውጤታማ ከመሆን ውጭ ምርጫ የላቸውም። ምንም እንኳን የወንድ በሆነ ዓለም ውስጥ ሴቶችን ወደፊት ማውጣት ቢከብድም፤ ወደፊት ለወጡት ወንዶች ግን የጀርባ አጥንት መሆናቸው ዓለም የመሰከረውና የሚታይ ሃቅ ነው። ሴቶች የማይቻል የሚመስለውን ሁሉ ችለው፤ ቀዳዳውን ጠግነው፤ የጎበጠውን አቃንተው፤ ለችግሮች ሁሉ እማ መላ ሆነው፤ ጨለማውን ገፈው ብርሃን መሆን ይችላሉ። ሴት ልጅ እናት፣ እህትና ሚስት ከመሆን ባለፈ በቤት ውስጥና በተለያዩ ማህራዊ ግንኙነቶች እንዲሁም አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ሳይቀር ትርጉም ያለው ሥራ በመሥራት አገርን መለወጥ የምትችል ተፈላጊና አስፈላጊ ናት።

የሴቶች ተፈላጊና አስፈላጊነት የሰው ዘርን በመተካት ትውልድን የማስቀጠል ብቻ አይደለም። ከመውለድና ከማሳደግ ጸጋቸው ባለፈ አበርክቷቸው የትየለሌ ነው። በተፈጥሮ ከተሰጣቸውና ልዩ ከሚያደርጋቸው ተፈጥሯዊ ባህሪ በተጨማሪ ሴቶች ዕድሉ ከተሰጣቸው በየትኛውም መስክ ቀዳሚና ልዩ መሆን የሚችሉ ብርቱዎችና አገርን በበጎ የሚያስጠሩ ናቸው። ከቀደሙት ቀደምቶች ብንነሳ ሉሲ (ድንቅነሽ) ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ለመሆኗ ማረጋገጫ ምሳሌ በመሆን ለአገር ኩራት የሆነችው ሉሲ (ድንቅነሽ) ሴት ናት።

ሉሲ (ድንቅነሽን) በቀዳሚነት አነሳን እንጂ በቀደመው ዘመንም ይሁን አሁን ባለንበት ዘመን ተዓምር የሠሩ፣ እየሠሩ ያሉና መሥራት የሚችሉ እልፍ አዕላፍ እንስቶች አሉ። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ እንቅስቃሴያቸው አንቱ የተባሉ ለቁጥር የበዙ ኢትዮጵያዊ እንስቶች አሉ። በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ዘርዐያቆብ ዘመን ሴቶች ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸው በተጨማሪ በፖለቲካው ዘርፍ ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራችው። ንጉሱ ዘጠኝ ሴቶችን በከፍተኛ የመንግሥታቸው አመራር ውስጥ ሾመው እንደነበርም ታሪክ ይነግረናል። በአፄ ልብነድንግል የንግሥና ዘመንም ንግሥት እሌኒ የንጉሡ አማካሪ ነበረች። የአክሱም ሥልጣኔ ንግሥት የሰለሞናዊ ስርዎ መንግሥት አስጀማሪ ንግሥተ ሳባንም ማንሳት እንችላለን። በዘመነ መሳፍንት ወቅትም እንዲሁ ጉልህ ተሳትፎ የነበራቸው በርካታ ሴቶች ስለመኖራቸው ታሪክ ያስረዳል።

ዘመነ መሳፍንት ሲነሳ ለዛሬ ነጻነት የበቃንበት የዓድዋ ድል ደምቆ መታየቱ የግድ ነው። ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካውያን ኩራት የሆነውና ደማቅ አሻራ ያኖረው የዓድዋ ድል ሲነሳ ደግሞ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ከፊታችን ድቅን ማለታቸው አይቀሬ ነው። ጀግናዋ ሴት ጠንካራና ብልኋ መሪ ጣይቱ ብጡል በእቴጌነት ዘመናቸው የነበራቸው የፖለቲካ እና የአመራር ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር። ብዙዎች እንደሚስማሙት እቴጌ ጣይቱ የጦር መሪ፣ የጦርነት ዘዴ ቀያሽ፤ የአዲስ አበባ ከተማ እንድትመሰረት ሐሳብ አመንጭ፤ ብልህ እና ጥበበኛ ሴትም ነበሩ።

የፖለቲካ ተሳትፏቸውን እንደማሳያ ብንጠቅስ፣ ኢትዮጵያን በኃይል በቅኝ ለመግዛት የመጣው ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን በውጫሌ አንቀጽ 17 የውል ስምምነት ላይ ኢትዮጵያን ከጨዋታ ውጭ ሊያደርጋት የነበረውን ሴራውን በማክሸፍ ሚና የነበራቸው እቴጌ ጣይቱ ውሉ ሊያስከትል የሚችለውን አገራዊ ጉዳት ቀድሞ በመረዳት ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ምኒልክ ውሉን ቀደው በጣልያን ላይ ጦርነት እንዲታወጅ ጠንካራ አቋም የወሰዱ ብርቱና ኩሩ ሴት መሆናቸውን ታሪክ ያስታውሳቸዋል። በዓድዋው ጦርነት በተዋጊነት እንዲሁም በጦርነቱ የተጎዱትን ወታደሮች በማከምና በማበረታታት በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ውስጥ ያለተነገረላቸው ብዙ ሴቶች መኖራቸውን ታሪክ ያስታውሳል።

ከቀደምቶቹ መለስ ስንል ታዲያ ዛሬም በጦር ሜዳው መስክ ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር የሚዋደቁ ጀግኒቶችን ቤት ይቁጠራቸው። ከጦር ሜዳው ባሻገርም ኢትዮጵያ ስሟ በዓለም መድረክ ከፍ ብሎ እንዲጠራ የሚተጉ ሴት አትሌቶቻችን እልፍ ናቸው። «ወላድ በድባብ ትሂድ» እንዲሉ ከለምለሟ ምድር ኦሮሚያ፣ ከሰሜኑ የአገሪቷ አካባቢ እንዲሁም ከደቡብ የሚተካኩቱ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም አደባባይ ደግመው ደጋግመው ከፍ አድርገዋል።

በማህበራዊ ዘርፉም እንዲሁ በአበርክቷቸው ነጥረው የወጡ በርካታ ሴቶች አሉን። ከእነዚህም መካከል ወላጅ አልባ ለሆኑ ህጻናት እናትም አባትም ሆነው የብዙ ህጻናትን ዕድል ፈንታ መስመር የቀየሱ ወይዘሮ አበበች ጎበናን ማንሳት የግድ ነው። «ስም ከመቃብር በላይ ይውላል» እንዲሉ አበበች ጎበና ሁሌም ሲወሱ የሚኖሩ የደጋግ ልቦች ተምሳሌት ናቸው። እንደ አበበች ጎበና ሁሉ ታዲያ ስማቸውን ጠርተን የማንዘልቃቸው አንድ ሺ አንድ ሴቶቻችን እናት፣ ሚስትና እህት ሆነው አገራቸውን በተለያየ ዘርፍ እያገለገሉ ይገኛሉ።

በኢኮኖሚው ዘርፍ ቢባልም ጉልት ቸርችረው ቤታቸውን ሞልተው፤ ከኑሮ ጋር ታግለው ትውልድ ከሚያፈሩ እናቶች ጀምሮ እስከ ላይኛው ወጪ ገቢ ንግድ ድረስ የሚሳተፉ ሴቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ጉልህ ድርሻ በመወጣት ላይ ናቸው። በፖለቲካው ዘርፍም እንዲሁ በተለያዩ የሥልጣን እርከን ላይ ሆነው አገራቸውን በታማኝነት ያገለገሉ፣ እያገለገሉ ያሉና ዕድሉ ቢሰጣቸው ደግሞ የበለጠ የሚሰሩ እልፍ እንስቶች በኢትዮጵያ ምድር አሉ። እነዚህን ብርቱና ትጉ ሴቶችን ይዘን ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና እናሻግር በማለት አበቃሁ ሰላም!

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**

“እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”

# የተሸናፊነት ስሜትን ከውስጣቸው ያስወገዱት እንስት

**እፀገነት አክሊሉ**

ዶክተር ራሄል ባፌ ተወልደው ያደጉት በቀድሞው ከፋ ክፍለ አገር የአሁኑ ደቡብ ምዕራብ ክልል ዳውሮ ዞን ውስጥ ነው። እድሜያቸውም ለትምህርት ሲደርስ ደግሞ ዋካ ከተማ ውስጥ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን የትምህርት ቆይታቸውን አጠናቀዋል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ከአካባቢያቸው ውጪ ዱራሜ የአሜሪካን ሚሽንና የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተክርስቲያን ያቋቋሙት አዳሪ ትምህርት ቤት መከታተል ችለዋል።

ዶክተር ራሄል በጣም ጎበዝ የሚባሉ ተማሪ ከመሆናቸው የተነሳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሰው 12ተኛ ክፍል ሲፈተኑም ጥሩ ውጤትን በማምጣት በቀጥታ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላይ የመመደብ እድልን ያገኙም ናቸው።

"....... በትምህርቴ ጎበዝ ነበርኩ እንደነገርኩሽ ማትሪክ ተፈትኜም ያመጣሁት ውጤት በጣም ጥሩ ስለነበር በቀጥታ ነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገባሁት" ይላሉ።

ለቤታቸው የመጀመሪያ ልጅ የሆኑት ዶክተር ራሄል፤ ከአራት ወንድምና ከአራት እህቶቻቸው ጋር በመሆን ጥሩ ቤተሰባዊ ጊዜን ማሳለፋቸውን ይናገራሉ። በተለይም አባታቸው መምህር መሆናቸው የትምህርትን ጥቅም በውል ስለተረዱት እሳቸውን ጨምሮ ሁሉም ልጆች በትምህርታቸው እንዲጎብዙ መደበኛ ስራቸው አድርገው እንዲይዙት ከማድረግ እስከ ማበረታትና ውድድርን በመካከላቸው እስከመፍጠር የዘለቀ ሚናቸውን ስለመወጣታቸው ያስታውሳሉ።’

እሳቸውን ጨምሮ ልጆቻቸውን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ የእናታቸውም ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም። በተለይም በወቅቱ እንደ አሁን ዘመን መዋዕለ ህጻናት የሚባል ባይኖርም እናታቸው የፊደል ሰራዊትን ያስተምሩ ስለነበር በልጆቻቸው እድገት እንዲሁም እውቀት ላይ ከፍ ያለ ሚናቸውን ሲወጡም ነበር።

"........እናቴም ሆነች አባቴ ስለትምህርት ትልቅ ግንዛቤ የነበራቸው በመሆኑ እኛን ለማስተማር ጥረትም አድርገዋል፤ ከአካባቢው ውጪ እንኳን ሄደን እንድንማር ከፍ ያለ እገዛን ያደርጉልን የነበረው ጥቅሙን በመረዳታቸው ነው" በማለት ይናገራሉ።

ዶክተር ራሄል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ይቀላቀሉ እንጂ የትምህርት ሂደቱ ግን ባሰቡት ልክ ጤናማ አልሆነላቸውም ትልቁ ምክንያት ደግሞ በወቅቱ የነበረው ፖለቲካዊ ሁኔታ ነበር፡፡ ቤተሰቦቻቸውም ፖለቲካው ፈጥሮባቸው የነበረ ችግር በመኖሩ የከፍተኛ ትምህርታቸውን ባሰቡት ልክ ማስኬድ ሳይችሉ ቀሩ።

".......አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ትምህርት ክፍል አራት ኪሎ ነበር የገባሁት ነገር ግን ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ላይ የምፈልገውን የትምህርት ዓይነት እንኳን ሳልመርጥ ነው ለማቋረጥ የተገደድኩት፤ በራሴና በቤተሰቤ ችግር ምክንይት ትምህርቴን ባለበት ባቆመውም ራሴን ለማስተዳደር የሚሆን ስራ ግን ለማግኘት አልተቸገርኩም ነበር፡፡ በወቅቱ በትምህርት ሚኒስቴር ስር በነበረ ማስ ሚዲያ ገባሁ፤ ነገር ግን ብዙ ሳልሰራ ለቅቄ ጭነት ማመላለሻ የሚባል ድርጅት ውስጥ ገባሁ" ይላሉ።

ይህም ቢሆን ግን ዶክተር ራሄል የመማር እልሃቸው ውስጣቸው ስለነበር ነገሮች ሲረጋጉና እሳቸውም አረፍ ካሉ በኋላ ዩኒቨርሲቲውን ዳግም ምዝገባ ጠይቀው ፋርማሲ የትምህርት ክፍል በቀን ትምህርታቸውን ለመቀጠል ገቡ። እልሃቸውና ሲማሩም የሚችላቸው ባይገኝም አሁንም ግን በድጋሚ የጀመሩትን መጨረስ ባለመቻላቸው ዳግም ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ።

".......ትምህርቱን አሁንም ለማቋረጥ የተገደድኩት በራሴ የግል ምክንያት ነው፤ ነገር ግን ትምህርቱን ባቋርጥም የራሴን ህይወት መቀጠል ነበረብኝና ስራዬን እየሰራሁ ትዳር መሰረትኩ፤ ልጅም ወለድኩ፡፡ አሁን መረጋጋት እየጀመርኩ ስለሆነ የትምህርት መስኬን ከተፈጥሮ ሳይንስ ወደ ማህበራዊ ሳይንስ በመቀየር መማር አለብኝ ብዬ ወስኜ ማኔጅመንት ለመማር ገባሁ" ይላሉ።

የማኔጅመንት ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ በሚገባ አጠናቀቁ፤ ከዛም ብዙም ሳይቆዩ በቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን የትምህርት መስክ ለመከታተል



ዶክተር ራሄል ባፌ

ቻሉ። እየሰሩ፣ ቤተሰብ እያስተዳደሩና ልጆች እያሳደጉ በመማርም የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአስደሳች ሁኔታ ለማጠናቀቅ ቻሉ።

ከዩኒቨርሲቲ በኋላ በግብረ ሰናይ ድርጅት ወስጥ ስራን የጀመሩት ዶክተር ራሄል፤ በተለይም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሲማሩ ከአለቆቻቸው ይደርሳቸው የነበረውን ማበረታታትና ጊዜን የመስጠት ነገር ትልቅ ውለታ እንደሆነ ይናገራሉ ፤ በዚህ አጋጣሚም ያመሰግናሉ።

".......ማስተርሴን ስጨርስ የሶስተኛ ዲግሪዬን ወይም ዶክትሬቴን ከአሜሪካን አገር ካሊፎርኒያ ከሚገኝ ቪዝን ዩኒቨርሲቲ በሊደር ሺፕ የትምህርት ዘርፍ ለማግኘት ችያለሁ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች በቀላሉ የታለፉ አይደሉም ብዙ ውጣ ውረዶች ነበሩበት፡፡ ነገር ግን እኔ ደግሞ ለነገሮች ትኩረት የምሰጥ ለራሴ ግብ አስቀምጬ የምንቀሳቀስ ነበርኩ። ትምህርቴን አቋርጬ ወደትዳር ከገባሁ በኋላም ቢሆን ባለቤቴ በጣም መልካም ሰው ስለነበር ግቤ ጋር እንድደርስ በከፍተኛ ሁኔታ አግዞኛል" በማለት ያሳለፉትን ውጣውረድ ይናገራሉ።

እሳቸውና ባለቤታቸው በከፍተኛ ሁኔታ በመደጋገፍና ፕሮግራም በማውጣት ቤታቸውን ይመራሉ፡፡ በተለይም ለልጆቻቸው ጊዜን ከመስጠት ጀምሮ ትልቅ መስዋዕትነት በመክፈል የተሻለ ትምህርት ያገኙበታል ባሉበት ቦታ አስተምረዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የከፈላቸው ይመስላል፤ ምክንያቱ ደግሞ እሳቸው ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ሲመረቁ የመጨረሻ ልጃቸውም በዶክተርነት ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ስትመረቅ ተገጣጥሟልና፤ ይህ ለዶክተር ራሄል እጅግ በጣም ትልቅ ቦታ ያለውና አስደሳች ሁኔታ ነበር።

ዶክተር ራሄል ‹‹ከልጆቼ ጋር እኩል ነው የተማርነው›› ይላሉ፡፡ በዚህም እሳቸው የእናትነታቸውን እነሱ ደግሞ የልጅነታቸውን እየተረዳዱ ኑሮ ሳይከብዳቸው ኃላፊነት ብቻቸውን ተሸክመው ሳይማረሩ ሁሉም ልጆቻቸው እስከ ሁለተኛና ከዛም በላይ ዲግሪ ተመርቀው በትልልቅ ተቋማት ውስጥ እያገለገሉ ይገኛሉ።

ዶክተር ራሄል አገራቸውን በእጅጉ ለማገልገል የሚፈልጉ ከመሆናቸው የተነሳ ልጆቻቸውም ለአገራቸው ፍቅርና ክብር እንዲኖራቸው አድርገው ስለማሳደጋቸው ይናገራሉ ።".....ሁሉም ነገር የሚያምረው በአገር ነው! ከአገር ከወጡ በኋላ ብዙ ችግር አለ፤ ምናልባት ኑሮ ሊመች ይችል ይሆናል፤ ግን ደግሞ ማን እንደ አገር ፤ ልጆቼም የእኔን አይተው ከአገራቸው መውጣት አይፈልጉም ፤ የሚገርምሽ ወንዱ ልጄ የትምህርት መስኩ አርክቴክቸር ነበር፡፡ እናም በጣም ጎበዝ ተማሪ ስለነበር የኢትዮጵያን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወክሎ በርካታ አገራትን የመዞር እድል አግኝቶ የነበረ ቢሆንም አንድም ቀን ግን ወጥቶ ስለመቅረት አስቦ አያውቅም"ይላሉ።

ሴቶች የቤታቸው ራስ ናቸው የሚባለው ያለምክንያት አይደለም፤ የቤቱን የሞላ ጎደለ እንዲሁም የውጪውን ሁኔታ አጣጥመው የመምራቱ ትልቅ ኃላፊነት በጫንቃቸው ስለሚሸከሙ ነው። ዶክተር ራሄልም ቤተሰብን መስርተው ትምህርት እየተማሩ ስራ እየሰሩ ከዚህ ጫና ያመለጡ አልነበሩም ፤ በወቅቱም ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሟቸዋል። ግን ደግሞ ሴት ነኝ አልችልም ሳይሉ ነገሮችን እንደ አመጣጣቸው እየመለሱ ከባለቤታቸው ጋር እየተጋገዙ ሁሉን አሳልፈዋል።

"......ከልጅነቴም ጀምሮ ሳድግ የተሸናፊነት ስሜት በውስጤ የለም ፤ እንደውም የማይቻል ነገር የለም ብዬ ነው የማምነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ነገር የቱንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለኝ ዝቅ ብዬ ለመስራት የማልሸማቀቅና ችግሩን ለማለፍ የምችል ነኝ፤"ይላሉ።

ዶክተር ራሄል ቀድሞ እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፖለቲካን በሩቁ ሲሉ ነው የኖሩት ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ከቤተሰባቸው ጀምሮ በተለይም ሀይማኖትን በተመለከተ ጠለቅ ያለ እውቀት ያላቸው አባት ስለነበራቸው ፖለቲካና ሀይማኖት አብሮ አይሄድም በሚል ነው ያደጉት። አባታቸውም "ልጆቼ ፖለቲካ ውስጥ አትግቡ ስራችሁን ስሩ አገራችሁንም በሙያችሁ አገልግሉ " ይሏቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

ይህም ቢሆን ግን የአገራቸው ፖለቲካዊ ሁኔታ ያሳሰባቸው እንደውም እስከ መቼ ነው ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ እንዲወስኑ እያደረግን አገራችንና እኛ የምንፈልገውን ነገር ሳናገኝ የምንኖረው የሚለው ነገር ያሳሰባቸው ስለነበር ዶክተር ራሄልም ራሴ ፖለቲካው ውስጥ ገብቼ በመሳተፍ የማመጣውን ለውጥ ማየት አለብኝ ብለው እንደገቡ ይናገራሉ።

"...... በግሌ ሃሳብ ማቅረብ ምክር ቤትም ራሴን ችዬ ተወዳድሬ ቦታ ሊኖረኝ ይችላል ብዬ ማሰብን ጀመርኩ፤ እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ነገር አባቴ ፖለቲካ ውስጥ እንዳትገቡ ብሎ አሳድጎን አሁን እኔ ደግሞ ፖለቲከኛ ለመሆን ማሰቤ ለራሴ ስላስፈራኝና እሱንም ስለፈራሁት እስኪ በቅድሚያ ላማክረው ብዬ ጠየኩት ፤ ለመጀመሪያ ጊዜም ከእሱ ያልጠበኩት " እግዚአብሔር ካለው ማን ይከለክላል" የሚል ምላሽ ሰጠኝ፤ በመሆኑም ልብሽ የተሰማውን አድርጊ ሲለኝ በጣም ነበር የተደሰትኩት"በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

"ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1983 ዓ.ም መንግስት አደረጃጀቴን በብሔር ብሔረሰብ ነው የማደርገው ሲል የእኛ አካባቢ ወደኋላ እንዳይቀር እንዲመዘገብ ለማድረግ አስችያለሁ፤ በመቀጠልም ወደ ኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ውስጥ ተቀላቀልኩ" ፤ እዚህ ላይ ግን ዶክተር ራሄል ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ ይሰሩ ነበርና እነሱ ደግሞ የማንንም የፖለቲካ ድርጀት አባል ስለማይፈልጉ ሁኔታው ቢያስቸግራቸውም ትንሽ ጊዜ በድብቅ የፖለቲካ ስራቸውን ሲሰሩ ቆዩ።

ዶክተር ራሄልን ከፖለቲካው ተሳትፎ የሚያርቃቸው ምክንያት ተፈጠረ በተለይም ባለቤታቸው የኢሰፓ አባል በመሆናቸው ምክንያት ከስራ ሲታገዱ የቤተሰባቸው የመኖር ህልውና በእሳቸው ላይ ወደቀ፤ አሁን የፖለቲካ አባል መሆናቸው ከታወቀ ከስራ ሊሰናበቱ ነው በመሆኑም ለቤተሰባቸው ህልውና መቀጠል ሲሉ ፖለቲካውን አቁመው ስራቸው ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግን መረጡ።

".......ነገሮች ሲስተካከሉና የፖለቲካው ሁኔታ እየባሰ ሄዶ አስገዳጅ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ ሲደርስ ሕወሓትም መጥቶ ደርግን እንድንናፍቅ ሲያደርገን ሁላችንም ለአገራችን የድርሻችንን መወጣት አለብን በሚል ውሳኔ ፖለቲካውን ተቀላቀልኩ"ይላሉ።

ፖለቲካ ለሴቶች አስቸጋሪ የሚሆንበት ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንዱ ባህላችን ሲሆን ሌላው ደግሞ ኢኮኖሚያዊ አቅማችን ከወንዶቹ ጋር ሲነጻጸር ዝቅ ያለ መሆኑ የቤት እመቤቶች መብዛታቸው ይጠቀሳል፡፡ ከወላጆችና ከባሎች ፍቃድ ውጪ መሆንም ከባድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ሁሉ ጫናዎች ተቋቁመው ወደ ፓርቲ ሲመጡ ደግሞ የሚመች ሁኔታ አይፈጠርላቸውም ሞራልም የሚሰጣቸው አያገኙም በዚህ ምክንያት ደግሞ ተሳትፏቸው የወረደ ነው ።

ለምሳሌ ማርች 8 እንቅስቃሴ አሜሪካን አገር ኒዮርክ ከተማ ላይ ነው የተጀመረው፡፡ ይህ ሲጀመርም ሴቶቹ እኩል ስለማይከፈላቸው፣ መብታቸው ስለታፈነ፣ በምክር ቤት መምረጥም መመረጥም አለመቻላቸው የፈጠረው ብሶት ለራሳችን ጉዳይ ራሳችን መነሳት አለብን በማለት እንቅስቃሴ ጀመሩ፤ ይህ እንግዲህ የሚያሳየን ማንኛዋም ሴት ብትሆን መብቷን ለማስከበር ራሷ ካልተነሳች ማንም ስለሷ የሚገደው እንደሌለ ነው።

በመሆኑም ሴቶች በዛን ወቅት ስለ መብታችን ብለው ባይነሱ ኖሮ እውቅናም አያገኙም መብታቸውም አይከበርም ነበር፤ መምረጥም መመረጥም ሳይችሉ ይቀሩ ነበር፤ አሁን ደግሞ በዚህ ዘመን ሴቶች የተከበሩላቸው መብቶች ቢኖሩም አሁንም ብዙ የሚቀር ነገር ስላለ በየዓመቱ ቀኑን ከመዘከር ባለፈ ለመብታችን በመቆም የሚያስፈልገንን መብትና ነጻነት ዋጋ ከፍለን ለማግኘት ዝግጁ ካልሆንን እለቱን ማክበር ብቻውን በስጦታ የሚያስጠን መብት አይኖርም።

"........ማርች 8ን ስናከብር እንደ አገር የት ነው ያለነው? የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። የሴቶች ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሞራላዊ ችግሮች ሁሉ የቱ ጋር ነው ያሉት? ሴቶች ለሚገጥሟት ችግሮች አይሆንም ማለት የምትችልበት አቅም ላይ ናት ወይ ? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሴቶች የምትመች አገርስ እየገነባን ነወይ? የሚለው ሊታይ ይገባል" ይላሉ።

ዶክተር ራሄል ባፌ እራሳቸውንና የኢትዮጵያን ሴቶች በመወከል በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ በሰብሳቢነት ለአንድ ዓመት ተኩል አገልግለዋል፤ ሴቶች ወደመሪነት ቢመጡ እንደማያስወቅሱ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንደሚችሉ፤ ከእኔ በኋላ ለሚመጡት ይችላሉ የሚለውን ነገር ለማንጸባረቅና የሴቶችን አቅም ለማሳየት ችያለሁም ባይ ናቸው።

‹‹አሁን በጋራ ምክር ቤቱ እንደ ጸሃፊ እያገለገልኩ ነው፤ ይህ ደግሞ አሁንም የኢትዮጵያ ሴቶች እጅ እንዳለበት የሚያሳይ በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነኝ›› ብለዋል።

# «በሚያልፍ ዓለም የማያልፈውን ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ትልቅነት ነው»

- ወይዘሮ ወርቅነሽ ሙንኤ
የክብረ አረጋውያን ምግባረ ሰናይ ድርጅት መስራች



ፎቶ- ፀሐይ ገጉሜ

ማህሌት አብዱል

**«ችግር ብልሃትን ይወልዳል» እንዲሉ የዘንድሮ የሴቶች ቀን አርያችን ከ15 ዓመታት በፊት በድንገት ያጋጠማቸው የልብ ህመም ዛሬ ላይ ከሁለት መቶ ለማያንሱ አረጋውያን ከመሬት አንስቶ የሚንከባከብ ትልቅ የበጎ አድራጎት ድርጅት መከፈት ምክንያት እንደሆነ ያነሳሉ። የጥንካሬ አብነት የሆኑት እኚህ ሴት ከሞት አፋፍ መንጭቆ በህይወት ያቆማቸውን ፈጣሪ ጥሪ ተቀብለው እንደ ቀልድ የጀመሯት የበጎ አድራጎት ድርጅት ጧሪ ቀባሪ አጥተው ጎዳና የወደቁ የአገር ባለውለታ አረጋውያን ከመንከባከብ ባለፈ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ረገድም ተምሳሌትነቱን በማስመስከር ላይ ይገኛል። አዲስ ዘመን ጋዜጣም የክብረ አረጋውያን መስራችና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ወርቅነሽ ሙንኤ በዚህ ስራ ውስጥ ያሳለፉት ውጣ ውረድ ለሌሎች ሴቶች መልካም ተሞክሮ ይሆናል ብሎ በማሰብ እንግዳ አድርጎ ይዞላችሁ ቀርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ወደ በጎ አድራጎት ስራ የገቡበትን አጋጣሚ በማንሳት ውይይታችንን ብንጀምር ?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** ይህንን ራዕይ የጀመርኩት ከዛሬ 10 ዓመት በፊት ነው። ራዕዩን ግን የተቀበልኩት ከእግዚአብሔር ነው። ይሁንና ራዕዩን እግዚአብሔር ሲሰጠኝ ዝም ብሎ አልሰጠኝም፤ ወይም ሽማግሌዎችን ስለምወድ ብቻ አልሰጠኝም። ከዛሬ 15 ዓመት በፊት ድንገተኛ የልብ ህመም አጋጥሞኝ ሁለት ጊዜ ሞት አፋፍ ላይ ደርሼ ነው የተመለስኩት። እዚህ አገር ለመታከም ስለማይችል ሐኪሞች ሳይቀሩ እኔ እንደማልተርፍ ደምድመው ነበር። ግን እግዚአብሔር ዕድሜ ቀጥሎልኝ ደቡብ አፍሪካ የመሄድ ዕድል አጋጠመኝና ታከምኩኝ። አራት ቀን ሆስፒታል ቆየሁና በማርፍበት ሆቴል ውስጥ የተለየ ድምፅ ሰማሁ። በነገራችን ላይ ከፈጣሪዬ ጋር ያለኝ ግንኙነት ጠንካራ ነው፤ ደግሞ ሐኪሞች ተስፋ የቆረጡበትን ህመሜን ፈውሶ ዳግም ያቆመኝ በመሆኑ ከምንም በላይ የሱን ፈቃድ ለማድረግ ነው ሁሌም የምተጋው።

በመኝታ ክፍሌ ውስጥ ሆኜ ‹‹ምድሪቷን እየረገሙ የሚሄዱ አረጋውያንን ታነሻለሽ እንጂ አትሞችም! በህይወት ትኖሪያለሽ›› የሚል ድምፅ ሰማሁ። የሚገርመው በዚያ ወቅት በዊልቸር ነበር የምንቀሳቀሰው፤ አይደለም ሌሎችን ከወደቁበት ላነሳ እኔ ራሴ በህይወት ቆይቼ መሄድ እችላለሁ ወይ? የሚለው ነገር አስግቶኝ ነበር። በነገራችን ላይ አረጋውያን የሚለውን ቃል የሰማሁት ያኔ ነው፤ ከዚያ በፊት ሽማግሌ ወይም አዛውንት የሚሉትን መጠሪያዎች ብቻ ነበር የማውቀው። እናም በመጀመሪያ ያደረኩት የቃሉን ትርጓሜ ማወቅ ነው። በተጨማሪም እኔ ብዙ እድሜዬን ውጭ በመቆየቴ እዚህ ስመጣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ባይም በዚህ ደረጃ አረጋውያን ጧሪ ቀባሪ አጥተው መንገድ ላይ ወድቀዋል የሚል መረጃም አልበረኝም።

እናም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አረጋውያን ለአገራቸው ብዙ ዋጋ ከፍለው ሳለ በመጣላቸው ምክንያት ምድሪቷን እየረገሙ ስለመሄዳቸው ማሰብ ጀመርኩኝ፤ የኢትዮጵያ አለመባረክ ምክንያት ይህ ይሆን እንዴ? የሚል ጥያቄ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩኝ። በዚህ ጉዳይ ላይ ትልልቅ የሚባሉ ሰዎችን አማካርኩኝ። ግን ደግሞ ብዙዎቼ ባለቤቴ አምባሳደር በመሆኑ ምክንያት ከመንግስት ስራ ጋር አብሮ አይሄድም የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው። ሁሉም ሰው ተቃወመኝ። ደግሞም በዚያ ጊዜ የበጎ አድራጎት ስራ ሲባል ሁሉም ሌባ ነው ስለሚባል ከባለቤቴ የፖለቲካ ስራ ጋር አብሮ ማስኬድ በጣም አስቸጋሪ ነው። በሌላ በኩል ከእኔ ቀጥተኛ ተናጋሪነትና ባህሪ አንፃር አይሄድም የሚልም ስጋት አጭረውብኝ ነበር። በዚህ ምክንያት ትንሽ ጥርጣሬ ስላደረብኝ በመጀመሪያ ቤት ለቤት እየዞርኩኝ ለመርዳት ወሰንኩኝና ጀመርኩኝ። እናም መገናኛ አካባቢ አምስት አረጋውያንን መረጥኩና ቤታቸውን ሰራንና የተለያዩ ድጋፎችን አደረኩላቸው።

በወቅቱ በዚያ ጊዜ ካየሁት ችግር አንፃር አረጋውያን ምድራቸውን እየረገሙ ነው የሚሙት የሚለውን ነገር ትክክል እንደሆነ ለማየት ችያለሁ። በየቤቱ ጓዳ ውስጥ ገብተሽ ስታይ የሚኖሩበት ሁኔታ በጣም አስቸጋሪና አሳዛኝ ነው። ለእነዚያ ሰዎች እየከፈልኩኝ ቁርስ ምሳ እራት ማብላት ቀጠልኩኝ። ወጣቶችን በማስተባበር የአረጋውያኑን ቤት ሳይቀር እናፀዳ ነበር። ይሁንና በጤናዬ ምክንያት በየሶስት ወሩ ደቡብ አፍሪካ ለክትትል እመላለስ ነበር። አንድ ጊዜ ከሄድኩበት ስመለስ እኛ የምንረዳቸው አንድ የቀድሞ ሰራዊት አባል የነበሩ ሰው የሚያያቸው ሰው አጥተው ሞተው ደረስኩኝ። በዚህ ጊዜ በጣም አዘንኩኝ፤ እናም የአምላኬን ትዕዛዝ ማሰብ ጀመርኩኝ። እግዚአብሄር ሰብሳቢ እንጂ ቤት ለቤት እየዞርሽ አግዣቸው እንዳለለኝ ስረዳ የቤት ለቤቱን ድጋፍ አቁሜ በአንድ ላይ ሰብስቤ ለማኖር ወሰንኩኝ።

ይሁንና በወቅቱ ምንም አይነት ገንዘብ ስላልነበረኝ እንዴት ብዬ እንደምጀምር አላውቅም ነበር። በተጨማሪም ሕጋዊ ለመሆን አስቀድሞ የፕሮጀክቱን ፕላን መስራት እንዳለብኝ አንዳንድ ሰዎች ነገሩኝ። ያኔ ደግሞ ፈቃድ የሚሰጠው ፍትሕ ሚኒስቴር ነበር። አጠቃላይ ፈቃድ የማግኘት ሁኔታ በጣም ፈታኝ ነበር። እነሱ እንዳሚላ የጠየቁኝ ጥያቄ ሕጉን መሰረት አድርገው ነው፤ እኔ ደግሞ ራዕይ እንጂ ምንም የሌለኝ በመሆኑ እነሱ የሚጠይቁትን መስፈርት ማሟላት አልቻልኩም። በብዙ መከራ ግን ፈቃዱን ተሰጠኝ፤ ግን ቶሎ አልጀመርኩም። ምክንያቱም ቤት መከራየት ነበረብኝ፤ አረጋውያንን ከየት እና እንዴት እንደምሰበስብ አላውቅም ነበር። ማነውስ ለእኛ የሚሰበስብልን? የተቸገሩ መሆናቸውንስ እንዴት ነው የምናውቀው? የሚሉት አሳስበውኝ ነበር።

‹‹ክብረ አረጋውያን›› የተባለ ድርጅት ከአቋቋምኩኝ በኋላ የመጀመሪያ ስራ ያደረጉት ስለአረጋውያኑ ጥናት ማድረግ ነበር። ከባለቤቴ ጋር በመሆን ያለችንን ትንሽ ብር አሰባስበን ቤት ተከራየሁ፤ ሁለት ሰራተኞችን ቀጠርኩኝ። ግን ቤቱ ምንም ዕቃ አልነበረውም፤ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ወሳኝ የሚባሉ አልጋና ሌሎች እቃዎች ማሟላት አልቻልንም ነበር። አንድ ቀን አንድ ሰው ልጄን ትምህርት ቤት ያገኘውና መልኩ ከአባቱ ጋር ስለሚመሳሰል ‹‹የአምባሳደር ተሾመ ቶጋ ልጅ ነህ?›› ብሎ ይጠይቀዋል። ልጄም መሆኑን አረጋገጠለትና ስልክ ቁጥሬን ወስዶ ደወለልኝ። መቼም እግዚአብሔር አመጣጡና መንገዱ አይታወቅም። በዚያ ሰው አማካኝነት ሌሎች ሰዎች ተዋወኩኝና ስለጀመርኩት ስራ አጫወትኳቸው፤ የሚገርመው ግን ልመና እንኳን አልችልበትም ነበር።

እነዚያ ሰዎች ድርጅቴን ሊጎበኙ ሲመጡ ባዶ ቤት ሆነው ሲያዩት የሚያስፈልገውን ጠየቁኝ። እኔም ፈጠን ብዬ አልጋ፤ ፍራሽ፤ አንሶላ፤ ብርድልብስ እንደሚያስፈልግ ነገርኳቸው። የተወሰነው ሰው አልጋልብስ፤ ሌላው ብርድልብስና አንሶላ አመጣለሁ ብሎ ቃል ገቡልኝ። ከዚያ 20 አልጋ እንደሚገዙልኝ ነገሩኝ። የሚገርምሽ ያንጊዜ 250 ብር የተገዛው አልጋ አሁንም ድረስ ነው እየተጠቀምንበት ያለው። ቃል በገቡት መሰረት 20 አልጋ፤ ፍራሽ ገዙልኝ፤ አንሶላና በረድ ልብሱንም አመጡልኝ። በዚያ መነሻ አድርገን አንዲት አረጋዊት ተቀብለን መንከባከብን ጀምረን፤ ከዚያ በኋላ ቁጥራቸው እያደገ መጣ።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ማህረሰብ አቀፍ ስራም እንሰራ ነበር፤ በተለይም አቅም የሌላቸውን ሴቶችን ወፍጮ ቤት፤ ሻወርና መፀዳጃ ቤት ገንብተን አከራይተው እንዲጠቀሙ አድርገናል። አሁን ድረስ በብዙ በመልሶ ግንባታ ፈረሰባቸው እንጂ በወቅቱ ቤቶቻቸው በጣም ያረጁ ሴት አረጋውያንን ቤት አፍርሰን ገንብተናል። እነዚያ ሰዎች ስናገኛቸው አይደለም ሰው እንስሳ እንኳን ይኖርበታል ተብሎ የማይጠበቅ ነበር፤ ሰው በሕይወት እያለ በተኛበት ትልና ነፍሳት ሲበላው ያየሁት ያኔ ነው። እኔ ራሱ እነሱን ስረዳ የዚያ እጣ ፈንታ ተካፋይ የሆንኩባቸው ገጠመኞች ብዙ ናቸው። ጉንዳን ይዞኝ መንገድ ላይ ልብሴን አውልቄ ያራገፍኩበት ቀንም አለ። ከዚያ በኋላ ነው ሰዎች መክረውኝ ተባይ የማይዝ ቆዳ ልብስና ቦት ጫማ እየለበስኩኝ አረጋውያኑን ማንሳት የጀመርኩት።

**አዲስ ዘመን፡- አረጋውያኑን በምን መስፈርት ነው የምትመርጧቸው?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** በአብዛኛው የሚመርጡልና በትክክል ችግረኛ መሆናቸውን ለይተው የሚሰጡን የከተማዋ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሰዎች ናቸው። ይሁንና እኛም ብንሆን ስራውን የጀመርነው እነዚህ አረጋውያን አዲስ አበባ መጥተው ጎዳና ላይ የወደቁበትን ምክንያት በማጥናት ነው። ብዙዎች ልጆቻው በጦርነትና በተለያየ መንገድ ሞተውባቸው ረዳት አጥተው ጎዳና የወጡ ናቸው። አንዳንዱ ደግሞ በሱስ ምክንያት እንደሆነ ተረዳን። ሌሎች ደግሞ በተፈጥሮ መውለድ ባለመቻላቸው ጧሪ ቀባሪ አጥተው ለጎዳና ህይወት መዳረጋቸውን በጥናታችን ለይተናል። አንዳንዱ ግን ለጠበል መጥተው ‹‹የአዲስ አበባ ህዝብ ደግ ነው›› በሚል ልመና ውስጥ የገቡም አሉ። በዚያ መሰረት ነው እነዚህን አረጋውያን መሰብሰብ የጀመርነው።

አረጋውያኑን ሰብስቤ ምደግፍበት ቤት የአንድ የሐይማኖት ቤት አይደለም። እኔ የፕሮቴስታንት ክርስቲያን እምነት ተከታይ ብሆንም በአብዛኛው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ያሉበት እዲሁም ጥቂት ሙስሊም አረጋውያን የሚኖሩበት የሁሉም ቤት ነው። የኦርቶዶክስ ተከታይ የሆኑ መመልኮስ ሲፈልኩ አስፈላጊውን ድጋፍ አደርግላቸዋል፤ ለሙስሊሞቹም በፆም ጊዜ ቤታቸው የሚደረግላቸውን ሁሉ እንክብካቤ አደርጋለሁ፤ ሌላው ይቅርና የሙስሊም አልባሳትን መስኪድ ድረስ ሄጄ ለምኜ አመጣላቸዋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በጎ አድራጊነት ስነልቦና ከየት ነው ያዳበሩት መነሻውስ ምንድን ነው?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** በመሰረቱ ያደኩበት ቤተሰብም ሆነ የአካባቢው ማህበረሰብ በቸርነትና ለሰዎች በጎ በማድረግ የሚያምን ነበር። በተለይ አባቴ የራሱ ፋርማሲ ያለው በአካባቢው የታወቀ ሐኪም ነበርና ሰዎችን ይረዳ ሲረዳ ነው የኖረው። እኔን ፋርማሲ እንድጠብቅ ሲያደርገኝ ለመጣሁ ሁሉ መድሐኒት በነፃ መስጠት ያስደስተኝ ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን ሰዎች ተርበው ስመለከት የራሴን ምግብና ውሃ ሳይቀር እሰጥ ነበር። አሁንም ድረስ ሰዎችን መርዳት፤ ያለኝን ሁሉ ማካፋል እጅግ ያስደስተኛል። ካገባሁ በኋላም ከባለቤቴ ጋር ለስራ በምንዞርባቸው አገራት ሳይቀር ለተቸገሩ ሰዎች እንረዳ ነበር። ለምሳሌ ኬኒያ በነበርንበት ወቅት በመጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ ስደተኛ ኢትዮጵያውያንን እንደግፍ ነበር፤ እርግጥ ደመወዛችን ብዙ የሚያወላዳን ባይሆንም እቤት ያለውን ትርፍ ምግብም ቢሆን መጥተው እንዲወስዱ እናደርግ ነበር። እኔ ቤት ምግብ ኖሮ ሰዎች ተርበው ማየት አልፈልግም።

አሁንም ቢሆን አብሮ መብላትና መካፈል የእኔ የህይወት መርህ ነው። የተከፋ፣ የተቸገረና በህይወት ተስፋ የቆረጠ ሰው በእኔ ትንሽ እርዳታ ቀና ማለትና ዳግም ተስፋ ሲያደርግ ማየትን የመሰለ ሌላ የሚያስደስተኝ ነገር የለም። በመሰረቱ ይሄ ደስታ አንድም የፈጣሪን ትዕዛዝ መፈፀም ነው፤ ምክንያቱም ቃሉ እንደሚለው ለድሀ የሚሰጥ ለእግዚአብሄር ያበድራልና ነው። ደግሞም በዓለም ላይ ሁሉ ነገር ያልፋል፤ ውበት ይረግፋል፤ ሃብት ንብረት ይጠፋል፤ ቁም ነገር ሰርቶ ማለፍ ነገር ትልቅ መታደል ነው። ስለዚህ ለሚያልፍ ዓለም የማያልፈውን ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ትልቅነት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ስራ እጅግ ፈታኝና የማይረሱትን ገጠመኝ ያጫውቱን?**

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

## ልዩ ዕትም

# “እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”



**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** ዱቄት አልቀብን የቤቴን ሁሉ እስከ ማምጣትና ቤተሰቤን ሳይቀር ችግር ላይ እስከመጣል የደረስኩበትን አጋጣሚ መቼም አረሳውም። አንድ ወቅት ላይ 20 አረጋውያን ስንረዳ በነበረበት ጊዜ እንጀራ ጋጋሪዋ ጠርታኝ ስምንት እንጀራ ብቻ መኖሩንና ለእነዚያ ሁሉ ሰዎች እንዴት እንደምትመግባቸው ግራ መጋባቷን ነገረችኝ። እኔ ግን የመለስኩላት መልስ«እግዚአብሄር የመስዋቱን በግ ያዘጋጃል» የሚል ምላሽ ብቻ ነበር። ግን ለእሷ እንዲህ ብልም ሰዓቱ እየገፋ ሲሄድ በውስጤ መጨነቄን አላቆምኩም ነበር። ከፈጣሪዬም ጋር ሙግት ውስጥ ገብቼ ነበር። ሕክምናም ያስፈልጋቸው ነበር። በባንክ አካውንቴ ላይ የነበረው ደግሞ 1ሺ 250 ብር ብቻ ነበር። ያ ደግሞ ምንም ሊያደርግ አይችልም ነበር። ምክንያቱም ለአንድ ሰራተኛ ሶስት ሺ ብር ነው የሚከፈለው፤ የቤት ኪራይ 6ሺ 500 ብር መክፈል ይጠበቅብኝ ነበር። ሁሉም ችግር የእኔን ምላሽ ይጠብቅ ነበር፤ ግን ደግሞ ምንም አልነበረኝም ነበር።

አስቀድሜ እንዳልኩሽ እግዚአብሄር መምጫው ሁሉ የተለየ ነው። አንድ ኬኒያ የምናውቀው ሰው በአጋጣሚ ይደውላል። መታመሜን ሰምቶ ስለነበር ካላየሁሽ አለኝ። በዚህ ጊዜ ይሄ ሰውዬ ከመጣ የሆነ ነገር ሊያደርግልኝ ነው ብዬ አሰብኩኝ። ሰውየው እንዳለሁ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ ድርጅቱ ድረስ መጣና አረጋውያኑን ጎበኘ፤ ስለስራዬ ሁኔታ እየተወያየን እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ቆየን። በጣም የሚገርምሽ ይህ ሰው እጁን ወደ ኪሱ በከተተ ቁጥር የሆነ ነገር የሚሰጠኝ እየመሰለኝ አይኔ ከእጁ ላይ መነሳት አቅቶት ነበር። ጊዜው እየመሸ ሲሄድ ሰውየው ዝም ሲለኝ ተናድጄና ተስፋ ቆርጬ በቀልድ ዝም ብሎ በወሬ ከሚያደርቀኝ መኪና ስለያዘ ቤቴ እንዲያደርሰኝ ጠየኩት።

ሰውየው ቤቴ አድርሶኝ እንደተመለሰ በጣም ከፍቶኝ ስለነበር ምርር ብዬ አለቀስኩኝ። እምባ የእሳት ያህል እንደሚፋጅ ያየሁት ያኔ ነው። እነዚህን ሰዎች ምን ላበላቸው ነው? የሚለው ነገር እጅግ አስጨነቀኝ። ልጆቼ በሁኔታዬ ተደናግጠው አሚታል ብለው ለአባታቸው ደወሉለት፤ በወቅቱ ደግሞ ባለቤቴ አጣዳፊ ስራ ስለነበረው ለሌላ ሰው ነገሮ ሐኪም ቤት ሊወስደኝ መጣ፤ የተላከው ሰው ተጣድፎ ሲመጣ እኔ የተለመደውን ስራ ማዕድ ቤት ገብቼ እየሰራሁኝ ነው። ሰላም መሆኔን ነገርኩት። ሌሊት ተነስቼ ግን በአምላኬ ፊት ተንበርክኬ መጮህ ጀመርኩኝ፤ እነዚህን ሰዎች እንድሰበስብ የነገረኝ ራሱ ሆኖ እንዴት እንደዚህ ያደርገኛል? ብዬ ከፈጣሪዬ ጋር ሙግት ያዝኩኝ። እነዚህ ሰዎች ለመደገፍ ዕድሜ ቢቀጥልልኝም፤ እነሱን እንደሚገባ ማኖር ካልቻልኩኝ የእኔንም ህይወት እንዲወስደው ተማጸንኩት። ምክንያቱም ደግሞ የነበረው ሁኔታ እጅግ ተስፋ አስቆርጦኝ ነበር። «ጀምራ ተወች» የሚባለውም ነገር አሳስቦኝ ስለነበር በሌሊት እያለቀስኩኝ ከፈጣሪ ጋር ተከራከርኩኝ።

በማግስቱ ጠዋት ያው ሰውዬ ሲደውልልኝ ብዙ ሬስቶራንቶች ስላሉት ትርፍራፊ እንጀራ ሊሰጠኝ እንደሆነ አሰብኩኝ። ያም ቢሆን ከችግሩ አሳሳቢነት የተነሳ ለመቀበል ወሰንኩኝ። ጠዋት ቢሮ ስገባ ላንድሮቨር ፒካፕ መኪና ተከትሎኝ መጣ፤ ወጥቼ ስመለከት በመኪናው ሙሉ የተጫነ እህል የያዘ መኪና ነው። ልክ ያንን ሳይ ማንም ይላከው ማን ብቻ ፈጣሪ ጥያቄዬን ሳይዘገይ ስለመለሰልኝ በደስታ ብዛት ዘለልኩኝ። ጎበዝ ዘላይ መሆኔን ያወቅሁት የዚያን ቀን ነው። በኋላ አንዷት ሴት ከመኪናው ወረዱና የማታው ሰው እንደላካቸው ነገሩኝ። እኔ ትርፍራፊ ስጠብቅ እግዚአብሔር ግን አስር ኩንታል ጤፍና ሶስት ኩንታል የስንዴ ዱቄት ነው የተሰጠኝ። የሚገርመው ያንን ያህል እህል የማስቀምጥበት እቃም ሆነ ቦታ እንኳን አልነበረኝም። ሴትየዋን ችግሬን ነገርኳቸውና እሳቸው ጋር ተቀምጦ እኔ በየወሩ እንዳመጣ ተስማማን። በዚህ ብቻ አላበቃም ሴትየዋ ባዩት ነገር እጅግ በመደሰታቸው ምክንያት ሶስት ተጨማሪ ኩንታል ጤፍ፤ ፍሪጅ፤ አልጋ፤ ክራንች፤ የማዕድ ቤት ዕቃዎችና የህክምና መሳሪያዎች በሙሉ ሰጡኝ። ጤፉ የጠፋው ለካ ብዙ ሊያመጣ ነው ብዬ አሰብኩኝ።

**አዲስ ዘመን፡-ድርጅቱ ያለበትን ቦታ ያገኙበት አጋጣሚ ለየት እንደሚል ሰምቻለሁ፤ እስቲ ስለዚህ ሁኔታ ይንገሩን?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** ይህንን ቦታ የሰጠኝ መንግስት ነው፤ ከዚያ በፊት ግን በኪራይ ቤት በጣም ብዙ ዋጋ ከፍለናል። በቤት ኪራይ ብዙ ተጎላልተናል፤ ያም ቢሆን ግን አንድም ቀን ጊዜ አሳልፌ ከፍዬ አላውቅም። አንድ ወቅት ላይ ቀኑ እስከሚደርስ ድረስ ምንም አይነት ገንዘብ አልነበረንም። ደግሞ የስድስት ወር በአንዴ 35 ሺ ብር ስለሚከፈል ገንዘብ ማጣቴና የቀኑ መድረስ እጅግ አስጨንቆኝ ነበር። በአጋጣሚ ልጄን ከትምህርት ቤት ላመጣ ስሄድ አንድ ሰው ደወለልኝ እንደሚፈልገኝና እዛው ቆሜ እንድጠብቀው ነገረኝ። ሰውየው ምንም ሳልነግረው በቃ ውስጤ አሳስቦኝ ነው ብሎ በካኪ ፖስታ የታሸገ 30 ሺ ብር ሰጠኝ። በዚህ አይነት የእግዚአብሔር ምህረትና ቸርነት በዝቶልን ቀን ከሌሊት የሱን ክንድ እያየን እስካሁን አለን።

ወደ ጥያቄሽ ስመለስ አዲስ አበባ ሰራተኛና ማህበራ ጉዳይ ጋር ስንፈራረም በፕሮጀክቱ ከተቀረፀው ሶስት ሚሊዮን ብር ውስጥ 10 በመቶ የሚሆን ገንዘብ አካውንት ላይ መኖር አለበት የሚል ነገር ነገሩኝ። እኔ ግን አካውንት ከከፈትኩበት 50 ብር ውጪ ምንም አልነበረኝም። ያለብኝን ችግር ለኃላፊው አጫወትኳቸው፤ ይሁንና የተቀመጠ ሕግ በመሆኑ እሳቸው ምንም ሊያደርጉልኝ አልቻሉም። አዝኜ ከቢሯቸው ስወጣ አንዷት የተቋሙ ሰራተኛ ምን እንደሆንኩኝ ጠየቀችኝና ሁኔታውን አጫወትኳት፤ ከዚያ ከንቲባ ጽህፈት ቤት እንድሄድ መከረችኝ። አሁን ላይ ሳስበው ይህችን ሴት እግዚአብሔር የላከልኝ መልዕክተኛ እንደሆነች ነው የምረዳው።

ሴትየዋ እንዳለችኝ በዚያው በኩል ሄድኩኝና ከሰዓት በኋላ ፀሐፊዋ ለ15 ቀን ቀጠሮ እንደተሰጠኝ ነገረችኝ። በዚያ ቀጠሮ መሰረት ከቦርድ አባላት ጋር በመሆን ከንቲባው ቢሮ ሄድኩኝ፤ በአጋጣሚ ሆኖ እኛ የከለከሉኝ የማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ እዛው አገኘኋቸው። ከንቲባው ኃላፊውንና እኛን አብረን እንድንገባ አደረጉ። ወቅቱ ደግሞ የአዲስ አበባ ባላደራ ቦርድ አማካኝነት የተሾሙት ከንቲባ ብርሃኑ ደሬሳ ጉዳዮን ከመሰረቱ ጀምሮ ሳጫውታቸው አይናቸውን ለሰከንድ ሳይነቅሉ በተመስጦ ነው ያዳመጡኝ። አሁን ያለብኝን ችግር ሲጠይቁኝ ወደ ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊው ሰውዬ እያመለከትኩኝ ችግሬ እሳቸው ናቸው ብዬ በድፍረት ተናገርኩኝ። እሳቸውም ቢሆኑ ሕግና ደንብ ማክበር ስለሚገባቸው እንጂ ለክፋት ነው ብዬ እንደማላምን አከልኩበት። ግን ደግሞ አረጋውያን ምድራችን ባርከው እንዲሄዱ ከተፈለገ ለአሰራር ማነቆ የሆኑ እነዚህ ህጎች እንዲስተካከሉልኝ ጠየኳቸው። እሳቸው ሁኔታዬን በሚገባ ተረድተው ስለነበር እያመመኝ ለአረጋውያንን ያለኝን ጉልበትና አቅም ሁሉ ሳልሰስት መስጠቴ በራሱ እንደገንዘብ ተለውጦ በአስቸኳይ ችግሩ እንዲፈታልኝ ማስጠንቀቂያ ሰጡልኝ።

በዚህ ብቻ ሳይወሰን ቤት እንዳሌለኝ ስነግራቸው አዲስ አበባ ውስጥ የቀበሌ ቤት ካለ ፈልገሽ ጠቁሚኝ አሉኝ። በደላላ አማካኝነት እየዞርኩኝ የቀበሌ ቤት ባይኖርም ለመኖር አስቸጋሪ ሆነብኝ። በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለው ቤቱ ካልሆነልሽ ቦታ ትፈልጊያለሽ? ብለው ጠየቁኝና ሶስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሲኤምሲ አካባቢ 10 ሺ ካሬ የሚሆን መሬት ተሰጥቶኝ ውል ፈረምኩኝ። የሚገርመው ከአራት ቀን በኋላ የባላደራው አስተዳደር ቀርቶ ሌላ ከንቲባ መጣ። ያንን ተከትሎ የተሰጠ መሬት እንዲሁም መስጠት እንዲታገድ ተደረገ። ትንሽ ቆይቶ ወደ መሬት ባንክ እንደሚገባ ሰማን። እኛ ግን ይህንን ሁሉ ከመስማታችን በፊት የህንፃ ፕላን አሰርተንና መስሪያ ገንዘብ ፈጣሪ እንዲሰጠኝ እየጸለይን ነበር። በኋላ ግን አዋጁ ሲታወጅ ባንክ የገባ መሬት ማንም አያወጣውም ብለን ሁሉንም እርግፍ አድርገን ተውነው።

አንድ ወቅት ላይ ፈረንሳይ አገር ሔጄ እንደተመለስኩ ውስጤ ማዘጋጃ ቤት እንድሄድ ተሞላና ቀጥብዬ መሬት አስተዳደር ሄድኩኝ፤ ግን ለምን እንደምሄድ ምንም አላውቅም ነበር። ዝም ብዬ ወደፎቁ እየወጣሁኝ ሳለ አንድ ከረጅም ጊዜ በፊት የማውቀው ሰው አገኘሁና ዝም ብዬ ጉዳዬን አጫወትኩት። ይህንን ሲሰማ ተመልሶ አብሮኝ ኃላፊው ቢሮ ገባንና በአዲስ መልክ ስለድርጅታችንና ለዚህም ስራ በቀድሞው ከንቲባ ተሰጥቶኝ ስለነበረው መሬት ሁኔታ ለኃላፊው አስረዳሁት። ኃላፊው በጣም መልካም ሰው ስለነበር በትዕግስት አዳመጠኝ። የረጅም ጊዜ ጥያቄ ለነበረው ለአንድ አረጋውያን ድርጅት መሬት መስጠቱን ግን ደግሞ የትኛው ድርጅት እንደሆነ በውል እንደማያውቅ፤ አጣርቶ እንደሚነግረን እየተናገረ ሳለ የሚመለከተው ሰው በአጋጣሚ ስለዚያው ጉዳይ ከኃላፊው ጋር ለመወያየት ነበር የመጣው። እሱም ያንኑ ነገር አረጋገጠልንና መሬት የተሰጠው ድርጅት ማንነት ለማጣራት መዝገብ ቤት ሄድኩኝ። የመዝገብ ቤቱ ሰራኞች ለካ በቴሌቪዥን ያውቁኝ ኖሮ ገና ሲያዩኝ መሬቱ የተወሰነው ለእኔ ድርጅት መሆኑን አበሰሩኝ። እናም በዚያ መሰረት ነው አሁን ቦሌ ቡልቡላ ያለውን ይህንን መሬት ያገኘሁት። በተጨማሪም የእኔን ስራ በቴሌቪዥን ያዩ ሴት ቤታቸውን ሸጠው ገንዘቡን ለእኛ ሰጡን፤ ከሌሎችም ሰዎች ገንዘብ ፈልገን አሁን በምታይው ቦታ ላይ በርካታ መኝታ ክፍሎችና ቢሮዎችን ሰራን። በዚያ አልተወሰንም ከአራት ዓመት ወዲህ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት የሚሰጥ ህንፃ መገንባት ጀምረን በገንዘብ እጥረት ማጠናቀቅ ሳንችል ቀርተናል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ድርጅት ምንያህል ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል? ለስንት ሰዎችስ ነው የስራ እድል የተፈጠረው?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** ድርጅታችን አስቀድሜ እንዳነሳሁልሽ ወፍጮ ቤት፤ ዳቦ ቤት፤ መፀዳጃ ቤትና ሻወር ከፍቶ ለአንድ ሺ 500 እናቶችና አባቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። በድርጅታችን ውስጥ ተቀጥረው በቋሚነት የሚሰሩት 15 ናቸው። በሌላ በኩል እዚህ በድርጅታችን ውስጥ ያሉትንም አረጋውያን ዘንቢል፤ ሽመና እንዲሁም ባልትና እየሰሩ ራሳቸውን የሚደጉሙበት ሁኔታ ፈጥረን ነበር። ሆኖም ኮቪድ ከተከሰተ በኋላ ስራው ቆሟል። ምክንያቱም አረጋውያኑ ተይዘውብን ስለነበር፤ ከስራው በላይ አደጋው የከፋ በመሆኑ ነው በውስጥ የምንሰራውን ስራ ያቆምነው። ከዚሁ ጎን ለጎን ግን የጓሮ አትክልት እየተከልን ራሳችንን ምንመግብበት ስርዓት ዘርግተናል፤ ሆኖም በአካባቢው ከፍተኛ የውሀ እጥረት በመኖሩ የምንፈልገውን ያህል ማስፋት አልቻልንም። ከዚህ ችግር የተነሳ የራሳችንን የውሃ ጉድጓድ ለማስቆፈር በዝግጅት ላይ ነን ያለነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ስራ ስትጀምሩ ብዙ ሰዎችና ሁኔታዎቹ ተስፋ ቢያስቆርጥም፤ ራዕዮን ተስፋ ሳይቆርጡ ለስኬት በቅተዋል፤ ለመሆኑ እንደርእርሶ ራዕይና ህልም ኖሯቸው ግን በሁኔታዎች ተስፋ ቆርጠው ለተቀመጡ ሴቶች ምን ይመክራሉ?**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** በነገራችን ላይ ባለቤቴን ጨምሮ አንዳንድ ሰዎች መጀመሪያ ላይ ከነበረኝ ጤና አንፃር ስጋት አድሮባቸው እንጂ እኔን ተስፋ ለማስቆረጥ ብለው አይደለም። ልብ ደግሞ የሰውነታችን ሞተር ነው፤ ድንገት ልብ ከታመመ ህይወት ሙሉ ለሙሉ ሊቋረጥበት የሚችልበት እድል ሰፊ ነው። እናም እኔ የምረዳው ከዚያ አንፃር ለእኔ ከመሳሳት እንደሆነ ነው። በመሰረቱ ባለቤቴ ለዚህ ስራ እዚህ መድረስ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። የሚገርምሽ ይህንን ስራ ከጀመርን ጀምሮ በዓል ቤታችን አክብረን አናውቅም፤ ያለንን ይዘን አብሮኝ ከአረጋውያኑ ጋር ነው የሚያከብረው። እሱ ለፍቶ የሚያገኛትን ገንዘብ ሳይቀር ሳይሰስት ነው ለድርጅት የሚሰጠኝ። እኔ እዚህ ቀን ከሌሊት ስዳክር ልጆቼን ተንከባክቦ ያሳደገው እሱ ብቻውን ነው። አንድ ቀን ገንዘብ አውጥተን ውጪ ሻይ ቡና ብለን አናውቅም፤ በጋራ ተጋግዘን ቤታችን ውስጥ ነው የምንዝናናው።

በአጠቃላይ የባለቤቴን ውለታም ሆነ መረዳት እንዲሁ በቀላሉ የምገልፀው አይደለም፤ በጥቅሉ ፈጣሪ ይክፈለው ነው ማለት የምችለው። በዚህ አጋጣሚ ግን በጣም እንደምወደው ልገልፅለት እፈልጋለሁ። ሌሎቹም ሰዎች ቢሆኑ ከእኔ ባህሪ አኳያ አይሆንላትም ብለው በቀናነት ከማሰብ ይመስለኛል። ምክንያቱም ደግሞ እኔ ፊት ለፊት የማምንበትን የምናገርና የማደርግ በመሆኔ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብታ መስራት ይከብዳል በሚል ስጋት እንጂ በክፋት አልነበረም።

እንደ እኔ ራዕይ ይዘው በስጋት ለተቀመጡ ሴቶች ግን ከእኔ ሁኔታ በመነሳት ልመክራቸው የምፈልገው ነገር አንድን ነገር ለመስራት ካሰቡ የማንም አፍራሽ ሀሳብ መስማት እንደሌለባቸው ነው። የቱንም ያህል ሁኔታዎች ተስፋ የሚያስቆርጡ ቢሆኑም ወድቆ መነሳት እንዳለ ተገንዝበው ወደፊት እንጂ ወደኋላ ማለት የለባቸውም። በመጀመሪያ ደረጃ ተስፋ የሚሰጥ እግዚአብሔር የታመነ መሆኑን ማመን አለባቸው። እንዲህ አይነት ስራ ደግሞ በዋናነት የሚፈልገው ንፁህ ልብና ቁርጠኝነት ነው። ገንዘብ ብቻውን የሚሰራ ነገር የለም። «እችላለሁ!» የሚል ልብ ካለ ሁሉንም ማሳካት ይቻላል። ይህንን ስል ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ነው ማለቴ አይደለም፤ የሚያጋጥማቸውን ፈተና ለማለፍ ዝግጁ መሆን አለባቸው። እንደተባለው ሴቶች ብዙ እውቀትና አቅም ቢኖራቸውም ካደጉበት ማህበረሰብ አስተሳሰብ አኳያ ራሳቸውን እንደደካማ ይቆጥራሉ። ግን ይህ እውነት አይደለም ሁላችንም የተሰጠኝ እምቅ አቅምና እውቀት አለን፤ ልዩነታችን አቅማችን ለመጠቀም በቆራጥነት መወሰናችን ላይ ነው። እኔ ይህንን አስተሳሰብ ፈፅሞ አልቀበለውም፤ በየቀኑ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ተነስቼ ለቤተሰቤ የሚያስፈልገውን ሁሉ ብቻዬን ሰርቼ፤ ልጆቼን አብልቼ ትምህርት ቤት አድርሼ ደግሞ ቢሮዬ በሰዓቴ ደርሼ አረጋውያኑን አጥቤ፤ ቁርስ አብልቼ ሌሎች የሚሰሩ ስራችን ሁሉ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከውኜ ለስኬት በቅቻለሁ። ሌላዋም ሴት እንዲሁ ብቃቷን ማስመስከር ትችላለች ብዬ ነው የማምነው። ስለዚህ ራሳቸውን ማሳነስ የለባቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ስላካፈሉን ተሞክሮ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ወይዘሮ ወርቅነሽ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ልዩ ዕትም

# ልመናን የተጠየፉ፣ ሥራን ያከበሩ እጆች

መልካምሥራ አፈወርቅ

አዲስ አበባ እንደ ‹ሊቃ ዱለቻ›› አልሆነላትም። ኑሮ ከብዷታል፣ ህይወት ፈትኗታል። ታደርገው፣ ብታጣ አንገቷን ደፍታ ማልቀስ ይዛለች። እየጨነቃት ነው። ዘወትር ሀዘን ከቁጭት፣ ሲያስተክዛት ይውላል። አቀርቅራ ታስባለች፣ በየሰበቡ ሆድ ይብሳታል። ቤተሰቦቿ በዓይኗ ውል ሲሉ ናፍቆቱን አትችልም። ትዝታው ያንገላታታል። ፈጥና ወደቀዬዋ አትመለስ፣ ካገሯ ወለጋ ርቃ መጥታለች። ሁሌም በዕንባዋ ጭጋግ ‹‹ሊቃ ዱለቻ›› ትውስ ይላታል።

‹‹ሊቃ ዱለቻ›› ተወልዳ ያደገችበት መንደር ነው። አካባቢው ክረምት ከበጋ ያመርታል። የገጠሯ ጉብል ሌሊሴ ቀጀላ ወላጆቿ አራሽ ገበሬዎች ናቸው። ዕድሜዋ ከፍ ሲል ከግብርናው ንግድን መረጠች። ለእሷ ሥራውን መልመዱ፣ መሸጥ መግዛቱ አልከበዳትም።

ሌሊሴ የቤተሰቦቿን ኑሮ ታውቃለች። ችግረኞች ናቸው። ልጅ ብትሆንም በእሷ ሰበብ ህይወታቸው ቢቀየር፣ ኑራቸው ቢለወጥ ትወዳለች። ይህ ህልሟ በየቀኑ ከተማ አውሎ ይመልሳታል።

ሌሊሴ በሥራዋ ከቤተሰብ መራቋ ለገንዘብ ብቻ አልሆነም። ድንገት ከአንድ ሰው በፍቅር ወደቀች። ስሜቱን ወደደችው። አፍላነቷ እሱን፣ እሱን ብቻ ይላት ያዘ። እንዲህ መሆኑን አልጠላችም። አጋጣሚው ልቧን ክፉኛ ቢያሸፍት ሌላውን መንገድ አሰበች። ከምትወደው ሰው መራቅ፣ መለየት አልፈለገችም። ይህ ሰው ደግሞ ከአካባቢው ሊሄድ እግሩ ተነስቷል፣ ጓዙን ሸክፏል።

ሌሊሴ ይህን ስታውቅ አብራው ልትሄድ ወሰነች። ፍቅረኛዋ ሀሳቧን አልተጋፋም። ወጣቷ ‹‹ቤተሰቤን›› አላለችም። ፈጥና የእጇን ጣለች፣ ንግዷን ተወች ‹‹ ሊቃ ዱለቻ››ን ርቃ ወላጆቿን ትታ ስትወጣ ደስ እያላት ሆነ።

### አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ለሌሊሴ አዲስ ዓለም ነው። ከዚህ ቀድሞ አታውቀውም። ትጠጋበት፣ ታርፍበት ዘመድ የለም። አሁን ባለቤቷ ከጎኗ ነው። እንዲያም ሆኖ የተመቻት አይመስልም። ለጊዜው ከእሱ ወንድም በቀር ተቀባይ ዘመድ አላገኙም።

ውሎ አድሮ ባልና ሚስት ራሳቸውን ቻሉ። አዲስ አበባ እንደአገራቸው አልሆነም። ኑሮ ይከብዳል፤ የቤት ኪራይ፣ የዕለት ወጪው አይገፋም። እሱ ውሎውን በጉልበት ሥራ መግፋት ያዘ። ህይወት እንዳሰቡት አልሆነም። በእሱ ትከሻ ብቻ ጎዶሎው አልሞላም፣ ሀሳብ አልተሳካም። ጥብ፣ ጭንቅ ሆነ።

ባለቤቷ እንደ ትናንቱ ፈገግታ የለውም። በየሰበቡ ይናደዳል፣ ይበሳጫል፣ ሌሊሴ ሁኔታው እያሳሰባት ውስጧን ታዳምጣለች። ጤና ይሉት የላትም። ደርሶ የሚረብሻት ስሜት እየደጋገማት ነው። እውነቱ አልጠፋትም። መፀነሷን አውቃለች። ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› እንዲሉ እርግዝናዋ ዕንቅልፍ ነስቷታል።

የእሷ ማርገዝ ለባሏ ጫና ሆኖ መነጫነጩ ቀጥሏል። መሀላቸው ሰላም ጠፍቷል፣ ፍቅር ርቋል። ሌሊሴ እየከፋት ነው። በቸገራት ጊዜ ክፉኛ ታዝናለች፣ ትተክዛለች። ኑሮ እንደትናንቱ ቀጥሏል። ህይወት አልተቀየረም፣ ችግር አልራቀም።

### አዲስ እንግዳ

ሌሊሴና ባሏ ህይወትን በአንድ ጎጆ እየመሩ ነው። ኑሮ ባይደላም፣ ቤት ባይሟላም እንደነገሩ ጊዜያት ተቆጥረዋል። አሁን ደግሞ በቤታቸው አዲስ እንግዳ ተቀብለዋል። የምታምር ትንሽ ህጻን ከህይወታቸው ገብታለች። ከሁለት ሶስት የሆኑት ጥንዶች ስጦታቸውን በደስታ ተቀብለዋል።

ሌሊሴ የልጅ እናት ከሆነች ወዲህ ኑሮ ይበልጥ አሳስቧታል። ከዚህ በኋላ የእሷን ጨምሮ ለህፃኗ ብዙ ያስፈልጋል። ዛሬም ኑሮ አልተለወጠም፣ አሁንም ባሏን ለማገዝ፣ ሸክሙን ለማቅለል አቅሟ አልበረታም። ይህ እውነት የጥንዶቹን ሰላም ይሸረሽር ይዟል።

አሁን ትንሸዋ ልጅ ‹‹ድክ ድክ ›› ማለት ጀምራለች። የምታምር፣ ለዓይን የምታጓጓ ቆንጆ ነች። ‹‹ሴና›› በድህነት ጎጆ የተገኘች የጥንዶቹ ፍሬ የዓይን ማረፊያ ናት። ያያትን ሁሉ ትቀርባለች፣ የቀረባትን ትወዳለች። አላፊ አግዳሚው ሴናን አይቶ አያልፍም። እየሳመ ያጫውታታል፣ እያጫወተ ይስማታል።



ሌሊሴ ቀጀላ፤

ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

ሴና የአንድ ዓመት ልደቷን እንዳከበረች በቤቱ አዲስ ነገር ሆነ። አባወራው ለሥራ እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። ሌሊሴ ባሏ ትቷት መሄዱን ስታውቅ ሰማይ የተደፋባት ያህል ከበዳት። የእሷንና የልጇን ዕጣ ፋንታ እያሰበች በትካዜ ቆዘመች። ብቸኝነት፣ ከባይተዋርነት ተዳምሮ ሆድ ያስብስ፣ ያስለቅሳት ጀመር።

ሌሊሴ ችግሮቿ በረከቱ። አፍ የፈታችበት የኦሮምኛ ቋንቋ የልቧን በወጉ እንዳትናገር ምክንያት ሆነ። ለጠየቋት ሁሉ ምላሸዋ በዝምታ ተዋጠ። ትንሸዋን ሴና ይዛ በዕንባ ከመታጠብ ሌላ ምርጫ አልነበራትም። አሁን ለልጇና ለእሷ ቀለብ፣ ለቤቷም የወር ኪራይ ያስፈልጋል። በእጅጉ ጨነቃት። ‹‹የኔ›› ትለው ወዳጅ ዘመድ ቅርቧ የለም።

ሌሊሴ ቁርጠኛው የችግር ቀን መድረሱን አወቀች። ከሁሉም ህጻኗ በርሀብ ልትቀጣ ነው። የወደፊቱ ክፉ ችግር እየታያት ተብሰለሰለች። የሰው እጅ ለማየት ልምድና ድፍረት ይጠይቃል። ‹‹ቸገረኝ›› ብሎ ለመጠየቅ ብልሀት ያስፈልጋል። ሌሊሴ ይህን ለመሞከር ወኔ ከእሷ ርቋል።

ቆም ብላ ማሰብ፣ ማብሰልሰል ያዘች። አዎ! ‹‹ከመሞት መሰንበት›› ይሻላል። የአዲስ አበባ ሰው እንኳን ልጅ ለያዘች ለሌላውም አይሰስትም። ያለውን ይሰጣል። ደግማ፣ ደጋግማ ከራሷ ሞገተች፣ ቤት ኪራይ ደርሷል። እየራባት፣ እየጠማት ነው።

ሀሳቧን ዓይምሮዋ በዋዛ አልተቀበለውም። ለቀናት ከርሀብና ከውስጧ ስትታገል ቆየች። ሌሊሴ ወደአገሯ መመለስ ፈለገች። ብቻዋን ወጥታ ልጅ ይዛ መመለሱ ከበዳት። ሰው ቤት ሰራተኛ ለመሆንም አሰበች። ከነልጇ ለመቀጠር ፈተናው ከባድ ነው። እሱንም ተወችው።

### የወዳጅ ምክር

ቀናት ከነችግራቸው እየነጎዱ ነው። ሌሊሴ በዝምታ ያለፈቻቸው ጊዜያት መፍትሄ አላመጡም። አሁንም ጨንቋታል፣ ችግሯን በየቀኑ የምታይ አንዲት ባልንጀራዋ ግን ይበጃል ያለችውን መላ ማመላከት ይዛለች። ሴትዬዋ ጠዋት ወጥታ ማታ የምትመለስ ጎረቤቷ ነች። መንገድ ላይና ቤተክርስቲያን ደጃፍ እንደምትለምን ታውቃለች።

ጎረቤቷ ሌሊሴን ካለችበት መከራ ያሻግራል ያለችው የልመናውን ሥራ ነው። ራሷን ምሳሌ አድርጋ እንድትሞክረው ስትገፋፋት ቆይታለች። ሌሊሴ ይህን በሰማች የመጀመሪያ ቀን ሀሳቧን ስትኮንነው፣ ድርጊቷን ስትቃወመው ውላለች። ልመና አስነዋሪ መሆኑን ነጋሪ አያሻትም። ደጋግማ ባሰበችው ቁጥር በጎረቤቷ ምክር አፍራለች፣ ተሸማቃለች።

አሁን የቤቷ ችግር ብሷል። ልጇን እያጠባች፣ ስታለቅስ ትውላለች እስከዛሬ ጎረቤቷ ያለቻትን ለመቀበል ስትወላውል ነበር። አሁን ግን ሀሳቧን ከመቀበል ሌላ ምርጫው የላትም። ሌሊሴ ሁኔታው ቢከብዳትም ልመናውን ልትሞክረው ወሰነች። ቤት ተቀምጣ ልጇን በርሀብ ከመግደል፣ ራሷም ከመሞት የተባለችውን መፈጸም ግድ መሆኑን አመነች።

### የሰው ፊት እሳቱ

አንድ ቀን ማለዳ ሌሊሴ ትንሸዋን ልጅ ይዛ ከመንገድ ዳር ተቀመጠች። ውስጧ ፈርቷል፣ ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል። የሰው ፊት እሳት ሆኖ እየፈጃት ነው። ሙሉ አካል ይዞ እጅን ለልመና መዘርጋት እጅግ ይከብዳል። ሌሊሴ ይህን ተቋቁማ መለመኑን ይዛለች። የመጀመሪያው ቀን በቁም የሞተች ያህል ተሰማት። ቀና ብላ የሰው ዓይን ማየት እስኪከብዳት አፈረች፣ ተሸማቀቀች።

በሚቀጥለው ቀን እንደ መጀመሪያው አልሆነችም። ፍርሀቱ ባይለቃትም ጥቂት ለመደችው። ትንሸዋ ሴና ባህሪዋ ይለያል። ያየችውን ትለምዳለች፣ አላፊ አግዳሚው አያልፋትም። የመልኳን፣ ማማር፣ የልጅነቷን ለዛ ያዩ ሁሉ እያቀፉ ይስሟታል። ሴና ፍቅር የሰጧትን ተከትላ ትሄዳለች። ስትመለስ እጇ ባዶ አይሆንም። የተጠቀለለ ብር ታመጣለች።

መሀል አራት ኪሎ ሌሊሴንና ልጇን የሚያዩ ሁሉ ከልብ ያዝናሉ። አብዛኞቹ የምሳ ዕቃቸውን ያካፍሏቸዋል። አንዳንዶች ያልተጎዳ ፊታቸውን እያዩ በሀዘኔታ ያልፋሉ። ጥቂቶች ደግሞ እናት ሌሊሴ ሰርታ እንድትበላ ይመክራሉ። ትንሸዋ ልጅ በየተራ ፀሐይና ብርድ ያገኛታል። ቀን ውላ ማታ ስትመለስ የጠዋት ገጽታዋ ይጠቁራል። እያደገች ቢሆንም ተጎሳቁላለች፣ የዕለት ጉርስ ባታጣም የአካሏ ጉዳት ኑሮዋን ያሳብቃል።

የጎዳናው ላይ ውሎ ቀጥሏል። ሌሊሴ ውስጧ ቢጨነቅም ልመናውን አልተወችም። ወደ ቤት ስትገባ የእጇን ገቢ ትቆጥራለች፣ ሲጠራቀም የቤት ኪራይዋን ይችላል። ቀለባቸውን ይሸፍናል። ከወጪዋ የሚተርፋትን ለይታ ለነገ ታስቀምጣለች። እንዲያም ሆኖ ውስጧ ሰላም ያጣል።

አንድ ቀን የሚያውቋትን ብታገኝ ሊሆን የሚችለውን ታስብና ራሷን ትረግማለች። ካገሯ ወጥታ ለልመና መዳረጓ ደጋግሞ ያሳፍራታል። ሌሊሴ ከልመና ይልቅ ሥራን ትመርጣለች። ካለችበት ሕይወት የሚያወጣትን እያሰበች ነው። አጋጣሚ ሆኖ አንድቀን ጆሮዎቿ መልካም ነገር አቀበሏት። አንድ ድርጅት ሥራን ለሚሹ ሰዎች ራስን እንደሚያስችል ሰማች።

ከተባለችው ስፍራ ስትሮጥ ደረሰች። ድርጅቱ ተገቢውን ጥያቄ አቅርቦ፣ በስልጠና መክሮ ጥቂት መቋቋሚያና ለጀብሎ ንግድ የሚሆኑትን አሟልቶ ሰጣት። ውላ አላደረችም። የያዘችውን ይዛ ማስቲካና ብስኩት መሸጥ ጀመረች። ትናንት በልመና የሚያውቋት መንገደኞች ሌሊሴን ቢያዩ አመሰገኗት። ጥቂት ነገሮች በሳንቲም እየገዙ ብዙ ገንዘብ ይተውላት ያዙ።

የሌሊሴ ገጽታ በፈገግታ ፈካ። ቀድሞ በልመና ከምታገኘው ብር የአሁኑ ጥቂት ገቢ ከልብ አስደሰታት። አንገቷን ቀና አድርጋ የእጇን መሸጥ ልምዷ ሆነ። ከማስቲካና ብስኩት ትርፍ ተነስታ የሞባይል ካርድ ሽያጭ ጀመረች። አዋጣት። አሁን የሠው እጅ እያየች አይደለም። ደስ እያላት ቤቷ ትገባለች።

### ከቀናት በአንዱ

ሌሊሴ ልመናን ከሥራ ባየችበት ጎዳና ብዙ ወዳጆችን አፍርታለች። እስከዛሬ እሷንና ልጇን የሚያውቁ ‹‹አይዞሽ፣›› ሲሏት ቆይተዋል። የአንዲት ሴት አቀራረብ ግን ከሁሉም ይለያል። ሄለን የባንክ ሰራተኛ ነች። ለትንሸዋ ሴና ልዩ ፍቅር አላትና አይታት አታልፍም። በየቀኑ የተጠቀለለ ብር ከእጇ ታኖራለች። በፍቅር ራሷን ዳብሳ አቅፋ ትስማታለች።

አንድ ቀን ይህች ወጣት ሌሊሴ ዘንድ ቀርባ ስለእሷ ነገ ያሰበችውን ነገረቻት። የቺፕስ ማሽን ከነሙሉ ወጪው ልትገዛላት ማቀዷን ስትሰማ ጆሮዋን ማመን ተሳነው። ከውስጧ እየተሟገተች ጥቂት ቀናት ቆየች። ፈገግታና ዕንባ ፈተኗት፣ ተስፋ ከድንጋጤ ከበባት። ህልም እንጂ እውነት ያልመሰላት ሀቅ ጊዜው ደረሰ።

ወዳጇ ቃሏን አላጠፈችም። ማሽኑን ገዝታ፣ አስፈላጊውን አሟልታ የኢትዮጵያን ፕሬስ ድርጅት በራፍ አንኳኳች። ፊት ያዞረባት፣ በር የዘጋባት የለም። ሀሳብ ዕቅዷን የተረዱት የድርጅቱ ዋና ሥራአስኪያጅ ሌሊሴን በሚፈለገው መጠን ለማገዝ ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋገጡላት። ይህን የምስራች ለእናት ሌሊሴ ያበሰረችው ሴት ሙሉ የኤሌክትሪክና የውሀ ፍጆታ በነፃ መጠቀም እንድትችል አመቻችታ ሥራውን አስጀመረቻት።

### ፈገግታ ያበራው ፊት

እነሆ! ሌሊሴ ታሪኳ ተቀይሯል፣ ትናንት ለልመና የተዘረጉ እጆቿ ዛሬ ለሥራ መጣደፍ ይዘዋል። አሁን የእሷ ጎዳና የልመና አይደለም፣ ፈጽሞ አትፈራም፣ አትሸማቀቅም። እጆቿ ድንች እየጠበሱ ብር ይቀበላሉ። ብር እየወሰዱ ሥራ ይፈጥራሉ። ዛሬ ዕንባዋ ታብሷል። ሀዘኗ ጠፍቷል ። ታሪኳ ተቀይሯል።

ሌሊሴ ደግማ ደጋግማ ፈጣሪዋን ስታመሰግን በጎ የዋሉላትን አትረሳም። ስለማንነታቸው ልዩ አክብሮት አላት። እነሱ ስሟን ለውጠዋል። ህልሟን ፈተዋልና ምስጋናዋ ከልብ ነው። የሌሊሴ ለውጥ በእሷ ብቻ አልቆመም። ልጇ ሴናም ታሪኳ ተለውጧል። አሁን እንደትናንቱ የጎዳና ብርድና ፀሐይ አያገኛትም። እንደቀድሞው የመንገደኛውን ዓይን አታይም።

ዛሬ ሴና በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሕፃናት ማቆያ ከሚጠቀሙ ባለመብት ልጆች አንዷ ሆናለች። እናቷ በሥራ ስትውል እሷ በተመቻቸ ስፍራ ታርፋለች። በዕድሜዋ የሚገባትን፣ ለማግኘት ድርጅቱ ያሻትን አሟልቷል። ጥሩ ለብሳ፣ ጥሩ ተመግባ የእፎይታ ዕንቅልፍ ትተኛለች። አሁን ጥቁረት ክሳቷ ጠፍቷል፣ ቁመቷ አድጓል። ፈገግታዋ ደምቋል።

### ሌሊሴ ዛሬ

እናት ሌሊሴ በቀን ከምታገኘው ገቢ ቆጥባ የሳምንት ዕቁብ ትጥላች። ነገ ስለሕፃን ልጇ የሰነቀችው ተስፋም ብሩህ ነው። አስተምራ፣ በወጉ አሳድጋ ዩኒቨርሲቲ የማድረስ ህልም አላት። ወደፊት ሥራዋን አስፍታ ከፍ ያለ ደረጃ ለመድረስ ዛሬ ብርታቷን ልታሳይ ቆርጣለች።

ሌሊሴ የትናንት ህይወቷ ለዛሬ ማንነቷ መሰረት ሆኗል። የዛኔ ሳትወድ የገባችበትን የልመና ታሪክ በጥንካሬዋ ዘግታዋለች። እንደዋዛ ልመናን ልምድ ለሚያደርጉት ደግሞ ከልብ ታዝናለች።

እሷን ወደጎዳና የገፋቻት ባልንጀራዋ ዛሬም ድረስ ሥራ ይሉትን አታውቅም። የሰውን እጅ ተማምናለችና ልመና ህይወቷ ሆኗል። እሷ ግን ዛሬ በለውጥ መስመር ቆማለች፣ ትናንትን ረስታ፣ ዛሬን አክብራ፣ ነገን ተስፋ ታደርጋለች። ብርቱዋ፣ ጠንካራዋ ፣ የሊቃ ዱለቻ ጉብል ሌሊሴ ቀጄላ።

# የሻከሩ እግሮችን ያልረሳው ውጤት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ዶክተር አዲስዓለም አባትሁን ትባላለች። እንደ ሀገር የሚቆጠርና የሚታይ ሥራን ከአበረከቱ ሴቶች መካከል አንዷ ነች። በተለይም በየዩኒቨርሲቲው ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ድረስ ብቸኛ ሴት ያውም አመርቂ ውጤት እያስመዘገበች የቀጠለች በመሆኗ በአብነት የሚያስጠቅሳት ነው። በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚገኙ ኮሌጆች ትልቁ ለሆነው የተፈጥሮና ኮምፒውቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ በ70 ዓመት ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት ዲን በመሆንም ከሶስት ዓመታት በላይ መርታለች። ከዚያ ባሻገር የአዲስ አበባ ምክር ቤት የመንግስት በጀትና ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ በጸሐፊነት በማገልገል ላይ ትገኛለች። እናም ይህን መሰል ተሞክሮዋ ብዙዎችን የሚያስተምር በመሆኑ ለዛሬ የሴቶች ቀን እንግዳችን በማድረግ ከብዙ አስተማሪ ሕይወቷ በጥቂቱ ጨለፍ አድርገን ለአንባቢያን እነሆ ብለናል።

## ትንንሾቹ እጆች ለአረቄ ማውጣት

ተወልዳ ያደገችው በአማራ ክልል ደብረማርቆስ ከተማ ነው። በኑሯቸው በጣም ዝቅተኛ ከሚባሉ ቤተሰቦች የተገኘች ናት። በመሆኑም በልጅነቷ ወቅት ችግሮችን እንዴት መጋፈጥና ማሸነፍ እንደሚቻል ሕይወት ራሷ ስላስተማረቻት ጠንቅቃ አውቃዋለች። በማገልገል ውስጥ ያለውን መለወጥም አሳምራ ተረድታዋለች። በተለይም ለቤተሰብና ለጎረቤት መታዘዝን ያለውን ጠቀሜታና በረከት በደንብ የተገነዘበችበት ጊዜ ነው።

ሴት ከወንድ ታንሳለች የሚለውን ሳታውቅ የማደጓ ምክንያትም ይህ በድህነት ውስጥ ያለው ጥረቷ ነበር። ሁሉም ላይ አሸናፊ እንደምትሆን አሳይቷታል። በጣም ጎበዝ መሪ እንደሆነችም አረጋግጦላታል። ምክንያቱም እናቷ የእርሷ አርአያ ናቸው። አባቷ የጥበቃ ሰራተኛ በኋላም ተላላኪ እና መዝገብ ቤት ሰራተኛ በመሆናቸው በቂ ገንዘብ አያገኙም ነበር። ስለዚህም አጋዥና ቤቱን የሚደጉም ሌላ ሰው ግድ ያስፈልጋል። እኚህ ሰው ደግሞ እናቷ ሲሆኑ፣ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ደግሞ በሚገባ ተወጥተዋል። አረቄ ሳይቀር አውጥተው እየሸጡ ቤቱ እንዳይጎል ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ ለትንሿ አዲስዓለም መሰረትም መወጣጫ መሰላል ነበር። በምን መልኩ ቤተሰቡን ማገዝ እንደምትችልም አሳይቷታል።

ከሦስት ኪሎ ሜትር በላይ በባዶ እግሯ እየተጓዘች እንጨት ለቅማ በማምጣት ለእናቷ የተረፈችውም በዚህ ምክንያት ነው። አደግ ስትል ደግሞ ከዚህ በበለጠ ሥራ እንድትሰማራ ሆናለች። ራሷን በመቻል ከቤተሰቡ ጫንቃ ላይ መውረድም ችላለች። ይህም ልክ እንደእናቷ አረቄውን በማውጣት ለደብተርና ለእስኪርብቶ እንዲሁም ለልብሷ ወጪ እንዳያስቡ አድርጋለች።

አዲስዓለም፣ ስራ የማይደክማት ልጅም ነች። የትምህርት ፈረቃዋን ጠብቃ ከትምህርት በኋላ እንጨት ለመልቀም ዘወትር ከሦስት ኪሎ ሜትር ያላነሰ መንገድን በባዶ እግሯ ትጓዛለች። ከዚያ ስትመለስም አረቄ ማውጣቱ ላይ ትጠመዳለች። እናቷም ሥራ ስለሚበዛባቸው እርሳቸውን ታግዛለች። ከምትሰራቸው ስራዎች መካከል እንጀራ መጋገርና ወጥ መስራት ዋንኛው ተግባሯ ነው። ይህ የጀመረው ገና በስምንት ዓመቷ እንደነበርም አትረሳውም።

አዲስዓለም፣ ቤተሰብን የምታስደስተው በሥራ ብቻ አይደለም። በሌሎችም ተግባሮቿም ጭምር እንጂ። ለታናናሾቿ አርአያ በመሆንና ቤተሰቦቿን ደግሞ በማዝናናት ትታወቃለች። በማዝናናቱ የአባቷን ህመም ታስረሳለች። እንዴት ከተባለ ወንድሟ በክራር እርሷ ደግሞ በእስክስታ ነው። በእድሜ እኩዮቿ ለሆኑ ትልቅ ምሳሌም የምትሆን ናት። ለአብነት በሽልማቷ ወቅት በምታደርገው ንግግር ሁሉንም የአካባቢዋን ልጆች ታበረታታቸዋለች። ወላጆችም በተለይም ሴት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኳቸው በዓይናቸው እያዩ እንዲያረጋግጡ አድርጋቸዋለች።

አዲስዓለም፣ በብዙ ሥራ ብትጠመድም ወላጆቿ የመጫወቻ ጊዜ ስለሚሰጧት ታከብራቸዋለች። ሥራዋን ከጨረሰች በኋላ ከወንዶች ጋር ሳይቀር እግር ኳስ ትጫወታለች። በዚህ እንኳን ማንም ምንም አይላትም።



ዶክተር አዲስዓለም አባትሁን

ፎቶ-ገበበ ገብሬ

ምክንያቱም በትምህርቷም ሆነ ቤተሰቧን እንዲሁም ጎረቤቱን በማገልገል ማንም አያክላትም።

## የ50 ሳንቲም ከረሜላና ሒሳብ

ዶክተር አዲስዓለም፣ የትምህርት አይነቶች ላይ ብዙ ምርጫ አልነበራትም፤ ሁሉንም በተለየ ትኩረት ትወዳለች። በተለይ የሳይንስ ትምህርቶችን ማበላለጥ አትፈልግም። አንድ አጋጣሚ ግን ነገሮችን እንዲቀየሩ አደረጋቸው። ይህ አጋጣሚም የ5ኛ ክፍል ተማሪ እያለች የተፈጠረ ነው። ጋሽ እምሩ የሚባለው የ5ኛ ክፍል የሂሳብ መምህሯ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ይጠይቃል። ማንም የሚመልስ አልነበረም። ከእነርሱ ክፍል በፊት ጥያቄውን ሁሉም ክፍል ላይ ጠይቆታል። ነገር ግን ሊመልስለት የሚችል ተማሪ አላገኘም። እነዶክተር ክፍል ግን እርሷ ተገኘች። በዚህም መልሷ መምህሩ የሚይዘውን የሚጨብጠውን ነበር ያጣው። ትንሿን አዲስዓለምን ታቅፎ በሁሉም ክፍል ይዟት እየዞረ «የሒሳቧን ንግስት ተመልከቷት» ማለትን ብቻ ነው የመረጠውም። ግን ይህም አልበቃውም። ከኪሱ 50 ሳንቲም አውጥቶ ከረሜላ እንድትገዛ ሰጣት።

ከሁሉም ከአዕምሮዋ የማይጠፋውም ይህ ተግባሩ ነበር። ምክንያቱም ማስጨብጨቡን ለምደዋለች። መምህር ግን በዚህ ደረጃ ተደስቶባት ሳንቲም ሰጥቶ ከረሜላ እንዲገዛ መደረጉ ጭራሽ የማይገመት ነው። ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰቦቿ ጭምር በእርሷ ተስፋ የነበራቸው የዚያን ጊዜ ጀምሮም ነው። ስለዚህም ይህንን አጋጣሚ የማትረሳው አድርጋ ለዘላለም አስቀጥለዋለች። የሂሳብ ትምህርቱን ቋሚ ምርጫዋ አድርጋም ዛሬ ድረስ ይዛው የዘለቀችውም ያለምክንያት አይደለም።

ዶክተር አዲስዓለም፣ መሆን የምትፈልገው ፋርማሲስት ነበር። ምክንያቷም በጣም የምትወዳቸው እና የምትሳሳላቸው የአባቷ ዘወትር መታመም እና በሽታቸው በሚሄዱበት ሃኪም ቤት በውሉ ባለመታወቁ እርሳቸውን መፈወስ የሚችል መድኃኒት ተመራምራና አጥንታ በማግኘት አባቷን በማከም ከጭንቀታቸው ማሳረፍ የሁልጊዜ ህልሟ ነበር። ነገር ግን ከፍተኛ ውጤት አግኝታ የተመደበችው በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ስለነበረ የምትወደውን የሂሳብ ትምህርት ለመማር ወሰነች። ሦስተኛ ዲግሪዋ ድረስ በሒሳብ ትምህርት የተጓዘችውም በዚህ የተነሳ ነው።

አዲስዓለም፣ በሁሉም ክፍል ላይ ትምህርቷን ስትከታተል የማንበቢያ ጊዜዋ ከአንዷ ቀን በስተቀር ውስን ነው። ምክንያቱም በሥራ ስትደክም ትውላለች። ትንሽ እንኳን እፎይ ብላ የምታጠናው የጥበቃ ሰራተኛ የሆኑት አባቷ ዘንድ ለአዳር ስትሄድ ነው። አስጠኚ ጭምር ታገኝበታለች። ምክንያቱም እርሳቸው እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋልና ያስጠኗታል። ሌላ የማጥኛ ጊዜዋ ሙሉ ቀኗን የምታሳልፍበት የተለየችዋ ቅዳሜ ናት። በቤት ውስጥ ምንም ሥራ አትታዘዝበትም፤ ማንም አይረብሻትም። የማጥኛዋና የቤት ሥራዋን መስሪያ ቀን ተደርጋ ተወስናላታለች።

የቁጥር ሥራ አብዝታ ስለምትሰራም ሙዚቃ ቢከፈትም ጭምር ለእርሷ ቦታ የለውም። ጆሮ ሳትሰጥ ልዩ ትኩረቷን ጥናቷ ላይ ብቻ ነው የምታደርገው። ምክንያቱም በርትታ መማሯና ውጤታማ መሆኗ ለእርሷ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቡ ጭምር እንደሚጠቅም ታውቃለች። በዚህም ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የደረጃ ተማሪ ነበረች። በየጊዜው ትሸለማለችም። በዚህም የአካባቢው ሰው ሳይቀር አርአያ የሚያደርጋት ልጅ ሆናለች። በእርግጥ ለዚህ ያበቃት የቤተሰቦቿ ሁኔታ ነው፤ እነርሱን ከዚህ ችግራቸው ማላቀቅ የምትችለው ጠንክራ ስትማር ነው። ስለዚህም የቤተሰቦቿ ውርስ ትምህርቷ ብቻ መሆኑን አውቃ ታጠናለች፤ ጠንክራ ትማራለችም።

እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በነበራት የትምህርት ጉዞ አንድም ቀን ጫማ አድርጋ የማታውቀው አዲስዓለም፤ ትምህርቷን አሀዱ ያለችው በአብማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተከታትላበታለች። ከዚያ ወደ ደብረማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዛወረች። እስከ 12ኛ ክፍል ተምራም ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የትናንቱን ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የዛሬው ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲን መቀላቀል ችላለች።

በኮሌጁ የሒሳብ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከተመዘገቡ 60 ተማሪዎች መካከል ብቸኛ ሴት ነበረች። ይህንን ያዩ ጓደኞቿ እና የቤተክርስቲያን ልጆች ሂሳብ መማር ከባድ ነው እያሉ የትምህርት ክፍሉን እንድትቀይር ጎተጎቷት። እርሷ ግን ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ አለች። ምክንያቱም አቅሟን በሚገባ ታውቀዋለች። ይህንን ልበ ሙሉነቷን ደግሞ ብዙዎች ውጤታቸው ሲበላሽ እርሷ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ አስደንቃቸዋለች። እንዲህ እንዲህ እያለችም ከኮሌጁ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የመጀመሪያ ዲግሪዋን በሒሳብ ትምህርትም አጠናቀቀች።

ከተወሰኑ ዓመታት የሥራ ላይ ቆይታ በኋላ የመጀመሪያ ልጇን ወልዳ ሁለት ዓመት ያልሞላውን ልጅ ለእናቷ ሰጥታ ሥራ ለቃ ነበር እየሰራች ለመማር ወደ አዲስ አበባ የመጣችው። ሁለተኛ ዲግሪ የሚያስተምረው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ስለነበርም በርካታ ተማሪ የመግቢያ ፈተና ይወስዳል። እናም ከተመረጡና ፈተናውን ከአለፉት ውስጥ አንዷ ሆና ትምህርቱን እንድትጀምር ተደረገች። ይህ ሲሆን ግን ቤት ለቤት እያስጠናች የራሷን ገቢ እያመነጨች ነው።

ቆርጠው ከተነሱ የማይታለፍ ነገር የለም የምትለው ዶክተር አዲስዓለም፣ ብዙም ሳትቆይ የበለጠ የምትሰራበትን አጋጣሚ አግኝታለች። አዲስ አበባ በመጣች በሁለት ወር ውስጥ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የቅጥር ማስታወቂያ በማውጣቱ እዚያ እየሰራች እንድትማር እድል አግኝታለች።

ኮተቤ 15 ሰዓት እያስተማረች ተጨማሪ የተለያዩ ቦታዎች ላይ እየሰራች፤ የዘጠኝ ክሬዲት ኮርሶችን እየወሰደች የቀደመውን ውጤታማነቷን አላስተጓጎለችም። በተጨማሪም የሁለት ዓመት ልጇን ከእናቷ በማምጣት የእናትነት እና የሚስትነትን ኃላፊነት ደርባ በአግባቡ ትወጣ ነበር። በዚህ ሁሉ ውስጥም በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ የማዕረግ ተሸላሚ በመሆን የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን እንደወትሮው ሁሉ በአመርቂ ውጤት አጠናቀቀች።

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**

# "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!"



ዶክተር አዲስዓለም፣ የትምህርት ጉጉቷ በዚህ አላበቃም፤ ሁለተኛ ልጇን ከወለደች ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በኋላም የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት እድል በሳንዱች ፕሮግራም በስዊድን ሀገር በማግኘቷ ልታልፈው አልፈለገችም። ስለዚህም የመጀመሪያ ስድስት ወሩን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታ በቀጣይ ስድስት ወሩን ትምህርት ደግሞ በስዊድን ስቶክሆልም ዩኒቨርሲቲ ለመከታተል ወደስፍራው አቀናች።

ይህንን ስታደርግ ደግሞ ልጆቿን ለባለቤቷ ሃላፊነት በመስጠት ነው። በዚህ ሁኔታ ስድስት ወር አዲስ አበባ ስድስት ወር ስዊድን በመመላለስ ከአምስት ዓመት የትምህርት ጉዞ በኋላ የሦስተኛ ዲግሪዋን አጠናቅቃለች። ጥረቷም የመጀመሪያዋ ሴት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሒሳብ ትምህርት ክፍል ሦስተኛ ዲግሪ ተመራቂ አድርጓታል። በእርግጥ ሁለተኛ ዲግሪዋን ስትማርም ከ70 ተማሪዎች እርሷ ብቻ ሴት ነበረች።

## በ70 ዓመት ታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት ዲን

የአዲስዓለም የሥራ ሀሁ የጀመረው በአማራ ክልል በከሚሴ ከተማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሒሳብ መምህር በመሆን ነበር። በወቅቱ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላት ሌላ ሴት አስተማሪ አልነበረችምና ብዙዎች ይገረሙባት ነበር። በዚህም የዞኑ የመምህራን ማህበር የሴቶች ዘርፍ ኃላፊ ሆና አገልግላለች። ከዚያም በጋብቻ ምክንያት የሥራ ቦታዋን ወደ ደቡብ ጎንደር ጋይንት ንፋስ መውጫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አድርጋ ለሦስት ዓመታትም ቆይታበታለች።

ቀጣዩ ሥራዋ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ሲሆን፤ ሁለተኛ ዲግሪዋን እስክትጨርስ ድረስ ያገለገለችበት ስፍራ ነው። ጎን ለጎን ምኒልክ ነርሲንግ እስኩል በትርፍ ሰዓት ታስተምርም ነበር። ሁለተኛ ዲግሪዋን ስትማር የነበራትን ትጋት፣ ታታሪነትና ከፍተኛ ውጤት ያዩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙት አማካሪዋን ቀስቅሶ በሌላ ቦታ የምትሰራበትን አጋጣሚ ፈጠረላት። እኔን የምትተካው እርሷ ነች በማለት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንድትቀጠር አደረጓት።

መጀመሪያ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የተቀላቀለችው በመምህርነት ነበር። ከአምስት ወራት በኋላ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ፕሮግራም ዩኒት ኃላፊነት ተሰጣት። አዲስዓለም ከሁሉም ሥራ በላይ ማስተማርን አጥብቃ ትወዳለች። ምክንያቱም በእርሷ እምነት ማስተማር መምራት ነው። ሥራ ተኮር ተግባር መከወን ነው። ከሰው ጋር የሚያጋጭ ሳይሆን የሚያስተሳስር እንደሆነም ከ16 ዓመት በላይ በማስተማር ያገለገለችበት የማስተማር ስራዋ አሳውቋታል። በነዚህ የስራ ዓመታትም በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይም አገልግላለች። ከዚህም ውስጥ አንዱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካሉት ትላልቅ ኮሌጆች አንዱ የሆነውን የተፈጥሮና ኮንፒውቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ በተለምዶ አራት ኪሎ ካምፓስን በዲንነት መምራት ነው።

በዲንነት በርካታ ስራዎችን የሰራች ሲሆን፤ በተለይም እርዳታ ለሚሹ ተማሪዎች ከተለያየ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር ማመቻቸት፥ ሴት ተማሪዎችን የማበረታቻ የልምድ ልውውጦችን ማዘጋጀቷ ከአብራኳ ክፋዮች ባሻገር ሌሎች ልጆችን የፈጠረችበት ነው። ለአብነት በሴቶች ክበብ ውስጥ ሴቶች በማደሪያቸው (ዶርማቸው) ውስጥ የራሳቸው የውይይት ጊዜ እንዲፈጥሩ እድሎችን ማመቻቸቷ አንዱ ነበር። ውይይቱ ቀን በቀን የሚደረግ ሲሆን፤ ችግሮቻቸውን ተወያይተው ለመፍትሄ የሚሰሩበት እንዲሆን በብዙ መልኩ ደግፋቸዋለች። እነርሱም ስኬታማም ሆነውበታል። በእያንዳንዱ ውይይት ላይ በቻለችው ሁሉ ትገኝና የራሷንና የገጠማትን ነገር እያጋራች ታወያያቸዋለችና ብዙ ልምድም የቀሰሙበት ነው። በዚህም በተማሪዎቹ ዘንድ እንደ ሁለተኛ እናት ሆና ትቆጠራለች።

ሌላው የሰራችው ተግባር ተፈጥሮ ሳይንስ የሴቶች የምርምር ግሩፕ መስርታ እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው። ትልልቅ የሚባሉ ውድድሮችን በምርምሩ ዘርፍ እንዲያደርጉ አስችላለች። ለአብነት ስምንት የሚሆኑ ሥራዎችን ሰርተው በውድድር ውስጥ በመሳተፋቸው አምስቱን የማሸነፋቸው ምስጢር እርሷ ናት። ለሴቶች ብቻ የሚሉትን በብቸኝነት መሳተፍም እንዲችሉም እድል ሰጥታቸዋለች። በተመሳሳይ ሴቶች በምርምር አይሳተፉም የሚባለውን አባባል በመጠኑም ቢሆን አስቀርታለች።

ዶክተር አዲስዓለም፣ ለግቢው የአስተዳደር ሰራተኞችም የምትተኛ አይደለችም። በርካታ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በማሰጠት የተሻለውን ነገር እንዲያገኙ አድርጋለች። በተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲው የሚጠቀምበትን ሁኔታም አመቻችታለች። ለምሳሌ፡- በግቢው ውስጥ የከርሰ ምድር ውሃ በማስወጣት የውሃ ወጪዎችን ማስቀረት ችላለች።

ዶክተር አዲስዓለም በተጨማሪም የፕሮግራም ኮርድኔተርነት፤ በበርካታ ተቋሞች የቦርድ አባል በመሆን አገልግላለች። አዲስዓለም የኢትዮጵያ የሒሳብ ባለሙያዎች ማህበር መስራችና ገንዘብ ያዥ በመሆን ለሦስት ዓመታት አገልግላለች። አምስት የሚሆኑ የአፍሪካ ሀገራትን ያካተተው የምርምር ግሩፕም አባል ናት። በዚህም የምርምር ስራዋን እንድታሰፋ አድርጓታል። ምርምሯ በአብዛኛው ልዩ ትኩረቱ መሰረታዊ የሂሳብ እውቀቶች ላይ መተንተን ሲሆን፤ ይህንን ደግሞ በተለያዩ ሀገራት በመዘዋወር ታቀርባለች። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሒሳብ ወርክሾፖችን ሲዘጋጁ በአዘጋጅ ኮሚቴ አባልነት ታገለግላለች።

የዩኒቨርሲቲው አንዱ ተልዕኮ በሆነው የማህበረሰብ አገልግሎት ላይ በስፋት ትሰራለችም። ለዚህም ማሳያው በተለይም አራዳ ክፍለ ከተማ ላይ ያከናወነቻቸው ተግባራት ናቸው። ለምሳሌ በዚሁ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ላይ ማህበረሰቡ በርካታ ዓመታትን በውሃ ችግር አሳልፏል። እርሷም ይህንን ችግር በቅርብ ትከታተለው ነበርና ተዳፍኖ የቆየውን የከርሰ ምድር ውሃ በፕሮጀክት አስቆፍራ ማህበረሰቡም ሆነ የዩኒቨርሲቲውን ተጠቃሚ እንዲሆን አስችላለች። አሁን ውሃው በአራት ቦኖ በፓይፕ ተደርጎ እንዲሰራጭ ሆኗል።

ዶክተር አዲስዓለም፣ ሌላም በማህበረሰብ አገልግሎት የሰራችው ሥራ አለ። ይህም የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት የሚያገኙበትን አጋጣሚ የፈጠረው ነው። የጋራ መጸዳጃቸው ወደ ውስጥ ሰመጠባቸው። በዚህም ማህበረሰቡ ችግር ውስጥ ወደቀ። በቀላሉ ለመስራትም የሚቻልበት ሁኔታ ላይ አልነበረም። እርሷ ግን አይቻልምን አታውቅምና በፕሮጀክት አስተባብራ ወደ 400 ሺህ ብር ወጪ በማድረግ በአዲስ መልኩ እንዲሰራ አደረገችው። በሦስተኛ ደረጃ አዲስዓለምን ከማህበራዊ አገልግሎት ጋር ያገናኛት ነገር የአካባቢው ሰው የመንገድ መብራት ነበር። መብራቱ ባለመኖሩ የተነሳ ማህበረሰቡ ለተለያዩ ችግሮች እንዲጋለጥ ሆኗል። ይህንን የተመለከተችው አዲስዓለምም መፍትሄ ለመስጠት እጆቿን ወደ አጋሮቿ ዘረጋች፤ ተሳካላትም። የመብራት ግብአቱን ከማህበረሰቡ በተሰበሰበ ገንዘብ የተገዛ ሲሆን፤ ቋሚ የመብራት ስርጭቱን ደግሞ ከዩኒቨርሲቲው እንዲጠቀሙ አድርጋለች። በዚህም ዩኒቨርሲቲውን እንደቤተሰቡ የሚያየው ማህበረሰብን ፈጥራለች።

ይህና መሰል ሥራዋ ማህበረሰቡ ልብ ውስጥ የገባላት ዶክተር አዲስዓለም፤ በዘንድሮው ምርጫ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባልና የመንግስት በጀትና ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ በጸሐፊነት እንድታገለግል አስችሏታል። ድምጽዋን ተጠቅማም አሁን ላይ ሀገሯን እያገለገለች ትገኛለች። በዚህም በርካታ ተግባራትን በቻለችው ልክ እየከወነች ትገኛለች።

‹‹ሴትነት ከማህበረሰቡ የተበረከተልኝ ስጦታ ነው›› የምትለው ዶክተር አዲስዓለም፣ ከልጅነቷ ጀምሮ አብዛኛውን ወጪ የምትሸፍን፣ የቤቱን ሸክም የምትሸከምና በኃላፊነት ሰርታ ቤቱን ቀጥ አድርጋ የምትኖረው ሴት ልጅ እንደሆነች አይታ ያደገች ነች። በዚህም ዛሬን አስባ ስትሰራ ትናንትን እያስታወሰች ለነገ የሚሆነውን እያለመች ነው። ይህ ደግሞ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ተመራጭ ካደረጋት ባህሪ መካከል አንዱ ነው።

## መሪነት ለሴት ልጅ ችሮታ አይደለም

‹‹እንደሴት አይደለም፤ ታችኛው ክፍል ላይ መሪ ሆነሽ ላይኛውም ላይ ብትሆኚ ወደታች የሚስቡሽ ሰዎች አይጠፉም። ወድቀሽ እንድትታይ ብዙ የሚቆፍሩ አሉ። በተደጋጋሚ ገጥመውኛልም። ነገር ግን መሪ ስትሆኚ ለእነዚህ ነገሮች እጅ መስጠት የለብሽም። ኃላፊነት እስከተሸከምሽ ተረድተሽ ክፍ ብለሽ መታየት አለብሽ። ይህ የሚመጣው ደግሞ ከወንዶች ሦስት እጥፍ ስትሰሪ ነው። መሪነት ለሴት መቼም ቢሆን ሥራ እንጂ ችሮታ አይደለም። ከሰራሽ ሊጥልሽ የሚፈልገው ጭምር ያከብርሻል፤ እናም ሴት ልጅ ውድቀቷን የምትቀንሰው ሰርታ በማሳየት ብቻ እንደሆነ ማመን ያስፈልጋል›› የምትለው ዶክተር አዲስዓለም፣ ‹‹ለሴቶች ጥንካሬ ምንጩ ተፈጥሯቸው ነው። ባህል ሲጎትታቸው በተፈጥሮ ሰርተው ያሸንፋሉ የሚል አቋም አለኝ›› ትላለች።

‹‹የሴቶች ፈተና የሚመጣው ከቤተሰብ ጭምር ነው። ለምሳሌ ልጆች ይበልጥ እናታቸውን ይፈልጋሉ፤ ቤቱ በራሱ ያለእናት ሙሉ አይሆንም፤ ትዳርም እንዲሁ። ከዚያም ባሻገር ማህበራዊ ሕይወት ጭምር የሚሞላው በሴት ነው። ስለዚህም ሸክምሽ የሚሆነው ሦስት እጥፍ ነው። እናም የምንተኛበትን ሰዓት ፣ ከማህበራዊ ተሳትፎ በመጠኑና ከቤተሰብ ጭምር በትንሹ ጊዜን ማዋጣት ግድ ይላል።›› የምትለው ዶክተር አዲስዓለም፣ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውንም ምልከታ መቀነስ ያስፈልጋል ስትልም ትገልጻለች። በተለይም በሴት መመራት የሚያመውን ሰው እንኳን መሪ ሆነች ማሰኘትን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ ምርጫው መስራትና መስራት ብቻ ነውም ስትል ትመክራለች።

## የሕይወት ፍልስፍና

‹‹እኛ ሳንሆን ፈጣሪ የእኛን መንገድ ይመርጣል›› የአባቷ የዘወትር ንግግር ነው። የእርሷም መርህ ነው። ማንም ሰው የሚያስጨንቀውን ነገር ተሸክሞ መዞር የለበትም። ምክንያቱም ጭንቀት አሲድ ነው። አሲድ ደግሞ ያጠፋል። ስለሆነም በዚያ እየተቃጠሉ ከመጥፋት ለችግሩ መፍትሄ መሆን ይገባል የሚል አቋምም አላት። ቅንነትን አስቀድመንና በመልካም ነገሮችን ተርጉመን አሲዱን ማምከን ከሁላችንም ይጠበቃል -ሌላኛው መርህዋ ነው።

## ሽልማት

ተማሪዎቿ ምርጥ የሒሳብ መምህርት በሚል የሸለሟት አንደኛው ነው። በአመራር ብቃቷ አንቱታን ያተረፈች ነች። ተምሳሌት ነች በሚልም በርካታ ሽልማቶችን ከተለያዩ አካላትና ተቋማት አግኝታለች። ለአብነት ኢንተርናሽናል ሳይንስ ፕሮግራም ( ISP) በኢትዮጵያ በሒሳብ የሴቶች አመራርን ለማጠናከር ላበረከተችው አስተዋፅዖ እኤአ የ2022 ምርጥ አርአያ ሴት መሪ በማለት እውቅና ሰጥቷታል። በቅርብ በጀርመን ሀገር ለአፍሪካ ጀማሪ መሪዎች የሚሰጠውን ስልጠና ለመከታተል ከ30 የአፍሪካ ሀገራት ከተውጣጡ መሪዎች መካከል የስልጠና እድል አግኝታለች።፡

## መልዕክት

እኛ ሴቶች ‹‹እባክሽን እዚህ ላይ ተቀመጭ›› እስክንባል መጠበቅ የለብንም። ልክ እንደወንዶች ሁሉ ተሻምተን የሚገባንን ቦታ ማግኘት አለብን። ከዚያ ባሻገር ሴቶቹ ለሴቶቹ ያለንን ክብር መጨመር ይገባናል። አንዳንችን ከአንዳችን የተሻልን ከሆንን ተደጋግፎ መውጣትን ማጎልበት ይጠበቅብናል።

ሴቶችን በአቅም ማሳደግ ላይ ከመንግስት አካል አለያም ከሌሎች ድርጅቶች እድል እስኪሰጥ መጠበቅ አይገባንም። የየራሳችንን ድርሻ መወጣት ላይ ማተኮር ይገባል። አንሺውም አድራጊውም እኛ መሆን ይጠበቅብናል። በሴቶች ላይ የሚመጡ ፈተናዎች መቼም አይቆሙም። መግታት ግን ይቻላል። ለዚህ ደግሞ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል። ሴቶችን ማበርታትና ወደ መሪነት ማምጣት ይገባል። ይህ ሲባል ግን ለግብዓት ፍጆታ፣ አበቃን ለማለት፣ ኮታ ለመሙላት መሆን የለበትም። እንደሚችሉ አምነን ወንበሩን በማቆናጠጥ ነው። ምክንያቱም ይችላሉ። የተሻሉ ሆነውም በብዙ ቦታዎች እየታዩ ናቸው። ስለዚህም ጠንካሮችን ፈልጎ ቦታውን መስጠት ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው።

ለሴቶች ብዙ እድሎች አሉ። ነገር ግን መሞከር ላይ በጣም ችግር አለብን። በዚህም መልካም እድሎችን እንዳንጠቀምባቸው ሆነናል። እኔ በቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአካባቢዬ ላይ ሳይቀር ለሴቶች አርአያ መሆን የቻልኩት ውጤታማነቴን አስጠብቄ በመሄዴ ነው። በተለይም 12ኛ ክፍል ላይ ከፍተኛ ውጤት አምጥቼ ማለፌና ዩኒቨርሲቲ መግባቴ የብዙዎችን ቤተሰቦች በትምህርት ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ እንድቀይር አድርጎኛል። አሁንም ለሴቶች እድል እየሆንኩ ነው። እናም ለሌሎች እህቶቼ የማስተላልፈው መልዕክት እነርሱም ለሌሎች እድል ሰጪ ይሁኑ የሚል ነው። ምክሯ ገንዘባችሁ ይሁን በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን። ሰላም!!

# የሕይወት ፈተና ያልበገራት እናት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ዛሬ የተገኘንበት በተለምዶ ‹‹ሀዲድ›› ገበያ አልያም ‹‹መሿለኪያ›› ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ነው። ይህ መገኛው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የሆነ ቦታ ምናልባትም የአካባቢው ልዩ ገጽታ ማሳያ ነው ቢባል መዳፈር አይሆንም፡፡

ቦታው እግረኛ እንጂ መኪና የያዘ ዝር አይልበትም። መኖሪያው ለአንቡላንስ ጭምር የተፈቀደ አይመስልም። ኮሮኮንች የበዛበት ጥርጊያ ቢሆንም ቤቶቹ እርስ በእርሳቸው የተጠጋጉና የተደጋገፉ ናቸው። በዋዛ መውጣት መግባት አይቻልም። በዚህ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች ቢያማቸው እንኳን የሚደርስላቸው ጎረቤት እንጂ አንቡላንስ አይሆንም። አያድርገውና እሳት ቢነሳ አብረው ከመጋየት የዘለለ ምርጫ አይኖራቸውም። የእሳት አደጋ መኪና መግቢያ ይሉት አይታሰብበትም።

ስፍራው እንዲህ ይባል እንጂ አይጠላም። እንደውም ይመረጣል፤ ይወደዳል። ምክንያቱም ድሆችን ሳይንቅ እፎይታን ይሰጣል። በጉልበት፣ በአቅም የደከመውን በዝቅተኛ ዋጋ ያሳርፋል። ከሁሉም የሚበልጠው ደግሞ የእርስ በእርስ መተጋገዝ ያለበት መሆኑ ነው፡፡

ስፍራው የጨነቀው ችግሩን የሚረሳባቸው፣ በርካታ አጋጣሚዎችም አሉት። ከነዚህ አንዱ መልካም የስራ እድል መኖሩ ነው። ብዙ ቤቶች ከሌሎች ጋር ተጋርተው የገቢ ምንጭ ያስገኛሉ። ሌሎች ደግሞ ከእነርሱ የባሱትን እያዩ እንዲጽናኑ ይሆናል። ከምንም በላይ ደግሞ መልካም ጉርብትናው ሁሉንም ችግር ገደል የሚሰድ ነው፡፡

በስፍራው የራበው አይመለስም፣ በኪሱ አቅም ይመገባል። የታረዘም ይለብሳል። የዚህ ስፍራ ድንቅ ጉዳይ በሚገኘው ጥቂት ገንዘብ ቤት ተደጉሞ፣ ችግር ተሸፍኖ ልጆች ለቁምነገር መብቃታቸው ነው። ይህንን ምስክርነት የሚያረጋግጡልን የዛሬዋ የ‹‹እንዲህም ይኖራል›› አምድ እንግዳችን ወይዘሮ ገበያነሽ መንገሻ ናቸው። ገበያነሽ በአካባቢው በዝቅተኛ ዋጋ ቤት በማከራየት ኑሯቸውን የሚገፉ ወይዘሮ ናቸው።

ወይዘሮ ገበያነሽ ሥራቸውን ‹‹አሀዱ›› ያሉት ጫማ ፋብሪካዎች ውስጥ ነበር። በጫማ ስፌት ሙያ 32 ዓመታትን አሳልፈዋል። 1983 ዓ.ም ግን ለእርሳቸው መልካም ሆኖ አልመጣም። ዓመታትን በሥራ ከዘለቁበት፣ ድርጅት በሰራተኛ ቅነሳ ሰበብ ተሰናበቱ። ብዙ ከለፉበት፣ ሙያን ካካበቱበት ሥራ ድንገት ለቀው የት እንደሚደርሱ ግራ ገባቸው፡፡

ወይዘሮዋ እንጀራን ፍለጋ ባዘኑ፣ ተንከራተቱ። በሙያቸው ሊቀጥሯቸው የሚችሉ ተቋማትን ያለ እረፍት ማፈላለግ ያዙ። አንድ ቀን ‹‹ኢትዮ ጣሊያን›› ጫማ ፋብሪካ የካበተ ልምዳቸውን መዝኖ በሙያቸው ቀጠራቸው። እጆቻቸው ዳግም በጫማ ስፌት ላይ ዋሉ። ‹‹እፎይ›› ማለት ሲጀምሩ ፋብሪካው ዓመታትን ያሻገራቸው አልሆነም።

በወቅቱ ጣሊያኖቹ በመክሰራቸው ፋብሪካውን ሊዘጉት ተገደዱ። የነበሩት ሰራተኞችም ሊበተኑ ግድ ሆነ። እናት ገበያ ድንገቴው አጋጣሚ ፈተናቸው። ሦስት ልጆቻቸውን በወጉ ለማስተዳደር ኑሮ ያንገዳግዳቸው ያዘ።

ባለቤታቸው ወታደር ነበሩ። ግዳጅ ሳሉ ተሰውተዋል። ሁሉም ልጆች የእርሳቸውን እጅ ናፋቂ ናቸው። ወይዘሮዋ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ተጋቡ። ሰማዩ የተደፋባቸው ያህል ጨነቃቸው። ከስራ ሲሰናበቱ ቀናትን የሚያሻግር እንኳን ገንዘብ አልያዙም። ያላቸውን ሸጠው ልጆቻቸውን የሚመግቡበት ጥሪት አላቆዩም፡፡

ዘወትር ስራ ፍለጋ ማልደው ይወጣሉ። ያለአንዳች ውጤት ይመለሳሉ። በአንድ አጋጣሚ ግን በሙያቸው ብቻ ስራ ፈልገው እንደማይዘልቁ ገባቸው። በደሞዝም ሆነ በሙያ የማይመጥናቸውን ስራ ለመስራት ወሰኑ። በላይአብ ሞተርስ ስፔርፓርትና መገጣጠሚያ ድርጅት ተቀጥረው በጥበቃ ስራ ዘብ ቆሙ፡፡

ምን የከፋ ችግር ቢገጥማቸው እጅ የማይሰጡት ወይዘሮ ገበያነሽ፤ ዝቅ ብሎ መስራት አንድ ቀን ከፍ እንደሚያደርጋቸው ያውቃሉ። ለልጆቻቸው የተሻለውን ለመስጠት የሙያውን ታላቅነት ተቀብለው በብርታት ስምንት ዓመታትን አሳለፉ።

‹‹እግዚአብሔር የሚወደውን ይፈትናል። እኔም በብዙ ተፈትኜ ተስፋ የቆረጥኩበት ጊዜ ነበር›› የሚሉት ባለታሪካችን፤ በዚህ ድርጅት ሳሉ የሚወዷት ልጃቸው



ወይዘሮ ገበያነሽ መንገሻ

በኩላሊት ህመም በጠና ስለመታመሟ ያስታውሳሉ፡፡ በወቅቱ በቀላሉ የሚያሳክሟት አልሆኑም። ህክምናው አቅምን ይፈትናል፡፡

ክፍያው እንደሳቸው ጥበቃ ለሚሰራ ቀርቶ በቂ ገቢ ላለው ሀብታም እንኳን አይደፈርም። ለአንድ ጊዜ ዲያሌሲስ ብቻ ከ1800 ብር በላይ ያስፈልጋል። በመንግስት ሆስፒታል በቀላል ወረፋ ስለማይገኝ የግል መታከም ግድ ሆኗል። በጊዜው ከዲያሌሲሱ ክፍያ ባሻገር ለሌሎች ወጪዎች የሚከፍሉት ክፍያ ከአቅማቸው በላይ ነበር።

የወይዘሮ ገበያነሽ ስቃይ በአንዱ ብቻ አልበቃም። የታማሚ ልጃቸውን ወጪ ለመሸፈን እየተንገዳገዱ ሳለ ሌላ ከፉ ገጠመኝ አገኛቸው። በድንገት ሁለተኛው ልጃቸው በስኳር በሽታ ታመመ። አንዱን ተወጣሁ ማለት የጀመሩት እናት በሁለተኛው ችግር ተስፋቸውን አሟጠጠው።

የመጀመሪያዋን ልጃቸውን ሲያስታምሙ የሥራ ባልደረቦቻቸው የአቅማቸውን ያግዟቸው ነበር። ገንዘብ የሌላቸውም ተራቸውን እየሸፈኑላቸው ቆይተዋል። ሁለተኛው ችግር ሲመጣ ግን ሁሉ ነገር ከበዳቸው። ለየትኛው ልጃቸው እንደሚሆኑ ግራ ተጋቡ።

አንደኛው ምግብ፣ ሌላኛዋ ደግሞ የዲያሊስስ ህክምና ወጪ ያስፈልጋታል። እሳቸው የትኛውንም ማሟላት አይችሉም። ዘወትር እንዳለቀሱ፣ እንዳዘኑ ዘልቀዋል። እናት ናቸውና ልጆቻቸውን ‹‹ይሙቱ›› ብለው አልተዋቸውም። ቀን እየሰሩ፣ ሌሊቱን በማስታመም ደክመዋል። እርሳቸው ሳይበሉና ሳይለብሱ ለእነሱ ህክምና እየደጎሙ ከአቅማቸው በላይ ለፍተዋል።

በሁለት ልጆቻቸው ህመም እየተሰቃዩ የቆዩት ወይዘሮ፤ ይባስ ብሎ ድንገቴ ችግር ገጠማቸው። ልጆቻቸውን እየደጎመላቸው የቆየው ሥራ በአንድ አጋጣሚ ቆመ። ለእሳቸው እንዲህ መሆኑ ሌላ ህመም ነበር። በወቅቱ የድርጅቱ ቦታ መቀየር ከሌሎች ቅርንጫፎች ጋር ሰራተኛው እንዲቀላቀል ተገደደ፡፡

ይህ እውነታ ሁለት የሴት የጥበቃ ሰራተኞችን ቀንሶ ከስራ አስወገደ። አንደኛዋ እሳቸው ነበሩ። አሁን ነገሮች የባሱ፣ ሆኑ። የበዛ ጭንቀታቸው ‹‹ከልጆቼ ቀድሜ እኔ መሞት አለብኝ›› እስከማለት አደረሳቸው።

ራሳቸውን ማረጋጋት ያልቻሉት ባለታሪካችን፤ ችግሩ ባሰባቸው። ይህ ከፉ አጋጣሚ ደግሞ ብቻውን አልመጣም። መጀመሪያ የታመመችውንና ጧሪ፣ መከታዩ ያሏትን ትልቋን ልጃቸውን በሞት ተነጠቁ። ሀዘናቸው ከፉ፣ ውስጣቸው ደም አነባ። እናት ገበያ ጠዋት ማታ ‹‹እዬዬ›› ማለት ልምዳቸው ሆነ።

ጥቁር ልብሳቸውን ሳይለውጡ፣ ሀዘናቸውን ሳይረሱ፣ ሌላ ሀዘን ሆነ። በዓመቱ ወንዱ ልጃቸው ተደገመ። የ21 ዓመት ወጣትና የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነበር። ገበያነሽ ሕይወት ከበዳቸው። መኖር አስጠላቸው። አሁን አንድ ልጅ ቀርቷቸዋል። የልጃቸው ልጅ ጭምር ተስፋቸው ነው፡፡

የእነሱ መኖር ራሳቸውን እንዳያጠፉ፣ ነገን በጭላንጭል እንዲያዩ ምክንያት ሆኗል። ይህ እውነት ለእነዚህ ልጆችስ ማን አላቸው እንዲሉ አስችሏቸዋል። ሀዘናቸውን ለመርሳት እንዲታገሉ ሰበብ ሆኗል።

ወይዘሮ ገበያነሽ በትዳር ሕይወታቸው ይኖሩ የነበሩት አራተኛ ክፍለ ጦር አካባቢ ነበር። አካባቢው ለልማት በመፈለጉ ግን ከቦታው እንዲነሱ ተደረጉ። ይህ የሆነውም በደርግ ጊዜ ነው፡፡፡ከጊዚያት በኋላ ወደዚህ ቦታ መጥተው እንዲሰፍሩ ሆኑ፡፡

በወቅቱ ቆርቆሮ በቆርቆሮ ተሰርቶ መደዳውን ነበር የተሰጣቸው። እናም ያለአባት የሚያሳድጓቸውን ልጆች በብርድና በሀሩር አላሰቃይም ብለው ቤቱን ከቆርቆሮ ወደ ጭቃ ቤት ቀየሩት። በእርግጥ ይህንን ያደረጉት ለልጆቻቸው በሚል ብቻ አልነበረም። የባለቤታቸውንም ስም በመልካም ለማስጠራት እንጂ። እርሱ ቢኖር ኖሮ ይህንን ያደርግ ነበር እንዲባል አይፈልጉምና ምንም እንዳልጎደለባቸው ለማሳየት የአቅማቸውን አድርገዋል። በዚህም ብዙዎች ይኮሩባቸዋል፤ ከአካባቢው ብዙ ሰዎች ‹‹ጠንካራ ነች›› ይሏቸዋል።

ወይዘሮ ገበያነሽ ልጆቻቸውን ማስረሻ ይሆነኛል ያሉት የልጅ ልጃቸው ምን እንኳን እርሳቸው ጋር ባይኖር በየጊዜው ይጠይቁት። ይንከባከቡት ነበር። ልፋታቸው አልተቆጠረም። ሀሳባቸው አልሰመረም። እርሱንም እንደእናቱ በከባድ ህመም በሞት ተነጠቁ። ልጁ በጉበት በሽታ ሲሞትባቸው ሀዘናቸው እጅግ ከባድ ነበር። ለረጅም ጊዜም በሀዘን ስቃይ ቆይተዋል።

ገበያነሽ ጉልበታቸው በደከመ፣ ደጋፊ፣ ጧሪና ቀባሪ በሚሹ ጊዜ ጎዶሏቸውን ያስባሉ። እኩያ የሚባሉ ልጆቻቸውን ማጣታቸው ልባቸውን ሰብሯል። አሁን ልጆቻቸውን መርሳት ባይችሉም የደከመ ጉልበታቸውን ለበለጠ ድካም ሳያጋልጡ መሥራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ናቸው ፡፡

ዛሬ ላይ በዝቅተኛ ዋጋ ልጃቸው ማከራየት የጀመረችው የአልጋ ኪራይ ቀጥለዋል። ከሞት የተረፈ አንድዬ ልጃቸውንና ሊያሳድጓት ያመጧትን ልጅ በሚያገኙት ገቢ ያስተዳድራሉ። የመኖሪያ ቤት ችግር ለብዙዎች ፈተና ነው። የመሰሎቻቸው ሕይወት ከዚህ የተለየ አይደለም። በተለይ የነ ገበያነሽን መንደር የመሰሉ ለዘመናት ኋላቀር የሆኑና ያለ ፕላን የተለጠጡ ነበር አካባቢዎች የፈተናው ገፈት ቀማሾች ናቸው።

እርሳቸው ግን በሌሎች ፈተናዎች የቤቱን ጉዳይ ተወጥተውታልና የከፋ ችግር አልገጠማቸውም። ይልቁንም አልጋ አከራይ ሆነው ተጠቃሚ ሆነዋል። አሁን ላይ በላይ ክፍል ሰርተው የሚያከራዩት ቤት በለስ ቀንቷቸው በደርግ ጊዜ ቀበሌ የሰጣቸው ነው። አነስተኛ ክፍያ ለመንግስት እየከፈሉ መኝታ ክፍል ሳያምራቸው ሳሎናቸውን መኝታ አድርገው የገቢ ምንጫቸው አድርገውታል።

ቤቱ ለደህንነታቸው ሲባል በግርግዳ የተለየ ሲሆን፤ የራሱ የሆነ በር አለው። ክፍሉ ግን እጅግ ጠባብ የሚባል ነው። በአንዱ ክፍል የሚሆነው በሌላው ክፍል በቀላሉ ይሰማልና እንቅልፍ ይናፍቃል። ምንም ምርጫ የላቸውምና ገቢው የቤተሰቡን ጉሮሮ የሚሞሉበት እንጀራቸው ሆኗል። አሁን ወይዘሮዋ ምንም ሥራ የላቸውም፤ ጉልበታቸውም ቢሆን ደክሟል። ምርጫ ባይኖራቸውም መፍትሄ ይሆነኛል ያሉትን ተግባር እየከወኑ ነው።

አልጋ ኪራዩ ልክ እንደ አውቶቡስ ተራው ‹‹ኬሻ በጠረባ›› ይሉት አይደለም። ከወለል ያለፈ አልጋን ብቻ የያዘ ኪራይ ነው። ስለዚህም በዝቅተኛ ዋጋ ማለትም በ30 ብር አንድ ሰው አንድ አልጋ ይዞ ማደር እንዲችል አድርገው ገቢ እያገኙ የሁለቱን ልጆች ወጪና የዕለት ምግባቸውን ይሸፍናሉ። ተደራራቢ ቆጡ በG+8 ድረስ ያለ ሲሆን፤ ክፍያው እንደ ከፍታው ይለያያል። ከፍ ካለው ቆጥ ላይ የሚተኛ ሰው ከፍ ያለ ዋጋ መክፈል ይጠበቅበታል። ምክንያቱም ለመሰረቅና በቀላሉ ፣ ለአደጋ ለመጋለጥ አይመቻችም።

ወይዘሮ ገበያነሽ አልጋ ሲያከራዩ ተመራጭ ናቸው። ልክ በትላልቅ ሆቴሎች እንደሚደረገው ‹‹ዕቃዬ ይሰረቃል›› የሚል ስጋት ያለው ሰው ንብረቱን ለሪስፕሽን እንደሚያስረክበው በሃዲድ መንደርም ስጋት የገባው ሰው ንብረቱን ለወይዘሮ ገበያነሽ አስረክቦ ያለስጋት እንቅልፉን ይለጥጣል።

ወይዘሮ ገበያነሽ በብዙ ነገር ተፈትነዋል፤ የሰዎችን የችግር ጥግ አይተዋል። በዚህም አልጋ ሲያከራዩ የልጆቻቸው ስቃይና የቤተሰባቸው የኑሮ ሁኔታ ፊታቸው ድቅን ይላል። ስለዚህም ተከራዮቻቸውን ምንም እንኳን ዘመኑ ሰው ለሰው የሚተማመንበት ባይሆንም እርሳቸው ግን በጎነት ይከፍላል ብለው ስለሚያምኑ ልክ እንደቤተሰባቸው አድርገው ነው የሚቀበሉት። በዓል ሳይቀር ያላቸውን አብሮ በመቋደስም ነው የሚያሳልፉት።

ከዚያም ከፍ ሲልም በቤት አዳሪዎቹ የተለያዩ ሰዎች በመሆናቸው መጥፎ ጠረኖች እንዳያስቸግራቸው በቂ ውሃ ያቀርባሉ፤ ካልሲያቸውን የሚያጥቡበት፤ እግራቸውን የሚታጠቡበት ሳሙና ጭምር ይሰጧቸዋል። አልጋ ተከራዮቹ የሚመጡበት ሰዓት የተወሰነ ሲሆን፤ ወደ አልጋ የመግቢያ ሰዓት እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ብቻ ነው። ሆኖም የተቸገረና የሚያውቁት ሰው ከመጣ ቦታ ካላቸው ይከፍቱለትና ከመንገድ ላይ አዳር ይገላግሉታል።

የወይዘሮ ገበያነሽ ደግነት በዚህ ብቻ አያበቃም። ላርፍድ ያለ ሰው እስከ ሁለት ሰዓት እንዲተኛ ይፈቀድለታል። ኑሯቸውንና ጎዶሏቸውን ለመሙላት ሲሉ መክፈል ላልቻለ ሰው ከልጆቻቸው ጉሮሮ ቀንሰው የሚያድርበትን እድል ይሰጣሉ። ምክንያቱም በእርሳቸው ልምድና እምነት ‹‹ቤት የእግዚአብሔር ነው›› እኛም የብርቱዋ እናት ደግነት ለሁሉም፤ ብርታት ጽናታቸውም ለሴቶች ተምሳሌት ይሁን ! እንላለን። አበቃን፡፡

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**

"እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!"

# "የሴት ልጅ ስለሆንኩ አሁን የደረስኩበት ስኬት ላይ ደርሻለሁ"

\- ወይዘሮ መቅደስ ገብረወልድ

**አስመረት ብስራት**



ወላጅ አባቷን በህፃንነት እድሜዋ አጥታለች። በዚህም እናቷ ከጉሊት ንግድ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ነበር እርሷንና ሌሎች ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት። ይህም ሆኖ እናቷ ቀን በሥራ ውለው የማታ ትምህርት በመማር ከልጆቻቸው እኩል ክፍል እየቆጠሩ ለከፍተኛ ውጤት በቅተዋል። ይህ ደግሞ ልጆቻቸውን በማሳደጉ በኩል የተሻሉ አድርጓቸዋል፡፡ ከስድስት ልጆች መካከል የመጨረሻዋ ልጅ ነበረች መቅደስ ገብረወልድ። "እናቴ አርአያዬ ነች" የምትለው መቅደስ ለእያንዳንዱ እርምጃዋ እናቷ ትልቁ መሰረቷ ናቸው፡፡ የስኬት መንገድ ልክ ብሎም ከፍታን አይታባቸዋለችና፡፡

እናቷ ከመንገድ ላይ የጉሊት ንግድ ተነስተው ሕይወታቸው እስካለፈበት ቀን ድረስ በኢ.ሲ.ኤ ሰራተኝነት አገልግለዋል። ለትምህርት ከፍተኛ ግምት የነበራቸው እኚህ እናት ልጆቻቸው በትምህርት ለውጥ እንደሚያመጡ በማመን ሌት ከቀን ይለፋሉ፡፡ በዚህም ልጆቻቸው በሙሉ በትምህርት የተሳካላቸው ሆነዋል።

በታላላቆቿ መካከል ማደጓ ቤት ውስጥ ያሉ ችግሮች እንዳይታወቃት ያደረጋት መሆኑን የምትናገረው መቅደስ፤ እናታቸው "የሴት ልጅ እንዳትባሉ" በማለት በስነ ምግባር እንዲመሩ አድርገዋቸዋልና ለዛሬ ስኬት በቅታለች፡፡ የመጀመሪያም ሁለተኛም ደረጃ ትምህርት ላይ ውጤታማ ከነበሩት ተማሪዎች መካከል መቅደስ ተጠቃሽ ሆናለችም።

የመቅደስ ጭንቀት የጀመረው የስኬት መሰረቷ የሆኑት እናቷ ገና ዩኒቨርሲቲ ስትገባ በጉበት ካንሰር ሲታመሙ ጀምሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እናት ይህንን ህመማቸውን አብራ ውላ አብራ የምታድረውን የመጨረሻ ልጃቸው ማሳየት አይፈልጉም፡፡ እንዳትጨነቅ ህመማቸው ምንም እንኳን ከባድ ቢሆንም ቻል ያደርጉት ነበርም፡፡ ሆኖም እስከመጨረሻው ህመማቸውን ማፈን አልቻሉም። «የፈሩት ይደርሳል...» እንደሚባለው ሆነና ላይመለሱ አሸለቡ፡፡

ይህ ጊዜ ለትንሿ መቅደስ እጅግ ከባዱ ነበር፡፡ ምክንያቱም የእናቷን ሃዘን በቀላሉ መቋቋም አልቻለችም፡፡ በወቅቱ ከፍተኛ ህመም ውስጥም ገብታ እንደነበረና ለሁለት ዓመታት በከባድ ስቃይ ውስጥ ቆይታ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገና ለመኖር ትግል መጀመሯን ታስታውሳለች፡፡

መቅደስ ዳግም እራሷን አረጋግታ እናቷ ይሏት የነበሩትን ተግባራት ለመከወን ትጥርም ጀመር፡፡ አንዱ "የሴት ልጅ እንዳታስብሉኝ..." የሚለው ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ስድብ የሚመስል አባባል እርሷ ሕይወትና ኑሮ እንዲሁም ስኬት አድርጋው ለሌሎች አርአያ ለመሆንም ታተረች፡፡ ለእናቷ ነፍስ ማረፍም ስኬቷን አማራጭ አደረገች፡፡ በማርኬቲንግ ማኔጅመንት የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በጥሩ ውጤት ያዘችም።

ከዲግሪው በኋላ ኮተቤ አካባቢ በሚገኝ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር የሥራ ዓለምን አንድ ብላ ጀመረች። በመቀጠል ሌላ ፒያሳ አካባቢ የሚገኝ አንድ የመንግስት ትምህርት ቤት አንድ ዓመት አስተማረች፡፡ ይህ ቦታ ግን ለእርሷ ሌላ ትምህርት የሰጣት ነው፡፡ ምክንያቱም የምትሰማቸው የድህነት ታሪኮች እጅግ ልብ የሚሰብሩ ናቸው፡፡ መቋቋም የሚችሉት አይነትም አይደለም፡፡

በአንድ ጎኑ የማታውቀውን የሕይወት ውጣውረድ ብታይበትም በአንድ በኩል ግን በየቀኑ የምታዝንበትን ነገር እንዲገጥማት አድርጓታል፡፡ ስለዚህም ከዚያ ወጥታ ሌላ የመንግስት ትምህርት ቤት ለመቀየር ወሰነች፤ አደረገችውም፡፡ ነገር ግን እዚያም ቢሆን የተለየ ታሪክ አልገጠማትም፡፡ የችግሩ መጠን መልኩን ቀይሮ አገኘችው እንጂ።

አዲሱ ትምህርት ቤቷ አንድ የእርዳታ ድርጅት የሚያግዛቸው ኤች አይቪ ፖዘቲቭ የሆኑ ህፃናት ያሉበት ነው፡፡ ስቃያቸው ከባድ ነበር፡፡ እጅግ በጣም ያሳዝናሉ፡፡ ሁሌም በእንባ ታጀባ ታናግራቸዋለች። ግን ይህ መፍትሄ እንዳልሆነ ታውቃለች፡፡ እናም የማህበረሰቡ ችግር እጅግ ሰፊ መሆኑንን ተረድታ አባይን በጭልፋ ቢሆንባትም ነገሩ የራሷን አሻራ ለማሳረፍ ወሰነች፡፡

አንድ አራት ኪሎ አካባቢ ያለ ህፃናት ላይ የሚሰራ ገብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ በመሆንም መስራት ጀመረች። በዚያም ልጆቹን ቤት ለቤት በመሄድ መመልከት ብሎም ከወላጆቻቸው ጋር የሚያገናኝ አይነት ሥራ መከወኗን ቀጠለች። ድርጅቱ አዲስ አበባ አራት ኪሎ አካባቢ የነበረ በመሆኑ አራት ኪሎ ላይ ያለውን የድህነት ጥግ ማየት፤ ልጆች ያለባቸውን ችግሮች የመመለከት እድል ሰጣት።

መቅደስ በዚህ ሥራዋ ሌላም ገጽታ ያለው ችግርን ተመልክታለች፡፡ ከሁሉ በላይ የሚያሳዝናት ልቧን ያደማው ግን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሆነው ማታ ማታ ገቢ ለማግኘት በሴተኛ አዳሪነት ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁሉ በተለያዩ በሥራና በሕይወት ልምድ የተመለከተችው ነገር የሕይወት አቅጣጫዋን ወደ አንድ መስመር እንዲያመራ ይቃኘው ጀመር።

«ሲሲ ኤፍ ካናዳ» የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ በመቀጠር በመላው ኢትዮጵያ በመዞር የሚሰሩ ሥራዎችን የመመልከት እድል አገኘች። በዚህም ከአዲስ አበባ የበለጠ ፍፁም ድህነት የሚታይባት አንድም የኢትዮጵያ ክፍል አለመኖሩን ተመለከተች፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ድህነት በዚህ ልክ ከሆነ የሀገራችን ሀብታሞች ምን እያደረጉ ነው፤ ይህ ሁሉ ህብረተሰብ በድህነት የሚማቅቀው የሚለውን የወስጧን ጥያቄ ለመመለስ የሀብታሞች መወያያ ነው ወዳለችው አንድ በአዲስ አበባ ውስጥ ያለ ትልቅ ሆቴል ተቀጠረች።

በሆቴሉም ለዘጠኝ ወራት በነበራት ቆይታ ያለ ምንም መሳሳት በአንደ ቀን እስከ 100 ሺህ ብር የሚከፍሉ ሀብታሞች መቶ ብር አጥተው መንገድ ላይ ከሚንጠራወዙት ድሆች ጋር ማነፃፀር ከአዕምሮ በላይ ሆኖባት፡፡ ሌላ የሥራ አማራጭ መፈለግ ጀመረች። ይህም በኤዩ ስር ያለ የጉድ ገቨርነንስ ዲፓርትመንት የሚመራ ድርጀት ላይ ጣላት፡፡

የአፍሪካ 2063 አጀንዳ እንዴት ተግባራዊ ሆኖ ሀገርን መቀየር ይቻላል በማለትም ማሰብ ጀመረች። በዚህም ሀገሪቱ በርካታ ወጣቶች በተለይም ሴቶች የሞሉባት ሀገር በመሆኗ እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ለማገዝና እነርሱ ላይ ሰርቶ ለውጥ ለማምጣት ብዙ የሚያዳግቱ ነገሮች እንደሌሉ አምናም ሥራ ጀመረች፡፡

በዚህ መካከል በእንግሊዝ ሀገር ሁለተኛ ዲግሪዋን ሊዲንግ ኢኖቬሽን ኤንድ ቼንጅ በሚል ትምህርት መስክ የያዘችው መቅደስ፤ ትምህርቱን ለመማር ያነሳሳት የኢትዮጵያዊን ችግር ምን ላይ እንደሆነ በመመልከት፤ የተቋማት ባህልን፤ የስራ ባህልን፤ በአጠቃላይ ያለውን የባህል ለውጥ በማጥናት "አሻጋሪ" የሚባል ድርጅት በማቋቋም ለመስራትም ነው፡፡ በዚህም ሀሳቧ ተፀንሶ "አሻጋሪ" የሚባል ተቋም ተወለደ፡፡

ትውልድን ከአንዱ ወደ አንዱ በመለወጥ ሀገርን የማሻገር ሀሳብ ያለው ነው፡፡ ትወልዱ የሚሻገር አስተሳሰብ እንዲያመጣ የአቅም ግንባታ ላይ ይሰራልም። በድርጅቱም የተለያዩ አይነት ትምህርቶችን ለመሪዎች መስጠት ጀመረች። "መሪነት ሲባል ራስን መርሳት ማለት ነው ለሕዝብ መኖር ማለት ነው›› ብሎ የሚያምን ዜጋ መፍጠር ነው፡፡ እኔ መሪ የሆንኩት ለምድነው? ለመሪነት በመጣሁበት መንገድ ልክ ነው ወይ? ሕዝቡን እያገለገልኩ ያለሁበት መንገድስ በሕዝብ ዓይን እንዴት ይታያል? የሚለውን ጥያቄ የሚመለስ መሪን እንዲሁ ለመፍጠር የሚያስችል ነው፡፡ በዚህም በርካቶችን የማሰልጠን ሥራ ሰርቷል ትላለች መቅደስ።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፐብሊክ ሰርቪሰና የሰው ሀብት አስተዳደር ቢሮ ጋር በመሆን ወደ 50ሺህ ሰዎችን ለማሰልጠን የቻለው ድርጅቱ፤ በስልጠናውም የመንግስት ሰራተኞችን ችግር በመፍታት ውጤታማ አገልጋዮችን ለመፍጠር እስካሁን ድረስ ስምንት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ለመድረስ እንደቻሉ ታብራራለች።

"‹እናቴ ለልጆቼ እዳ ጥዬ አልሄድም› በማለት ቤት ለመስራት እንኳን ዓመታትን ጠብቃለች። እኛም ለትውልደ እዳ ጥለን እንዳንሄድ በየተሰማራንበት ዘርፍ በቂ ስራን መስራት ይኖርብናል" ብላ የምታምነው መቅደስ፤ አሁን ሦስተኛ ዲግሪዋን በሚዲየሽንና ኮንፍሊክት ሪዞልሽን የትምህርት መስክ እየተማረች ትገኛለች፡፡ እስካሁን መሪዎችን በማሰለጠን ብትቆይም አሁን ላይ ማህበረሰብ ለማህበረሰብ፣ ቤተሰብ ለቤተሰብ እንዴት ተግባብቶ መኖር እንዳለበት ግራ የተጋባበት ዘመን ላይ ያለን በመሆኑ ይህን ችግር መፍታት ትፈልጋለች፡፡

ሌላው ዲፕሎማሲ በሚባል ትምህርት በዩናየትድ ኔሽን በተሰጣት የትምህርት እድል ጀኔቫ ላይ እየተማረች መሆኑንና ዘንድሮ እንደምትጨርስ፤ እስከ ዛሬ 135 ሺህ ሰዎች በላይ ስልጠና እንደሰጠችና ለ146 ሴቶች የስራ እድልን እንደፈጠረች የነገረችን መቅደስ፤ የእራሳችን የሆነ እሴትን በመጠቀም ችግሮቹን ተነጋግሮ የሚፈታበት መንገድን ማስተማር፤ ወጣቱ ላይም የተለያዩ አጋጣሚዎችን ተጠቀሞ ማን እንደሆነ ማሳየት፤ ባህሉን ወጉን ሳይረሳ የዘመኑ ጀግና የሚሆንበት አካሄድ እንዲከተል ማነቃቃት ላይ የተለያዩ ሀሳቦች በማንሳት ለወጣቱ ለመድረስ እየሞከረች ነውም፡፡

መቅደስ እንደምትለው፤ ስልጠናዎቹ እንደ ሰልጣኞቹ ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ፡- መሪዎች ሲሰለጥኑ እንዴት የሚመሩትን ተቋም መምራት እንዳለባቸው፤ እንዴት ሰራተኞችን ማስተናገድ እንደሚችሉ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ «ኮቺንግ» የተባለ ስልጠና ነው የሚወስዱት፡፡ ከዚያ ውጭ ወጣቶች ጋር ሲሄዱ ደግሞ ምን መሆን እንደሚፈልጉ፤ ምን መስራት እንደሚሹ ስለማያውቁ ያንን መምራት፤ ዓይን የሚከፍቱ ፕሮግራሞችን በማካተት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል።

በወጣቶች ስልጠና ላይ ደግሞ ሕይወትን እንዴት መምራት እንደሚችሉ፤ ራስን ማክበር ላይ፤ ጓደኝነትን መምረጥ ላይ፤ የተለያዩ ጥያቄዎቻቸውን መመለስ ላይ ትኩረት ያደረጉ ሀሳቦች ይነሳሉ። አሁን ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመፈራረም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ ዜጎች በስነ ምግባር የታነጹ እንዲሆኑ፤ ራሱን የሚያውቅ ትውልድ እንዲያፈራ እየተሰራ ይገኛል።

ሴቶች ላይ የሴቶች ዋጋን በአግባቡ ተረድተው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማስቻል ላይም እንደሚሰሩ የገለጸችው መቅደስ፤ ከሴቶች ጋር የስራ እድል ፈጠራን ለሴቶች ብቻ እየተሰጣቸው ቤተሰብን የሚመሩ ሴቶችን የማፍራት ሰፊ ተግባርም በአሻጋሪ ድርጅቱ አማካኝነት እየተከናወነ እንደሆነም ነግራናለች፡፡ አሁን ላይ በድርጅቱ ትኩረት ተሰጥቶት ከሚሰራው ስራ መካከል መልካም ወላጅነት ምን ይመስላል የሚል ሀሳብ ያለው ስራ ነው።

"ትውልድ የሚሰራው ከቤት ነው። ለእያንዳንዱ ትውልድ መንሻፈፍ ተጠያቂው ደግሞ ቤተሰብ ነው። የአሁን ጊዜ ወላጅ ስለ አበላ ስለ አጠጣ ምንም ስላላጓደለ ልጁን ያሳደገ ይመስለዋል። ልጅ ዝም ብሎ ቤት ቁጭ ሰላለ ጨዋ አይደለም። በዚህ በቴክኖሎጂ ዘመን ሁሉን ነገር እጃቸው ላይ ያገኙታል" የምትለው መቅደስ፤ ልጆችን ለማሳደግ መልካም አስተሳሰብ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ወላጅ ሊረዳው ይገባል። ልጅ የተዘራበትን ነው የሚያበቀለው፤ ምንም ያልተዘራበት ልጅ ወጥቶ ምንም አይሰራም።፡ ስለዚህ ቤተሰብ ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ መስራት እንዳለበት ትመከራለች፡፡

ድርጅታቸው ለታዳጊዎችም ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን፤ ይህም ከአስራ ሶሰት ዓመት በላይ የሆኑ ልጆችን የሚያካትት ነው፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ የሚሰለጥኑበት ሁኔታ ተመቻችቷል። ሌላው በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በኩል መምህራንን በማሰልጠን ተማሪዎቻቸው ጋር እንዲደርሱ የማድረግ ስራ እየሰሩ ነው፡፡

"ትውልዱ በጣም ከመፍጠኑ የተነሳ ያውቃል ተብሎ የማይታሰበውን ነገር በቀደመ እድሜ ሊያወቅ ችሏል። ልጆች በእውቀት፣ በማንነት መሰራት የሚገባቸው እድሜ ላይ የሌሎች ባህል ተፅእኖዎች ስር ወድቀዋል። ይህንን የማስተካከል ሀላፊነት ደግሞ የወላጅ ነው" ትላለች መቅደስ፡፡

እኛ ቤተሰቦቻችን የመከሩንን የመሩንን መንገድ ተከትለናል፡፡ ልጆቻችንም የእኛን ፈለግ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘመኑ የሚመጥነውን የእድገት ደረጃ ማሳየት ያለብን እኛ ነን፡፡ በጥበብና በማስተዋል ልናሳድጋቸው ያስፈልጋል፡፡ ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ድረስ ያለው እድሜያቸው ደግሞ ለዚህ ስኬታችን ጥሩ አማራጭ ነው፡፡ ስለዚህም በመመከር ሳይሆን አርአያ ሆነን በማሳየት ማሳደግ አለብን ባይ ናት።

ልጆች ከ12 ዓመታቸው በኋላ ምክር ይሰለቻቸዋል። ከዚያ ይልቅ የሚፈልጉት መሞከርን ነው፡፡ ወላጅን መስማት ትተው ጓደኞቻቸውን ማዳመጥ ይጀምራሉ። እናም በቀላሉ ለመመለስ እንቸገራለንና በእድሜያቸው ልክ እናሳድጋቸው፡፡ ወላጅ መናገርን አቁሞ ማዳመጥና እንደ ጓደኛ ነገሮችን የማስረዳት ጊዜ ላይ መድረስ አለበት ትላለች።

ይህ ጊዜ ለልጆች ሀሳባቸውን የሚከፋፍል ነገር የሚበዛበት ነው፡፡ እናም በትምህርታቸው ዝቅ የሚሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስለዚህም ይህንን በመረዳት የጥበበኛ ወላጅ ሚናን መወጣት ይገባናልም ስትል መልዕክቷን ታስተላልፋለች፡፡

ልጆች 16 ዓመታቸው ላይ ሲደርሱ በችኮላ ሁሉንም ነገር ማግኘት ይፈልጋሉ፤ ቶሎ ያስቡበት ላይ መድረስን ይሻሉ። ስለሆነም ከቤተሰባቸው ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እናም በትኩረት ሁኔታቸውን እየተመለከቱ መከታተልና መምራት ተገቢ ይሆናል በማለት ታስረዳለች።

ወላጅነት ማልበስ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ልጆችን አዳምጦ በትክከለኛው መንገድ መምራት ግዴታው ነው። ትውልድ ሳያመልጥ ለመመለስ የሚያስችለውን እያንዳንዱን ተግባር ማከናወን አለበት፡፡ ለስኬትም ሆነ ለውድቀቱ ዋናው የወላጅ ተግባር ነውና ከወለዱ በኋላ የልጅን ፍላጎት በመከተል ማስተካከል ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይገባዋል የማሳረጊያ መልዕክቷ ነው። አዎ ወላጆች የልጆች መሪ ናቸውና እንዲሆኑላቸው የሚፈልጉትን ሆነው በማሳየት ሊመሯቸው ይገባል በማለት ሀሳባችንን ቋጨን፡፡

“እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**





# ሙኒባ ማዛሪ የጥንካሬ ተምሳሌት

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ፈገግታ የዘወትር ስንቋ የውስጣዊ ሰላሟ ነፀብራቅ ነው:: በራስ መተማመኗ የአንድን ትልቅ አገር ህዝብ በንግስና ዙፋኗ ላይ ሆና የምታስተዳድር ንግስት እንጂ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጠች መሆኗን ያስረሳል:: ለዓለም ሁነቶችና ፈተናዎች ያላት በጎ አመለካከት እና ምላሽ ተኝቼ ስነሳ እሷን ሆኜ በነቃሁ ያስብላል::

አካል ጉዳተኛ መሆኗ ዳግም እንድትፈጠር እንድትወለድ አደረጋት እንጂ ከወደቀችበት ከቲቢያ እንድትቀር አላደረጋትም:: በተሽከርካሪ ወንበር ላይ መቀመጥ መቻልና ፈተናን አሸንፎ መኖርን በብዙ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ እንድትቀርፅ አደረጋት እንጂ መራመድ አለመቻሏን እንድታስብ አላደረጋትም:: ሚሊዮኖችን ባነቃቃችበት አንድ ንግግሯ የህይወትን ጎምዛዛ ገፈት የተጎነጨችበትን ግን ደግሞ ለዛሬ ማንነቷና ለገነባችው ጥንካሬ መሰረት የሆነን ክስተት ትተርካለች:: ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጣ ለአዳራሽ ሙሉ ህዝብ በወደቁበት ሳይቀሩ ይበልጥ ጎልቶና ጎልብቶ አንፀባርቆ የመነሳት ስነልቦናዊ ጥንካሬን ታጋራለች:: ሙኒባ ማዛሪ ፓኪስታናዊቷ ብረቷ እመቤት!

“እነሱ አካል ጉዳተኝነቴን ነው የሚመለከቱት፤ እኔ ደግሞ መቻሌን ነው የማየው፤ በህይወታችሁ ውስጥ የሚያጋጥሙ አንዳንድ ክስተቶች አሉ:: እነዚህ ክስተቶች ሊሰብሯችሁ ይችላሉ፤ ቅርፀ ቢስ ሊያደርጓችሁም ይችላሉ ግን በተሻለ አቅጣጫ ይቀርጿችኋል” ትላለች:: በሷም የሆነው ይህ ነው፤ ባል ስታገባ ገና የ18 ዓመት ወጣት ነበረች:: የትዳሯ መነሻም አባቷ ነበር:: አባቷ እንድታገባ ያለውን ፅኑ ፍላጎት የተመለከተችው ሙኒባ ‹‹የኔ ማግባት አባቴን የሚያስደስተው ከሆነ ይሁን›› በማለት የትዳርን ዓለም ተቀላቀለች:: ነገር ግን እንዳሰበችው ትዳሯ አባቷን አስደስታ እሷም ደስታን የምታገኝበት አልሆነላትም::

ካገባች ከሁለት ዓመት በኋላ ከፍተኛ የሆነ የመኪና አደጋ ደረሰባት:: “በአንደኛው በኩል ባለቤቴ ተኝቶ ነበር፤ መኪናዋ ወደ ገደል ተገለበጠች:: ባለቤቴ ከመኪናዋ ውስጥ ዘሎ በመውጣት እራሱን አዳነ:: በዚያ ደግሞ ደስተኛ ነኝ:: እኔ ግን መኪናዋ ውስጥ ቀረሁ” ትላለች ስለአደጋው ስታስረዳ:: በአደጋው ብዙ የሰውነቷ ክፍል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባት:: ወገቧ ተሰበረ፣ ትከሻዋ ውልቃት ገጠመው፣ ደረቷም ከፉኛ ተጎዳ፣ ሳንባዋና ኩላሊቷ አደጋ አገኛቸው:: መተንፈስ አቃታት፤ እናም ሆስፒታል ገባች:: ለሁለት ወር ተኩል ያህል ጊዜ የሆስፒታሉ አንድ ክፍል ውስጥ ተኛች፤ በርካታ ቀዶ ጥገናም ተደረገላት:: ያች ቀን ቀሪ ህይወቷን በሙሉ ፓራላይዝ እንድትሆንና በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆና እንድትንቀሳቀስ ምክንያት ሆነች::

ሆስፒታል በነበረችበት ባንዱ ቀን ዶክተሩ ወደሷ በመሄድ፤ “አርቲስት መሆን እንደምትፈልጊ ሰማሁ ነገር ግን መጥፎ ዜና ይዤልሽ ነው የመጣሁት” አላት:: “ከዚህ በኋላ ስዕል መሳል አትችይም ምክንያቱም ወገብሽ እና እጅሽ ክፉኛ ተጎድቷል” በማለት አረዳት:: በቀጣዩ ቀን ዶክተሩ አከርካሪዋ ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ መሆኑንና ከዚህ በኋላ መራመድ እንደማትችል ነገራት:: ከዚህ ሁሉ የከፋውና የሙኒባ ማዛሪን ስነልቦና የጎዳው “ከዚህ ጉዳትሽ የተነሳ




ከዚህ በኋላ መውለድ አትችይም” የሚለው የዶክተሩ ቃል ነበር:: “ያን ቀን ሙሉ ለሙሉ ጠፋሁ፤ እናቴን ‹‹ለምን በኔ?›› ብዬ ጠየኳት:: ያን ቀን ስለህልውናዋና ስለመኖሯ ትርጉም መጠየቅ ጀመረች::

“ይህም ያልፋል፤ ፈጣሪ ላንቺ ትልቅ እቅድ አለው” የሚለው የእናቷ ቃል የዳግም መፈጠሯ፤ ከወደቀችበት የመነሳቷ መሰረት ሆነ:: ከሁለት ወር በኋላ ከሆስፒታል ወጣች፤ ሁለት ዓመት በቤት ውስጥ ከአልጋ ሳትነሳ በመስኮቷ በኩል ውጪ ውጪውን አሻግራ እየተመለከተች በአንድ ክፍል ውስጥ ተወስና ቆየች:: የወፎቹን ድምፅ ብቻ እየሰማች የአልጋ ቁራኛ ሆና ከረመች:: በተኛችበት ክፍል ሆና አንድ ቀን እሷም ከቤተሰቦቿ ጋር ሆና ወደ ውጭ እንደምትወጣ፣ የዓለምን ውብ ተፈጥሮ እንደምታደንቅና ዳገት ቁልቁለቱን እንደምታይ አሰበች:: የዚህን ጊዜ ነበር ሰዎች ምን ያህል እድለኛ እንደሆኑ የተረዳችው::

የሙኒባ ቀጣይ ተግባር ፍርሃቷን መዋጋት ነበር እናም ሁሉንም ፍርሃቶቿን ማሸነፍ እንዳለባት ወሰነች:: “ትልቁ ፍርሃቴ ፍቺ ነበር፤ ከኔ ጋር ኪዚያ በላይ መቆየት የማይፈልግ ሰው ላይ የሙጥኝ ብዬ ነበር:: ፍርሃቴን ሳሸንፍ በቃ አልኩኝ:: ስለፈራሁ ነው እንጂ ምንም ማለት አይደለም አልኩኝ:: እሱን ለቅቄ ራሴን ነፃ አወጣሁ:: እናም እራሴን የጠንካራ ስሜት ባለቤት አደረኩ:: ሌላ ማግባቱን የሰማሁ ቀን የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክት ላኩለት ዛሬም እንደምፀልይለት ያውቃል” ስትል እንዴት ፍርሃቷን ማሸነፍ እንደጀመረች ታብራራለች::

ሌላኛውና ትልቁ ፍርሃቷ እናት መሆን አለመቻሏ ነበር:: ይህ ለሷ ለመቀበል የሚከብድና በትልቁ ቅስሟን የሚሰብር ነበር:: ግን በጥሞና አሰበች፤ ዓለም ላይ የሚቀበላቸው የሚፈልጉ ብዙ ህፃናት አሉ፤ ስለዚህ በምንም መልኩ ማልቀስ አያስፈልግም በማለት ወደ ህፃናት ማሳደጊያ ሄዳ አንዱን ህፃን በማደጎ ወሰደች፤ ልጅ አገኘች እንደምትመኘውም እናት ሆነች::

በተለያየ የዓለም ጥግ የሚኖሩ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን አናገኝም ብለው ያስባሉ ምክንያቱም ፍፁም በሆነች ዓለም ፍፁም ያልሆኑ እነሱ እየኖሩ ይመስላቸዋል:: ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን መጥቀም የሚችሉ ነገር ግን በሌሎች ፊት የሚኖራቸውን ተቀባይነት በማሰብ በቤታቸው የተቀመጡ ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን ፀጋ የሚያባክኑ በርካቶች ናቸው:: ሙኒባ ግን ይህ እንዲሆን አልፈቀደችም ራሷን በደንብ ብትገልፅ ከራሷ አልፋ ለሌሎች ተስፋ መሆን እንደምትችል አሰበች:: ወደ አደባባይ በመውጣት መንቀሳቀስ ጀመረች፤ ከልቧ የምትወደውንና ሃኪሟ ከዚህ በኋላ ማድረግ አትችይም ያላትን ስዕል መሳል ጀመረች:: በዚህ ብቻም አላበቃችም በፓኪስታን ቴሌቪዥን ጣቢያ በመግባት ዜና አንባቢ በመሆን መስራት ቻለች:: ባለፉት ሶስት ዓመታት በርካታ የቴሌቪዥን ሾዎችን አዘጋጅታለች::

ሙኒባ ስኬታማነቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቀጠለ፤ ለፓኪስታን ዩን ውሜን የመልካም አርአያ አምባሳደር በመሆን ተመረጠች:: ለሴቶችና ለህፃናት መብት ትናገራለች፤ ድምፅ ላጡ እህቶቿ ድምፅ በመሆን አጋርነቷን ታሳያለች:: ሁሌም ወደ አደባባይ ስትወጣ ፊቷ ላይ ትልቅ ፈገግታ አለ፤ ሰዎች የዚህ ፈገግታዋ ምንጭ ምንድነው? በማለት ይጠይቋታል:: ሙኒባ ግን ሁሌም መልሷ፤ “ስላጣኋቸው ነገሮች መጨነቅ ስላቆምኩ፤ ስላጣሁት ጤና፣ ሰው መጨነቅ ስላቆምኩ ነው” በማለት ምላሽ ትሰጣለች::

‹‹አንዳንዴ ከህይወታችሁ አንዳንድ ነገሮች ሲቀነሱ የተሻለ ሰው ሊያደርጓችሁ ይችላሉ:: ሁሌም ሁሉም ነገር የሚሆነው ለበጎ ነው:: ሙሉ ህይወታችሁን ኑሩ ፤ ራሳችሁን ተቀበሉት ለራሳችሁ ፍቅርን ስጡ፤ ራሳችሁን ውደዱ ያኔ ነው ሌላ ሰው የምትወዱት ህይወት ከባድና አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ እነዚያ ሁሁ ነገሮች ግን እናንተን ነው ጠንካራ የሚያደርጉት:: ራሳችሁን ስትቀበሉት ዓለምም እውቅና ይሰጣቿኋል፤ ሀሉም የሚጀምረው ከራስ ነው” በማለትም ሙኒባ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ለሰዎች መልዕክቷን ታስተላልፋለች::

ሙኒባ ማዛሪ ከ15 ዓመት በፊት በወጣትነቷ በደረሰባት የመኪና አደጋ ዘመኗን ሙሉ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ የምትቀመጥ አካል ጉዳተኛ ሆናለች:: የእናቷ ቃላት ግን ቃላት ብቻ ሆነው አልቀሩም፤ ሙኒባ ማዛሪ ዛሬ በመላው ፓኪስታን የምትወደድ አርቲስት ለመሆንዋ እርሾ ሆነዋታል:: የመጀመሪያዋ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጠች ሞዴልም ተብላለች:: በርካታ የቴሌቪዥን ሾዎችን አዘጋጅታለች፤ ከዚያም ባሻገር በፓኪስታን ብሄራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ዜና አንባቢ ሆናም ትሰራለች:: አነቃቂ ንግግር እንድታደርግ በየመድረኩ ትጋበዛለች:: ሙኒባ አሁን ሁሉም ሊሰማት እና የሷን ጥንካሬና ተስፋ ያለመቁረጥ ፅናት ለመጋራት የሚሻማባት በአነቃቂ ንግግር የሰዎችን የመኖር ፍላጎት ከፍ የምታደርግ የፓኪስታን እንቁ፤ ፈተና እንደወርቅ በእሳት የፈተናት የዓለም መሰናክል ያልበገራት የማትፈርስ አለት ናት::

እ.ኤ.አ 2015 ዓ.ም ቢቢሲ ከመቶ አነቃቂ ሰዎች አንዷ ሲል መርጧታል:: የፓኪስታን ብሄራዊ ዩን ውሜን አምባሳደር ተብላ ተሰይማለች:: በ2016 ፎርቢስ ከ30 ዓመት በታች ያሉ 30 የዓለማችን ምርጦች በሚለው ዘርፍ አንዷ አደረጋት:: በ2019 ዓ.ም የያኔው የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሚር አንከሃን የፓኪስታን ብሄራዊ የወጣቶች ምክር ቤት አካል አደረጓት:: እ.ኤ.አ2017 ዓ.ም በሰርቢያ የካሪክ ወንድማማቾች ሽልማት ተቀበለች:: ይህንን ሁሉ ስኬት የተጎናፀፈችው በደረሰባት አደጋ አካል ጉዳተኛ ሆና ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ከተገደደች በኋላ ነው:: ዛር ሙኒባ ማዛሪ ሚሊዮኖች የሷን ንግግር ለመስማት የሚሰለፉ ሊያይዋትና ሊያደንቋት የሚሹ የ35 ዓመት ሴት ሆናለች::

# ፍርድ ሰጪ እጆች

**በዳግማዊት ግርማ**

እትመት አሰፋ ትባላለች። ከአስመራ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛነት የተደረገ የስኬት ጉዞ ባለቤት ናት። እሷና ባልደረቦቿ የሰጡት ውሳኔ የአገሪቷ ህግ ሆኖ ይጸናል።

መጠቃት ሞቷ ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ ነበር ከዚህች ዓለም ጋር የተዋወቀችው፤ ጓዳ ጎድጓዳዋ በአስመራ መንደሮች መሀል ተደብቋል። የእውቁ ደራሲ የበዓሉ ግርማ ገጸ ባህሪ የሆነችው የፊያሜታ ጊላይ መብቀያ የድምጻ መረዋዎቹ ጸሀይቱ ባራኪ እና የየማነ ባርያው ሀገር ኤርትራ መዲና አስመራ የእትብቷ መቀበርያ ስፍራ ነው። የመኖር ጅማሬ መነሻዋ ምድርን መቀላቀያ ስፍራዋ አስመራ ናት። ዳኛዋ እትመት ከፍተኛ የሆነ የራስ መተማመን ያላት እና ያመነችበትን ነገር በግልጽ የምትናገር ቀለል ያለች ሴት ነች።

መብትን ለማስከበር መነሳት ለሰዎችም ለራስም ፍትህ ዘብ መቆም መለያዋ ነው፤ ሁሉም ሰው በስነ ስርዓት መመራት ህግም መከበር አለበት ባይ ናት። ዳኛ እትመት አሰፋ በሀገሪቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የህግ ሰውነት ያለው ተቋም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ናት። በእጇ የጨበጠችው የፍትህ መዶሻ የእልፍ ‹‹ከኔ በላይ ማን አለ›› ባዮች ትዕቢትን አዶልዱሟል። የፍትህ በትሯ ለብዙ ባለ እምባዎች መታበስ ሆኗል።

## የልጅነት ሕይወት፡-

ልጅነቷ ጥሩ የሚባል አይነት መልክ ነበረው። የተገኘችው መተዳደሪያ ገቢያቸው መካከለኛ ከሆነ ቤተሰብ ነው። የአባቷ ሻለቃ አሰፋ አሳምሬ ወታደራዊ ስርዓት የእርሷንና የእህት ወንድሞቿን ሕይወት በቀና መንገድ መርቷል። ወላጅ እናቷ ወይዘሮ ከበደች ደመቀም ቢሆኑ ሳይማሩ በርካታ ኃላፊነቶችን በመወጣት ለልጆቻቸው ዛሬ መድረስ ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ።

የአሁኗ ህግ ተርጓሚ በብላቴንነት ዘመኗ እልኸኛ እና ተደባዳቢ ነበረች። ጥቃት አትወድም፤ ለታናናሽ እህትና ወንድሞቿ ተቆርቋሪ ናት፤ አቻ ጓደኞቿ ከተደበደቡ የደበደባቸውን ሰው ለወዳጆቿ ተደርባ ትደበድብ ነበር። የቤት ውስጥ ስራ መስራት አትወድም፤ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቦርቃ ተጫውታ ለቤተሰብ ታዛ አድጋለች።

የአባቷ ወታደር መሆን እሷና እህቶቿን በጥብቅ ስነ ስርዓት ማሳደግ ችሏል። ጥልቅ የሙያ ፍቅር፤ ሐገር ወዳድነት፤ ሕዝብን ታምኖ በሀቀኝነት ማገልገል እና ለእውነት መታገልን ከአባቷ ወርሳለች። ከእናቷም ቢሆን የትዬለሌ ጉዳዮች ተጋብተውባታል። እናቷ ወይዘሮ ከበደች ደመቀ ባይማሩም የትምህርትን ጥቅም ከዘመናቸው ቀድመው ያወቁ ታታሪ ሴት ነበሩ፤ ባለመማራቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ተጽእኖ መሠረት በማድረግ ልጆቻቸው ተግተው እንዲማሩ ማድረግ ችለዋል። ሴቶች መብቶቻቸውን የሚያረጋግጡት በትምህርት ብቻ መሆኑን አምነው በመቀበልም ልጆቻቸውንም አሳምነዋል። ከተማሩ ደግሞ ለከፍተኛ ውጤት መሆን እንደሚገባቸው ሁሌም ይመክሯቸውም ነበር።

ዳኛዋ እስከ ዓለም ጥግ ብትኳትን ለእርሷ የእናቷን ያህል የራሱን ሕይወት ትቶ ለእርሷ ዋጋ የከፈለ አንዳች ፍጥረት የለም። በልቧ ሰሌዳ በትልቁ የተፃፈው የወላጅ እናቷ መልካም አድራጊነት ነው። እናቷ ሙሉ ጊዜያቸውን ለልጆቻቸው በመስጠት በአግባቡ አሳድገው አስተምረዋቸዋል፤ እንደውም ለዛሬ ደረጃ እንድትደርስ ትልቁን ድርሻ የወሰዱት እናቷ ናቸው፤ ለዳኛዋ እትመት እናቷ በእጅጉ ዋጋ በመክፈላቸው ሳይማሩ ላስተማሯት እናቷ ምስጋናዋ የበዛ ነው። ባሉበት በሰማዩ ዓለም ‹‹ደግ ይግጠምሽ፤ አፈሩ ይቅለልሽ›› ብላም በሞት ለተለዩአት እናቷ ደግ ደጉን ተመኝታለች።

የሕይወት መርኋ ሕሊና ምን ይላል የሚለው ነው። በእንግሊዝኛው / morale value / ጥሏም ንግግሯም ከህሊናዋ ነውና ለምትሰራቸው ስራዎች ብቸኛ ዳኛ አድርጋ የምትሾመው ህሊናዋን ነው።

## ትምህርትና እትመት

ዳኛ እትመት አሰፋ ከወደ አስኳላው ዓለምም ተሸላሚ ነበረች። ጥልቅ የሆነ የንባብ ልምድ ባለቤት ናት። ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ የማንበብ ልምድን አዳብራለች። የዛሬ ዳኝነቷን ያወቀች ይመስል የትላንቱ የልጅነት ልቧ ለወንጀል ታሪኮች ይማረክ ነበር። በዚሁ ጊዜም ልብ ወለድ፣ ከወንጀል ምርመራ እና ከስለላ ጋር የተገናኙ እንዲሁም የታሪክ መጽሐፍቶችን የማንበብ ልምድ ነበራት። አብዛኞዎቹ የሀገራችን እውቅ ደራሲያን የጻፏቸውን መጽሐፍቶች አንብባለች። እነኚህ መጽሐፎች አሁን ላላት ባሕርይ እና አመለካከት ትልቁን ሚናም ተጫውተዋል።

በትውልድ ስፍራዋ አስመራ በወቅቱ የትምህርት አሰጣጡ ጥሩ በተባለለት ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርቷን ተከታትላለች። ካደገች በኋላም ሙሉ የትምህርት ዝግጅቷ በሀገሪቷ አንጋፋ የትምህርት ተቋም ውስጥ ያለፈ ነበር።

ከሀገሪቷ ትልቁ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በሕግ ማግኘት ችላለች። ሁለተኛ ዲግሪዋን በሰብዓዊ መብት: በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የ ‘ Gender studies ‘ ማስተርስ ዲግሪ ተማሪ ስትሆን የመመረቂያ ጽሑፍ በማዘጋጀት ላይ ናት።



እትመት አሰፋ

> **የአባቷ ወታደር መሆን እሷና እህቶቿን በጥብቅ ስነ ስርዓት ማሳደግ ችሏል። ጥልቅ የሙያ ፍቅር፤ ሐገር ወዳድነት፤ ሕዝብን ታምኖ በሀቀኝነት ማገልገል እና ለእውነት መታገልን ከአባቷ ወርሳለች።**

## እትመትና የስራ ሕይወት

የዳኛ እትመት አሰፋ የስራ ዓለም ጉዞዋ በቀድሞ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አሀዱ ብሎ ተጀመረ። በዚሁ መስሪያ ቤትም ከ1995 ዓ.ም እስከ 2000 ዓም ድረስ ለአምስት ዓመታት በነገረ ፈጅነት አገልግላለች፤ በቀጣይም የጥብቅና ፈቃድ ለማውጣት ቻለች። ከ2000 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ጠበቃ በመሆን ለተጨማሪ አምስት ዓመታት ሰርታለች። ቀጣይ የስራ ታሪኮቿ ከዳኝነት የሚያስተዋውቁና ከስራውም በጥልቅ ፍቅር ያስተሳሰሯት ሆኑ። ከ2006 ዓ.ም መጨረሻ እስከ 2008 ዓም መጨረሻ ድረስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ሠራች። ከ2008 ዓ.ም መጨረሻ እስከ አሁን ድረስ ደግሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን በማገልገል ላይ ትገኛለች። በአሁኑ ሰዓት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 3ኛ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ናት።

የዳኝነት በጣም የምትወደው ሙያ ነው፤ ‹‹እግዚአብሔር እስከፈቀደበት ጊዜ ድረስ በከፍተኛ የሙያ ፍቅር ሥራውን እሰራለሁ ብዬ አምናለሁ›› ትላለች ለሙያው ያላትን ጥልቅ ፍቅር ስትገልጽ። የሀገሪቱ የመጨረሻ ፍርድ ቤት በሆነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውስጥ መስራት ለዳኛ እትመት ትልቅ ስኬት ነው። ከሌሎች ለመማር ዝግጁ ናት። በየጊዜው ራሷን ለማሳደግ የተለያዩ መጽሀፍትን ታነባለች። ከጊዜው ጋር ራሷን በማዘመን ወቅቱ ባመጣው ቴክኖሎጂ ትሳተፋለች። የማሕበራዊ ትስስር ገጾችን ለበጎ ዓላማም ትገለገልባቸዋለች። ራሷን ለማሳደግ እና አዳዲስ መረጃ ለማግኘትም ትጥራለች።

## እትመትና ዳኝነት

ዳኝነት በተቃራኒ ጎራ የተሰለፉ ሁለት ተፋላሚዎች በሚፋለሙበት የክርክር ሜዳ ላይ የሚከወነውን ውጊያ መምራት ነው። ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ እና ጥብቅ ተጠያቂነት ያለበት ሙያም ጭምር ነው። ይህን በመሰለ ሙያ ውስጥ በጥብቅ ስነምግባር በላቀ ትጋት እና በከፍተኛ የሙያ ፍቅር ትሰራለች። ለዚህ ሁሉ ብርታቷ የጀርባ አጥንት የምትለውና በዚህ ጥንካሬ ልክ እንድትሰራ ያስቻላት የወላጆቿ አስተዳደግ እና ሴትነት ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል የሚል እምነትም አላት።

በዳኝነት ሕይወት ሴት መሆኗ ጠቅሟታል። የሀገሪቱ የመጨረሻ ፍርድ ቤት የሆነው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ብትሆንም አሁንም ካለችበት በላይ ሩቅ ታልማለች፤ ሕልሟን እንደምታሳካም በራስ መተማመን አላት። ዳኝነት ልዩ መሰጠትን እና ከፍተኛ ኃላፊነትን ጠያቂ ነው። በላቀ ስነምግባር የሚከወን ሙያም ጭምር። ዳኝነት የልጆችን፤ የትዳርን እና የቤተሰብን ጊዜ የሚሻማ በአብዛኛው ከማሕበራዊ ሕይወት መገለልን የሚጠይቅ ሙያም ነው።

## ሴትነትና እትመት

ሴትነት ለእትመት ብዙ የእድል በሮችን ከፍቶላታል። ሴት በመሆን ውስጥ ያለውን ጸጋ አንጠፍጥፋ ተጠቅማለች። ሴትነት ውስጥ ባለው ጥንካሬ፣ ታጋሽነት፣ ውጤታማነት፣ አስተዋይነት፣ ስክነት፣ አቃፊነት፣ ደፋርነት ፣ ጀግንነት፣ ፍትሐዊነት እንዲሁም ውሳኔ ሰጭነት ዳኝነቷ የሰመረ ሆኗል።

የዚህ ሁሉ ጸጋ ባለቤቶች የሆኑ በተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የራሳቸውን ስራ የፈጠሩ፣ በንግድ የሚሳተፉ፣ የቤት እመቤት የሆኑ፣ ከታችኛው እስከ ላይኛው እርከን ድረስ በርካታ ብርቅዬ ሴቶች አሉ። እነኚህ ሴቶችም የሀገር ብርሃን ናቸው። ብርቅዬ የሆኑ ሴቶች እንዳይታዩ ወደፊት እንዳይመጡ የሚያደርጉ ማነቆዎች አሉና መንግስት እና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እነኚህን ማነቆዎች በማስወገድ የሀገር ብርሃን የሆኑ ውድ ሴቶችን ሊጠቀሙባቸው እንዲሁም ድጋፍ ለሚፈልጉትም ተገቢውን ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል የሚል መልእክቷንም አስተላልፋለች።

‹‹የሴቶች ነባራዊ ሁኔታ፤ ማሕበራዊ፤ ታሪካዊ፤ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ተጽእኖዎች ሴቶች መብታችን እንዳይረጋገጥ ተግዳሮቶች ናቸው፤ ሆኖም ዋነኛው መፍትሔ ያለው በሴቶች ላይ ነው፤ ሴቶች መብቶቻችን እንዲረጋገጥ ተግተን ልንጥር ራሳችንን ልናበቃ እና ባልተመቻቸ ሁኔታም ቢሆን ተግዳሮቶችን እየተቋቋምን ልንወጣ ይገባል። በግሌ ተግዳሮቶችን እንደዕድል ፈንታ በመውሰድ ሁሌም ራሴን ለማብቃት እና ለማሳደግ እጥራለሁ፤ ይህን በማድረጌም ውጤታማ ሆኛለሁ። እኔ ማሕበራዊ እና ቤተሰባዊ ጫናዎችን አሸንፌ ወጥቻለሁ፤ የቤት ውስጥም ሆነ የስራ ኃላፊነቴንም በአግባቡ በመወጣት ላይ እገኛለሁ ይህን በማድረግ ላይ ያሉ ብዙ ሴቶች አሉ።” ብላለች።

ሁሉንም እንደየአመጣጡ የመመለስ ፀጋ ተችሯታል። ቤት ስትሆን ለልጆች እናት፣ በችሎት አደባባይ ደግሞ ውሳኔ አሳላፊ ዳኛ ነች። በመአልት በውጭ መዶሻዋን ይዛ ለመዝገቦች ውሳኔ ስትሰጥ ትውላለች፤ በሌሊት በቤቷ ውስጥ ደግሞ ሻሿን ሸብ አድርጋ ምግብ አብስላ ቤቷን አሰናድታ ልጆቿን ትንከባከባለች። የችሎቱ ዳኛ ለመሆን እልፍ በጥንካሬ የተፈተነችባቸው ትላንቶችን አሳልፋለች።

የሁለት ወንድ ልጆች እናት ናት። በዚህ ወንዶች ፈላጭ ቆራጭ በሆኑበት ዓለም ለሴት ልጅ ክብር ያላቸውና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ አድርጋ ቀርጻ ነው ያሳደገቻቸው። የማንም እምባና ሀዘን ምክንያት እንዳይሆኑ በንፅህና አሳድጋቻዋለች። ለነገ የተሻለ ዓለም ዛሬ ትውልድ ላይ መስራት አቻ የሌለው መፍትሔ ነው ትላለች። ራሷን የለውጡ ሀዋሪያ በማድረግ ለሴት ምቹ የሆነ ነገ መፍጠር ላይም ተሳታፊ ናት።

# የሴቶችን መብት ማክበር ከነጮ የተማርነው አይደለም

**መክሊት ወንድወሰን**

ባደጉት አገራት የታሪክ አዛቢነት እና በራሳችንም ቸልተኝነት ጥሩ እና ጠቃሚ የሆኑ ባህሎችን ፤ ፖሊሲዎች ፤ አመለካከቶችን፤ የኪነ ህንጻ ጥበቦች እንደው በአጠቃላይ የጀብዱ ታሪኮች ሁሉ ከነጮች እንደቀዳን ተደርጎ ይቀርባሉ።

ለአብትነት ያህል የተወሰኑትን ላንሳና ወደ ዛሬው ቁም ነገሬ እገባለሁ። የጢስ አባይን መነሻ አገኘ ተብሎ የሚነገርው ከወደ ምእራቡ የመጣ ሰው ነው፤ ጣና ላይ ሲኖር የነበረውስ ያገሬ ገበሬ ? እሱማ ሲኖርበት የቆየው ከአባቶቹ የወረሰው ፤ በመኖር ያገኘው እውቀት ነውና አገኘሁ ብሎ ስላላወራ ያገኘው ምእራባዊው እንደሆነ ይነገራል።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ የጤፋችንም ታሪክ አስገራሚ ነው ። ኢትዮጵያ ስትፈጠር ጀምሮ ስንበላው የቆየነውን ጤፍ ምእራባዊቷ አገር አዲስ ያገኘሁት ግኝት ነው ስትል ለዓለም አስታወቀች። ልጁ ቀማኛ አባቱ ዳኛ ነውና ነገሩ እኛ ብንጮህ ማን ሰምቶን።

ላሊበላና ሌሎች ጥንታዊ ቅርሶቻችን ሁሉ በነሱ የተገነቡ ለማስመሰል ለሊት እና ቀን ሲታትሩ ማየት የተለመደ ነው። ለልጆቻቸውም በመማሪያ መጽሀፍቶቻቸው ሳይቀር የትምህርት ስርዓት አድርገው ሲያስጠኑበት ማየት እንግዳ ነገር አይደለም።

የዚህ ሁሉ ነገር ግን አላማው አንድ ነው፤ ስልጣኔ ከኛ ነው የተቀዳው፤ ከዚህ በኋላም ከኛ ፈቃድ እና እውቅና ውጭ ከእናንተ የሚመጣና እኛ የምንኮርጀው ምንም እውቀት፤ ባህልና ትውፊት የላችሁም ነው አሸሙሩ። እኔስ ኢትዮጵያዊ አይደለሁ አሽሙር እና ነገር ቶሎ ይገባኛል ።

ለማንኛውም ወደዛሬው ርዕሰ ጉዳዬ ልግባ። ደግሞ እንዲህ ስል እስካሁን ስለ ርዕሰ ጉዳይሽ ማውራት አልጀመርሽም ለምትሉኝ እሱ መግቢያ ነው እላችኋለሁ።

እንደ ታሪክ ባለሙያዎች ገለጻ፣ በ1960ዎቹ እና 1970ዎቹ ውስጥ የሴቶች መብት እና እኩልነት እንዲከበር የሚያደርግ ንቅናቄ እንደተጀመረ ይነገራል። ንቅናቄውም የሴቶች መብት የነጻነት ንቅናቄ በመባልም ይታወቃል። አላማውም ለሴቶች የበለጠ የግል ነፃነት እና የእኩል ዕድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ነው። መሰረቱም ከወደ ምእራባዊቷ አገር አሜሪካ ነው ይሉናል። ታሪክ አዋቂ ነን ባዮች ።

እኔ ግን በዚህ አልስማማም። አለመስማማቴ ደግሞ ምክንያታዊ ይሁን እንጂ መብቴ ነው።

እኛ ዲሞክራሲንም ሆነ የሴትን መብት ለማክበር ምእራባውያንን ምሳሌ ማድረግ የለብንም። አባት አያቶቻችን ያቆዩልን ያልተበረዘ እና እኛን የሚመስል ባህል አለን ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ቻይና አሜሪካንን እውቀት ቀድታ (ኮፒ) አድርጋ ነው ዛሬ ላይ ለደረሰችበት የኢኮኖሚ ማማ የደረሰችው። አንኮርጅ እንልም ምክንያቱም ሁሉንም አናውቅምና ነገር ግን መኮረጅ ብቻ ሳይሆን ሌላው ዓለም ከኛ ሊቀዳው የሚችል እውቀት፤ ባህል እና ማንነት እንቀዳለን ያለንን በማክበር እና በማሳየት ለዓለም ማሳወቅ አለብን ባይ ነኝ ።

ኢትዮጵያ ከምእራባውያን ንቅናቄ በፊት የተለየ የሴቶችን መብት የሚያከብር ጥንታዊ ባህል ያላት አገር ነች። ነገሩ እንግዲ እንዲህ ነው ፡- በኦሮሚያ ገዳ ስርአት የሴቶች መብት ማስከበር የሚችል ባህል ከ2000 ዓመታት በፊት ጀምሮ መከበር ጀምሯል። የሴቶችን መብት የሚያስከብረው የ”ሲንቄ” ስርአት ይባላል።

በአፋን ኦሮሞ “ሲንቄ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴቶች ከጋብቻ በኋላ የሚይዙትን ቀጭን ዱላ ነው። የመዋለድ፣ የምርታማነት እና የሀብት ምልክትም ነው። “ሲንቄ” በገዳ ሥርዓት ውስጥ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ተጽእኖም አለው።

“ሲንቄ” ከጥሩ መዓዛ ካለው ዛፍ ላይ ተቆርጦ በጥበብ ይዘጋጃል። በአብዛኛው “ሲንቄ” ለማዘጋጀት የበለጠ ተመራጭ የሆኑት ዛፎች በአገሬው ቋንቋ ‘ዋዴሳ’ ፣ ‘ሃሮርሳ’ ፣ ‘ልማና’ እና ‘ኡርጌሳ’ ከሚባሉ ዛፎች ነው።

በባለ ትዳር ሴት የምትይዘው ይህ ”ሲንቄ” ከሃሮሬሳ እንጨት እንዲዘጋጅ የሚደረገው ጠንካራ ስለሆነ በቀላሉ ስለማይሰበር ነው። ”ሲንቄውን” ለማዘጋጀት ለሴቲቷ ቁመት በሚስማማ መልኩ ይቆረጣል።

“ሲንቄ” የያዘች ማንኛዋም ወይዘሮ “ሲንቄውን” እንደ ማንኛውም እንጨት መጠቀም አትችልም። እንስሳትን አትመታበትም፤ ሰዎችንም መሳሪያ አድርጋ ለማጥቃት አትጠቀምበትም።

ማህበረሰቡ “ሲንቄ” የሴቶች መሳሪያ ነው ይላሉ፤ ምክንያቱም ሴቶች “ሲንቄ” ን በመያዝ በቡድን ብዙ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ይፈጽማሉ።

የገዳ ስርዓት ተብሎ የሚታወቀው የአስተዳደር መዋቅር ሴቶች መብታቸውን እንዲያስጠብቁ፤ የባሎችን የበላይነት እና ጫና እንዲያስወግዱ ያስችላቸዋል።

ሴቶች ልጆች ሲጋቡ እናቶቻቸው መብታቸውን የሚያስጠብቁበትን “ሲንቄ “ ይሰጡዋቸዋል።

የ”ሲንቄ” ህግጋት የሚገለፀው በቀጭኗ ዱላ ነው።

የሙሽራዋ እናት ለልጇ ስንቄ፣ ቦራቲ እና ባሬን ታዘጋጃለች። “ሲንቄ” የ’ቢርማድዱማ’ (የተፈጥሮ ነፃነት) ምልክት ነው። ከእንጨት ተቀርጾ በሃር የተጌጠ ‘ቦርቲ’ የእናትነት ምልክት ነው ለልጇ ትሰጣታለች። በጮጮ ውስጥም ወተት አዘጋጅታ ትሰጣታለች። የወተቱ በጮጮ ውስጥ መሆኑ የሀብት ምልክት ነው።

ሰርግ ላይ ሙሽራው ሙሽራዋን ሊያመጣ ሲነሳ የሙሽሪት እናት ከበሩ ፊት ለፊት “ሲንቄ” ፣ ቦራቲ እና ባሬ ይዛ ትቀመጣለች። የሙሽራዋ እናት “ሆ ባሬ፣ ሆ ባርሴ” ብላ እየዘፈነች ቦራቲውን እና ባሬውን ትሰጣታለች። ይህ ስርአትም ልጃቸውን ለወደፊቱ ባሏ ማስረከባቸውን የሚያሳይ ነው።

“ሲንቄ” ያላት ሴት በማህበረሰቡ ውስጥ በጣም የተከበረች ነች። “ሲንቄ” የያዘችን ሴት በመንገዷ ወንዝ ቢኖርና ማለፍ ቢያቅታት ማንም ወንድ ቀድሟት አይሻገርም። ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አድርጎ ያሻግራታል እንጂ።

ማንም ሰው “ሲንቄ” የያዘችን ሴት አልፏት መሄድ አይችልም እርሷ ካልፈቀደችለት በስተቀር።

የ”ሲንቄ” ተከታዮች አቴቴ ወይም ገንያ በመባል ይታወቃሉ። ሴቶቹ ከ”ብዩማ” (ከሰፈራቸው) ሲወጡ “ሲንቄያቸውን” በመያዝ እየዘፈኑ አንድ ወይም ብዙ ሰዎች ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ከፈረሳቸው ወርደው ተቀምጠው እርጥብ ሳርን እያጨዱ “ኢልቴኒናአ” ይላሉ። ሴቶቹም ሳሩን እየቆረጡ ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል። ሴቶቹ የስርአቱን ህግ ሳይከተሉ የሚቀሩትን ተከታትለው ይቀጣሉ።

በገዳ ስርአት ለኦሮሞ ሴቶች በስንቄ ህግ ከተሰጣቸው የመብት መገለጫዎች መሀል በቡድን በመሆን አንዲት ሴት በባሏ ብትደበደብ ለሴቲቱ ፍትህ ማስከበር ነው።

የተደበደበችው ሴት ካለችበት ቦታ ድምፅ ካሰማች፤ ድምጹን የሰማች ሴት በሙሉ ሮጣ ትወጣለች። ስታጠባ የነበረች ልጇን ጥላ፣ላም ስታልብ ነበረች “ኦኮቴዋን” ጥላ በእጇ ያለውን ስራ ሁሉ አስቀምጣ ወደ ውጭ መውጣት አለባት። ከዚያም ”በገዳ” ህግ መሰረትም ጥቃት ለደረሰባት ሴት ዳኝነት ይሰጣታል።

የ”ሲንቄ” ን ሥርዓት ለመፈጸም በቡድን የሚሄዱት ሴቶች ባሏ የደበደበባትን ሴት ቤት የሚሄዱት የ”ሲንቄ” መዝሙር እየዘመሩ ነው። መጀመሪያ የመጡት ሴቶች ልጅቱን ይዙና ከቤት ያወጧታል።

ሚስቱ በዚህ በሲንቄው ቡድን ውስጥ ያለች እያንዳንዱ ሰው ሚስቱን የደበደበውን ሰው ጨምሮ ሊያገኛቸው አይፈቀድለትም። በዚህ ሁሉ መካከል ቤቶች ሚስቶች የሌሉባቸው አና በረዶ ይሆናሉ። ህፃናት እናቶቻቸውን ማግኘት ስለማይችሉ ያለቅሳሉ። በዚህም ምክንያት ሌሎች አባወራዎች ተባብረው ሁሉም አጥፊውን ለፍርድ ለማቅረብ ይሞክራሉ፤ ቤት ያለ ሴት አይደምቅም እና ሚስቶቻቸው ሁሉ ከቤት የኮበለሉባቸው ባሎች አጥፊው ላይ ፍርድ ለማሰጠት ይፈጥናሉ።

ሴቶቹም ለተደበደበችው ሴት ፍርድ ሳይሰጥ አንዳቸውም ወደቤታቸው አይገቡም። ፍርዱ እስኪሰጥ ድረስ ሴቶቹ፣ የተጎዳችውን አባላቸውን ከበው፣ ጭቆናውን በዝማሬያቸው በመቃወም፣ በገዳ ሕጎች ውስጥ ለጨፌ / ለገዳ ምክር ቤት (ለአካባቢው ሽማግሌዎች) ይግባኝ ይጠይቃሉ።

ሴቶቹ ጉዳያቸውን ወደ “ጨፌ /ገዳ” ሲያመጡ ቁጢጥ ብለው ነው ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት። ይኸውም ለስርአቱ ያላቸውን ክብር ለማሳየት ነው።

ጉዳያቸውን ለመስማት የተቀመጠው እና የሴቶችን ክብር (ዋይዮማ) በሕግ ያስቀመጠው አካል የገዳ ስርአት ነው። በሌላ አነጋገር በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ደንቦች መፈጸማቸውን ያረጋግጣሉ፤ የህግ ጥሰት ደረጃዎችን ያዘጋጃሉ።

ከዚያም ሴቶቹን እንዲህ ሲሉ ይጠይቋቸዋል፡- “የኛ ሴት ልጆች ምን አጋጥሟችሁ ነው?” “በምንድነው የተበደላችሁት?” ብለው ይጠይቃሉ።

ቡድኑን የምትመራዋም ሴት የተደበደበችውን ሴት ከፊት ለፊቷ ይዛ ለጨፌው ተሰብሳቢ ምን እንደተፈጠረ ታስረዳለች። የሕግ አስከባሪዎች (የጨፌው ዳኞች) በደል ያደረሰውን በመለየት ጉዳዩን ያጣራሉ።

በመጨረሻም ጨፌው የደረሰውን ጉዳት ገምግሞ ውሳኔ ያሳልፋል። ይህ ውሳኔውም ካሳ የሚሆን በከብት ማረድን ሊያካትት ይችላል።

የ”ሲንቄው” አባላትም ይህንን ውሳኔ ያስፈጽማሉ። በመቀጠልም የታረደውን ስጋ ለጉባኤው ሰጥተው ዘፈናቸውን ይዘምራሉ እና ፍርድ ያገኘችውም ሴት ወደ ቤቷ ትመለሳለች።

እንዲህ ያለው ስርአት የሚተገበረውም በፊቷ ላይ ጠባሳ ላለባት ሴት ወይም ከስድስት ወር በፊት ለወለደች ሴት እንጂ በባሏ ለተደበደበች ሴት ሁሉ አይደለም የሚሉም አሉ። ነገር ግን ስርአቱ እንደየ አካባቢው ይለያያል።

ከሽማግሌዎች እንደሰማነው የገዳ ስርዓት ከመዳከሙ በፊት እንዲህ አይነት እርዳታ ለሁሉም ሴቶች ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመዋል። ከዚህ ሁሉ በተለየ አዋላጅ የሆነችን ሴት መደብደብ ደግሞ ቅጣቱ ትልቅ ነው።

የሲንቄ አባላትም በጦርነት ወይም በግጭት ጊዜ አስጣራቂና ተሰሚም ጭምር ናቸው። በኦሮሞ ጎሳዎች መካከል ግጭት ሲፈጠር ወይም ትልቅ ጦርነት ሲከፈት አንዱ ሌላውን የሚጎዳ ከሆነ፤ የጦርነቱን ዜና ቀድማ የሰማች ሴት በመንደሯ ያሉትን ሴቶች ታስተባብራለች። የጦርነቱን ዜና የደረሳቸው የሴቶች ቡድን ወዲያው ከ”ሲንቄዎቻቸው” ጋር ይሰበሰባሉ።

የ”ሲንቄ” ን መዝሙር እየዘመሩ ወደ ጦር ሜዳም ይሄዳሉ። ይህን ኃይል ለ”ሲንቄ” የሰጠህ አምላክ ተመስገን እያሉም ያመሰግኑታል። ወደ ጦርነቱ ሲቃረቡ ጦርነቱ እንዲያበቃ በእግዚአብሔር ስም ይጸልያሉ። ጦርነቱም ጋር ሲደርሱም ዘፈናቸውን እየዘፈኑ ጦርነቱ እንዲቆሙ ጸበኞቹን ይጠይቃሉ፤ ለማቆም ፈቃደኛ ካልሆኑ ጣልቃ ይገባሉ። ጦርነቱ የቱንም ያህል የከፋ ቢሆን ከዚህ ህግ በላይ አይሆንም። ወዲያውኑ ይቆማል። በዚህ ሰአት “ሲንቄ” የማስታረቂያ መሳሪያ ሆኖ ይገለጣል ።

በተፈጥሮ ልጅ መውለድ የማይችሉ ሴቶች ወይም መካን የሆኑ ቤተሰቦች ከዘመድ ወይም ከሌላ ሰው ልጅን በጉዲፈቻ መውሰድ ይችላሉ። ልጅ የሌላት እና በጉዲፈቻ ህግ ልጅን ማደጎ ለመውሰድ የምትፈልግ ሴት ሲንቄ, ወተት እና ጭኮ ይዛ ወደ ህጻኑ ወላጆች ዘንድ ትሄዳለች። ጉዲፈቻ ለመውሰድ የሚመረጡት ወላጆች ብዙ ልጆች ሊኖራቸው ይገባል። እንደነዚህ ያሉት ወላጆች ልጆቻቸውን የሲንቄ ዱላ ይዛ ወደ እነርሱ ቤት የመጣችን ሴት በክብር እንዲቀበሉ እና እንዲያስተናግዷት ይገደዳሉ። ሄዳ ልጃቸውን ለማደጎ የጠየቀች ሴት አሳፍረው መላክ አይችሉም።

”ሲንቄ” ይዛ ለምትማጸናቸው ሴት ልጃቸውን እንድታሳድግ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። በምትኩም እሷም ልጁን እንደልጇ የማሳደግ ኃላፊነት አለባት።

ይህ ነገር የሴቲቱን ሞራል እና ባለመውለዷ የሚደርስባትን ጫና ለመቀነስ ታልሞ የሚደረግ ባህል ነው። እንግዲ ወዳጆቼ ያሉንን ጠቃሚ ባህሎች አዘምነን እና በሰፊው ጽፈንላቸው ለዓለም ሁሉ አርአያ የምንሆንበትን ቀን ያምጣው እያልኩ ለዛሬው ጨረስኩ።

**እኛ ዲሞክራሲንም ሆነ የሴትን መብት ለማክበር ምእራባውያንን ምሳሌ ማድረግ የለብንም። አባት አያቶቻችን ያቆዩልን ያልተበረዘ እና እኛን የሚመስል ባህል አለን**

# ግብርናን በሙያ፣ ገበሬነትን በማዕረግ

**አስቴር ኤልያስ**



በረከት የበጎነት፣ የመልካምነት ፍሬ ማሳያ ነው። የበረከት እሴቶች በምድር ጸጋዎች፣ በድንቅ ተፈጥሮዎች ይመሰላሉ። ይህ እውነት ከስም በላይ ግብር ሆኖ ሲታይ ደግሞ የቃሉን ትርጉም ይበልጥ ያገዝፋል።

‹‹ሥምን መልአክ ያወጣዋል›› እንዲሉ ወላጆቿ ‹‹በረከት›› ይሉትን ስም የቸሯት በምክንያት ነበር። ውሎ አድሮ ሀሳባቸው እውን ሆነ። እነሆ ! ስሟ ትርጉሙን ለበሰ። የእነሱም ትንቢት ከቀኑ ደርሶ ፍሬያቸው አሸተ። በረከት እንደ ልባቸው ሀሳብ ሆና ጸጋዋን አበዛች። የህልማቸውን ትርጉም ፈታች።

አንዳንዴ አንዳንዶች ከነፍስ ጥሪያቸው ይናበባሉ። ከመክሊታቸው ጫፍ ይገኛሉ። እንዲህ በሆነ ጊዜ በረከታቸው ከእነሱ አልፎ ለሌሎች ይተርፋል። ፍሬያቸው ለብዙሀን፣ ዘራቸው ለበርካቶች ይዋረሳል።

‹‹ገበሬ›› ይሉት የወል ስም፤ ልክ እንደ ማዕረግ ስም ሁሉ ከስሟ በፊት ቀድሞ ይጠራል። ይህኔ የሚሰማት ክብር ላቅ ያለ ነው። ከግብርና ስራ ጋር ያላት ቁርኝት ከልጅነቷ የጀመረ ነውና ወደመሬት ተጥሎ ለሚያድግና ለሚያፈራ ሁሉ ልዩ ፍቅር አላት። እሷ የፍሬውን መጨረሻ እስከታይ ድረስ እንክብካቤዋ ልክ ለእንቦቀቅላ ልጅ የሚደረግ ጥንቃቄ አይነት ነው - ገበሬዋ በረከት ወርቁ።

በረከት፣ ትውልዷም ሆነ እድገቷ በውቢቷ ሐዋሳ ከተማ ነው። ፊደል ቆጥራ እስከ 12ኛ ክፍል የተማረችው በሐዋሳ ነው። አባቷ መምህር፤ እናቷ ደግሞ የኤች.አይ.ቪ እና ስነ ተዋልዶ መማክርት ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት ይሰሩ ነበር። እናት በበጎፈቃድ ያለ ወርሃዊ ደመወዝ መስራታቸው የእነ በረከትን ቤት አላጎደለውም። የኑሯቸው ሁኔታ እንደአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ቤተሰብ ቢሆንም ልጆቻቸውን ከመማር የሚያናጥባቸው አልሆነም።

አባት የቤተሰባቸው ብዛት ስድስት በመሆኑ በእርሳቸው ብቻ ይመጣ የነበረው የአስተማሪ ደመወዝ በቂ ነው ብሎ መቀመጥ አልወደዱም፤ ከመምህርነቱ ስራ ጎን ለጎን ተጨማሪ ስራ መስራት ግድ ብሏቸው እንደነበር ገበሬዋ በረከት ትናገራለች። ስለዚህም የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ምሩቁ የሆኑት አባቷ ተጨማሪ ስራ ፍለጋ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልጋቸው ባላቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ ችግኝ ማፍላቱን ተያያዙት።

ይህ ብቻ አይደለም ዶሮ ማርባቱንም ስለጀመሩ ኑሯቸውን መደጎም ቻሉ። በግቢያቸው ከችግኝ ማፍላቱና ከዶሮ ማርባቱ በተጨማሪ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች ስለነበሩ የጓዳውን ጎዶሎ በቀላሉ ማስተካከል ቻለ። አባታቸው የልጆቻቸውን የትምህርት ወጪም ሆነ የቤት አስቤዛ ይጠቀሙ የነበረው በግቢያቸው ካበቀሉት አትክልት ላይ በመሸጥ ነበር።

## የግብርና ጅማሬው ምስጢር

እንደሚታወቀው በክረምት ትምህርት ቤት ይዘጋል። በዚህ ወቅት የገበሬዋ በረከት አባት ቤተሰቡን ይዘው ወደትውልድ ቀያቸው ሱሉልታ ያመራሉ። ወደስፍራው ሲያመሩ በዓላማ ነው። የግብርና ስራ ዋንኛ እቅዳቸው ይሆናል። ይህ አጋጣሚ ነበር በረከት ‹‹ገበሬ ›› የሚለውን ስያሜ እንድታገኝ ምክንያት የሆናት። በረከት ገበሬነትን ከስሟ አስቀድማ የማዕረግ ስም ለማድረግ የክረምቱ ጊዜ መነሻዋ ሆነ። የግብርና ፍቅርም ውስጣዊ ሚስጥሯን ገለጠ። ውሎ አድሮ ግብርናውን በፍቅር የምትወደው፣ የምታከብረው ሙያ አደረገችው። በክረምት በሚሰራው የግብርና ስራ ከመመሰጥ አልፋ እያንዳንዱን ሒደት በትኩረት ትከታተል ጀመር። ከሌሎቹ እህት ወንድሞቿ በተለየ መልኩ ስራውን ትወደው ታከብረው ያዘች። ይሁንና የምትወደውን የግብርና ስራ ከምትወደው አባቷ ጋር በመሆን ረጅም ጊዜ ለመስራት አልታደለችም። ወላጅ አባቷን ሞት ነጠቃት። ይህኔ በእጅጉ ተፈተነች፤፡ እርሳቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ እንደምታደርገው አልሆነችም። ነፍስያዋ በሀዘን ተሸፍና ሕይወትን አከበደችባት። ችግሩ የእሷ ብቻ አልሆነም። በቤተሰቡ ላይ ጫናው አየለ።

## እናትነት በልጅነት - በስነ ልቦና ጫና

ብዙ ጊዜ በተማሪነት ያለጋብቻ መውለድ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ፍጹም ነውር ነው፤ ከጋብቻ በፊት በቤተሰብ ቁጥጥር ስር እያለች የምትወልድ ሴት የሚደርስባት ውግዘትም ከበድ ይላል። ከጎረቤት ጀምሮ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በሚያስብል ሁኔታ ልጅቱን ለማግለል የማንንም ምክክር አይጠብቁም። ገበሬዋ በረከትም በልጅነቷ የልጅ እናት ሆና ነበር።ይሁን እንጂ እሷን ብዘዎች የሚያጋጥማቸው ጫና አላገኛትም። የስነ ልቡና ተጽዕኖ ሳይበረታባት ቤተሰቦቿ ሊያጋጥማት ከሚችል አካባቢያዊ ጫና ነጻ ሊያወጧት ችለዋል።

> ‹‹ እኛ እንጂ ያልሰራንበት እግዚአብሔር ያልሰጠን መልካም ነገር የለም። ያለንን ብናውቅ ኖሮ የሌለን ነገር እንደሌለ ይገባንና ለ40 ካሬ የጋራ መኖሪያ ቤት አንገዳደልም ነበር›› ››

በተለይ አባቷ እንደሌሎች አባቶች አልነበሩም። አንዴ ለተከሰተ ነገር ብዙ እንዳትጨነቅ መከሯት። ልቧ እንዳይሰበር፣ ውስጧ እንዳይጎዳ ‹‹አለሁሽ›› ልጄ አሏት። የዛኔ በሰዎች ጫና ልጃቸውን እንዳያጧት በብዙ ተጠንቅቀውላታል። በዙሪያዋ የሚፈትኗት፣ የሚያነውሯት ቢበዙም በአባቷ አይዞሽ ባይነት በርትታ ጠንክራ ቆይታለች።

በረከት በወቅቱ እሷን ያሳቅቁ የነበሩ አባባሎች ውስጧን የሚፈታተኑ ነበሩ። አባባሎቹ ዛሬም ቢሆን ትውስ ይሏታል።

‹‹ቆመሽ ቀረሽ፣ የሴት ልጅ መጨረሻ ይኸው ነው፣ እንዲህ ሆነሽ ቀረሽ፣ የት ይደርሳል የተባለው ዛፍ ቀበሌ ቆረጠው›› በሚል እንድትሳቀቅ መሳለቅ ደርሶባታል። አባቷ ግን ከእነዚህ ሰባሪ አባባሎች በላይ ገዝፎ የሚሰማትን የሞራል ድጋፍ ያደርጉላት ነበር። በረከት የእሳቸው በጎ አባባል ዛሬ የዓይምሮዋ ደማቅ ማህተም ሆኗል። ‹‹አይዞሽ የእኔ ጀግና፤ አንቺ አሁንም ቆንጆና ጠንካራ ልጄ ነሽ፤ አንቺ ልብስ ቀርቶ ጆንያ ለብሰሽ ብትሄጂ እንኳ ዛሬም ያምርብሻል›› እያሉ ያበረቷት፣ ያጀግኗት ነበር።

አዎ! ድንቅ አባቷ እነዚያን የስነ ልቦና እሾሆች ለመንቀል ጠንካራ እጆች ሆነዋታል። በእሷ ጫና ለመፍጠር የሚወረወሩ ክፉ ማህበረሰባዊ ቃላትን አሽመድምደው ጥለውላታል። ይህ የአባቷ አጽናኝ ሐሳብ ሞራሏን ቢደግፍ ውስጧ በረታ። ትምህርቷን ሳታቋርጥ በታሰበችው መንገድ እንዳትገኝ ምክንያት ሆነ።

## ስራን በባህር ማዶ

በረከት፣ በመጀመሪያ አገር ለቅቃ ያቀናችው ወደ ደቡብ ሱዳን ነበር። ጥቂት ቆይታ ዑጋንዳ፤ ከዛም ኬንያ ተጓዘች። ይህ ብቻ አልበቃትም ታንዛኒያ ብሎም ሞዛምቢክ ተጓዘች። ከአፍሪካ አህጉር ወጣ ብላ ደግሞ ወደቻይና ጣሊያን እያለች ወደተለያዩ አገራት ካመራች በኋላ የትዳር አጋሯ የትውልድ አገር ወደሆነችው ‹‹አየርላንድ ደብሊን›› አቀናች። በዚያ ለተወሰነ ጊዜ ተረጋግታ ተቀመጠች።

## የአገር ናፍቆት

አሁን በረከት ባለትዳርና የሶስት ልጆች እናት ናት። ባለቤቷ ጆናታን ፒን፣ አየርላንዳዊ ሲሆን፣ የሶስት ድርጅቶች ባለቤትም ነው። እርሱ ገበሬዋ በረከት ለኢትዮጵያ ያላትን ጽኑ ፍቅር ጠንቅቆ ያውቃል። አገሯን መውደድ ብቻ ሳይሆን መኖር የምትፈልገውም በአገሯ ሰማይ ስር እንደሆነም ይረዳል። እንደ እርሷ እምነትም ሁሉም ሰው መኖር ያለበት በአገሩ ምድር ነው። ወደ ውጭ መሄድ የፈለገ ቢኖር ለተጨማሪ ትምህርት አሊያም ለመዝናናት መሆን ይኖርበታል። ኑሮን በዘለቄታው በሰው አገር ማድረግ ተገቢ አይደለም ባይ ነች።

የሰው አገር እንደሚያሳቅቅ ሁሉ በአገር መኖር የልብ ልብ ይሰጣል። በአገሬ ሆኜ ባጠፋ ‹‹ግፋ ቢል ቢያስሩኝ ነው እንጂ ወደመጣሽበት ሂጂ ተብዬ አልመለስም›› የሚል ጽኑ እምነት አላት፤ አገሯ ከሆነ ወደመጣችበት አገር እንድትመለስ አትደረግም። እንደሌላ አገር ተወላጅ ፓስፖርት አትነጠቀም፤ በተገኘባት ጥቃቅን እንከን ሁሉ ለእስር አትዳረግም።

## ኢትዮጵያዊ ቁጭት

ገበሬዋ በረከት፣ ከኢትዮጵያ በቆዳ ስፋትና በሕዝብ ብዛት የማይወዳደሩ፣ ሚዛን የማይደፉ አገራት ኢትዮጵያን ሲረዱ ስታይ በእጅጉ ትበሳጫለች። ኢትዮጵያ ያሏት ወንዞች እንኳን ለራሷ ለሌላው የሚተርፉ ናቸው። ከአየር ንብረቷ ጀምሮ የትኛውንም አይነት ምርት የሚያሳፍስ ለም መሬት አለን። ክረምቱ፣ በጋው፣ በልጉ ሁሉ ተስማሚ የአየር ንብረት እንጂ እንደሌላው ዓለም በረዶ የሚያዘንብ፣ በከባድ ሙቀት የሚያሰቃይ አይደለም።

በረከት እንደምትለው ‹‹እኛ እንጂ ያልሰራንበት እግዚአብሔር ያልሰጠን መልካም ነገር የለም። ያለንን ብናውቅ ኖሮ የሌለን ነገር እንደሌለ ይገባንና ለ40 ካሬ የጋራ መኖሪያ ቤት አንገዳደለም ነበር›› እሷ ይህን እውነት በአዕምሮዋ ስታስብ ቆይታ በመጨረሻም ወደአገሯ ለመመለስ ወስናለች። ወደ አገሯ መመለስ ብቻ አይደለም። ቁጭቷን በስራ ለመወጣት ጭምር እንጂ። ወስና አልቀረችም፤ አደረገችው፣ ወደ እናት ምድሯ ኢትዮጵያ ጓዟን ጠቅላላ ገባች። የሀሳቧ ሞላ፣ የልቧ ደረሰ።

## ህይወት በአገር ምድር - ኢትዮጵያ

ወደእናት ምድሯ ኢትዮጵያ የመመለሷ ምስጢር ሰርታ ለበርካቶች በጎ አርዓያ ለመሆን ነው። እርሷ መስራት የምትፈልገው ደግሞ የአገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በሆነው የግብርና ዘርፍ ላይ ነው። በረከት ወደመረጠችው የግብርና ዘርፍ ለመግባት ጉዞ ጀመረች። መንገዶች ግን አልጋ በአልጋ አልሆኑም።

የመጀመሪያውን ዕቅድ ዕውን ለማድረግ ባሰበች ጊዜ መሬት ለማግኘት አራት ዓመታትን መጠበቅ ግድ ብሏታል። እንዲያም ሆኖ የተሰጣት መሬት አነስተኛ ነበር። ይሁን እንጂ ከአርሶ አደሮች ጋር በአብሮነት በመስራት፣ መሬት እየተከራየች ስራዋን ማጣደፍ ጀመረች። የበረከት ዋንኛ መርህ ጠንክሮ በመስራት መለወጥ እንደሚቻል

“እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**




ማመን ነው። እሷም የበኩሏን አድርጋ አገሯን መለወጥ ትሻለች።

ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች በኋላ መጀመሪያ ላይ ኦሮሚያ ክልል፣ አርሲ ዞን መሬት አግኝታ አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት ቀጠለች። ባገኘችው 40 ሔክታር መሬት ላይ በትጋት እየሰራች ሳለ በአን ድ ወቅት በኦሮሚያ አካባቢ ተከስቶ ከነበረው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር ተያይዞ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዋ ሙሉ በሙሉ ወደመባት። በወቅቱ ብታዝንም ፈጽሞ ተስፋ አልቆረጠችም።

## በአገር ተስፋ አለመቁረጥ

ገበሬዋ በረከት ‹‹በአገር ተስፋ አይቆረጥም›› በሚል መርህ በትጋት መንቀሳቀሷን ቀጠለች። ‹‹ ያለችኝ አገር አንድ ናት፤ እርሷም ኢትዮጵያ ናት›› በሚል ቁርጠኝነት ተነሳች። በአገሯ ተስፋ መቁረጥ ማለት በራሷም ተስፋ እንደመቁረጥ መሆኑን አምና ዳግም ስራውን ለመቀጠል ተወተረተረች። ትጋቷን ዕለት በዕለት ከፍ በማድረግ በትጋት ሰራች። አልወደቀችም። በእጅጉ ተሳካላት። በአሁኑ ጊዜ በ840 ሔክታር መሬት፣ በፈለገችው መጠንና ልክ የግብርና ስራዋን እየከወነች ትገኛለች።

በዚህ ስራ ውስጥ መውደቅ እንዳለ ሁሉ መነሳት እንዳለ ታምናለች። ቢሮክራሲው በዛው ልክ ፈታኝ ነው። በዘርፉ ተግዳሮት የሚሆኑ አካላት ቢኖሩም ‹‹እነርሱ ትልቋን ኢትዮጵያ ሊወክሉ አይችሉም›› በሚል ጠንካራ ጽናት አገሯን ብቻ በማሰብ ከስራዋ እንዳትስተጓጎል ትጥራለች።

በስራ እንቅስቃሴ የሚያጋጥሟት በርካታ ነገሮች ናቸው። በባህሪዋ ሰዎች ለሙስና ሲሰናዱ ስታይ እንደ የአገሯ ደመኛ ትቆጥራቸዋለች። የኢትዮጵያ ጠላት ጦር የሰበቀ ብቻ ሳይሆን ሙሰኛም ጠላት እንደሆነ ነው የምታምነው። በሌላ በኩል ሴቶች ስራቸውን ሳያስተጓጉሉ እንዳይሰሩ የሚተነኩሷቸውን ሁሉ እንደ አገር ጠላት ትቆጥራቸዋለች። ስለዚህም በእርሷ ዘንድ ጠላትን መዋጋት እንጂ አሳልፎ ለጠላት አገርን መተው ክልክል ነው።

ስለዚህ እንዲህ አይነቱን የአገር ጠላት በመፋለም ለቀጣዩ ትውልድ ከጠላት የጸዳች አገርን ማስረከብ ፍላጎቷ ነው። ከሙስናው ጋር በተያያዘ እኛ ጤነኛ የሆነች ኢትዮጵያን እንዳልተረከብን የምትናገረው በረከት፣ ጤነኛ የሆነች ኢትዮጵያን እኛ ለትውልድ ማስተላለፍ ግዴታ አለብን በሚለው ሐሳብ ታምናለች። አሁን ድህነትንም ሙስናንም በመዋጋቱ ረገድ ግብግብ ገጥማለች፤ በዚህም ብዙ ለውጥ እያመጣች ስለመሆኗ ነው የምትገልጸው።

## የእርሻ ስራ አጀማመሯ

በረከት ወርቁ ኢንተግሬትድ አግሮ ኢንዱስትሪ ባለቤት የሆነችው ጠንካራዋ ገበሬ፣ ወደእርሻ ስራዋ ስትገባ የስምንት ወር ህጻን ልጇን አዝላ ነበር። አካባቢው ሞቃት እንደመሆኑ በአካባቢው ዘንዶው እባቡ እንዲሁም ከሌላውም የዱር አራዊት ጋር መጋፈጡ ከስራው ባህሪ እንደ አንዱ የሚቆጠር ነበር። እንዲያም ሆኖ ፍርሃት ይሉት ነገር አልበገራትም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ‹‹እመጫት ነኝና እንክብካቤ እፈልጋለሁ›› ሳትል ሕጻን ልጇን መኪናዋ ውስጥ አስቀምጣት ተመላልሳ እያጠባች ስራውን ሳታጓድል ስትሰራ ቆይታለች።

የእርሻ ሥራን ያህል ተግባር ታከናውን የነበረው ልጇን አቅፋ፤ ባስ ሲልም አዝላ ነው። ‹‹ልጅ ታቅፌ እንዴት መስራት እችላለሁ›› ለሚሉ ሴቶች መስራት እንደሚቻል የገለጸችው በንግግር አይደለም። በረሃ ወርዶ በተግባር በመስራት ነው። እውነት ለመናገር የእርሻ ስራ ፈታኝ የሚባል ነው፤ ነገር ግን ፈታኝ ነው ብላ አልተወችውም፤ ልጇን አቅፋ፣ ስራውን በገሀድ ተጋፈጠችው እንጂ።

በረከት ‹‹ሕጻንም አዝለን መስራት እንችላለንና የሚያግድ ነገር ምንም የለም›› ትላለች። እንዲያውም ልጅ ይዞ ስራ ብርታት የሚሰጥ ተግባር እንደሆነ ነው የምትናገረው። ለዚህ ምክንያቷ ደግሞ አንድ የምንኖርለት ዓላማም ተስፋ በመኖሩ ነው ስትል ትናገራለች። ‹‹እኔ እንዲያውም ልንገርሽና አለችኝ ‹‹ወደስራ ታጥቄ የመግባቴ ምስጢር ይህቺን አገር ወደከፍታ ማማ ለማውጣትና ወንዶች ሞክረው ስላቃታቸው እኛ ሴቶች ደግሞ መሞከር ሳይሆን እንቀይራታለን በሚል ተነሳሽነት ነው››።

## የማዕረግ መጠሪያዋ ቃል €€ ገበሬ‹‹

ቀደም ሲል የግብርና ሙያን የስራ ዘርፌ ነው ብሎ ለመናገር አብዛኛው ሰው ፍላጎት አልነበረውም። ሌላው ቀርቶ በሰፋፊ እርሻዎች ኢንቨስትመንት እያካሄዱ ከዘርፉ በሚገባ በመጠቀም ላይ ያሉ ባለሀብቶች ሳይቀሩ የስራ መስካቸውን ‹‹ግብርና›› ብሎ ከመጥራት አስመጪና ላኪ ወደሚለው እንደሚያመዝኑ ይታወቃል። በዚህ ዘመን ግን በረከት ግብርናንና ገበሬነትን የስሟ መጠሪያ ይሆን ዘንድ ከስሟ በፊት አስቀድማዋለች። የማዕረግ ስሟ ይሆን ዘንድም ፈቅዳለች። ግብርና የተዋረደ ስራ አይደለም፤ ይልቁንም ሰዎች ቀና ብለው እንዲሄዱ የሚያስችል የተከበረ የስራ መስክ ነው ትላለች። ግብርና ከምግብ እስከ መድኃኒት የሚገኝበት የሰው ልጅ የጀርባ አጥንት በሆነው ዘርፍ መሳተፏ ከምንም በላይ እርካታን ይሰጣታል። ስለዚህም ነው በየደረሰችበት ራሷን ስታስተዋውቅ ‹‹ገበሬዋ በረከት›› በማለት በልበ ሙሉነት ራሷን የምትገልጸው። በዛ ስም በመጠራቷም ትልቅ ክብር ይሰማታል።

እርሷ በምታለማበት አካባቢ በአሁኑ ወቅት ከ11 በላይ ባለሀብቶች መሬት ወስደው በማልማት ላይ ይገኛሉ። እርሷ በዛ ቦታ ከገባች በኋላ ለብዙዎች ብርታት ሆናለች። ከምንም በላይ ደግሞ ሴቶች ለአምስትም ለስድስትም በመሆን በረከት የሰራችው የግብርና ዘርፍ እኛም ብንገባበት ውጤታማ የማንሆንበት ነገር የለም በሚል መንፈስ ዘርፉን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። ምክር ሲፈልጉ ሁሉ ከመምከር ጀምሮ መንገድ እስከማሳየት ትደግፋቸዋለች።

እርሷ እንደምትለው ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር በመሆን አብሮ ማደግ ከሌለ ድካም ሁሉ የቁልቁለት ጉዞ ይሆናል። አገር በድህነት ውስጥ ሆና ውስን ዜጎቿ ብቻ ሀብታም ቢሆኑ ትርጉም አይሰጥም ትላለች። ሀብታሙ ራሱ መጠሪያ ስሙ የሚሆነው የዚያች የድሃዋ አገር ሰው ነው እንጂ ክብር ይሉት ነገር አይታሰብም ባይ ነች።

## ኅብረተሰብን የሚደግፍ ተግባር

እስካሁን ለልማት ስራ በተሰማራችበት አካባቢ የተለያዩ የድጋፍ ስራ ስታከናውን ቆይታለች፤ ለአብነትም ትምህርት ቤት በመገንባት አቅም ያጡ የማኅበረሰቡን ልጆች እንዲማሩ አድርጋለች። በቋሚነት‹‹ ቢሻን ጉራቻ›› ላይ የምታስተምራቸውም 400 ያህል ተማሪዎች አሏት። ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል በአባቷ ‹‹ወርቁ አደራ ቡታ›› ስም በገነባቸው በዚሁ ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ የተማሪዎቹን የ ትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት በማስተማር ላይ ትገኛለች። በትምህርት ቤቱ የሚማሩ 400ውም ተማሪዎች የምግብ አገልግሎት ጭምር ያገኛሉ።

ትምህርት ቤቱ ስራውን በዚህ ዓመት የጀመረ ነው። ትምህርት ቤት የተገነባላቸው ልጆች በሐዋሳ ሐይቅ መሙላት ምክንያት የተፈናቀሉና ከሱማሌ ክልል ለመጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነው። እነዚህ ልጆች ትምህርት ለመማር የአምስት ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጓዝ ይገደዱ ነበር፤ አለፍ ሲልም ሐዋሳ ድረስ ይሄዱ ነበር፤ ስለዚህ መፍትሔ ይሆን ዘንድ በማሰብ የተገነባ ትምህርት ቤት ነው ትላለች።

ከዚህ ጎን ለጎን የእርሻ ስራውን በምታከናውንበት አካባቢ ደግሞ ማዋለጃና የላቦራቶሪ ሙሉ ቁስ ያለው ክሊኒክ ዲዛይኑ ጸድቆ የግንባታ ስራው ተጀምሯል። ለዚህ ዋና ምክንያቷ የእርሻ ስራ በምታከናውንበት አካባቢ በ25 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ምንም አይነት የጤና ኬላ ባለመኖሩ ነው። ሴቶች በተለይም ወላዶች እንዳይቸገሩ በቅርቡ አገልግሎቱን ያገኙ ዘንድ ዕድል ፈጥራለች።

በክሊኒኩ የሚሰጠው ሕክምና ከክፍያ ነጻ የሚሆን ነው። ይህ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆንም ከክፍያ ነጻ የሆነ የአምቡላንስ አገልግሎትም እንደሚኖር በረከት ትናገራለች። ክሊኒኩ የሚሰራበት አካባቢ ያለው የኅብረተሰብ ብዛት ወደ አስር ሺ የሚጠጋ ሲሆን፣ የበረከት እርሻ የሚገኘውም በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን አቢቻ ወረዳ ውስጥ ነው።

በኮሮና ወቅት ለአገር መከላከያ ሰራዊት አስር ሺ የፊት ጭንብል እስከ 900 ሺ በላይ ብር በማውጣት እንዲሁም የወላይታ ፖሊስ የሚጠቀምበትን ኤሌክትሮኒክስ መገናኛ (ዘመናዊ የመገናኛ ሬዲዮ) ከ400 ሺ ብር በላይ በማውጣት ገዝታላቸዋለች፤ ለየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በኮሮና ወቅት ልክ እንደ አገር መከላከያ ሁሉ አስፈላጊዎቹን የኮቪድ 19 መከላከያ ቁሳቁስ ከአንድ መቶ ሺ ብር በላይ በማውጣት ገዝታ አበርክታለች። ለፍቼ ዞን አስተዳደር እንዲሁ የ200 ሺ ብር ድጋፍ ለኮሮና መከላከል ስራ አድርጋለች።

በፍቼ ስር ባለች ዱበር አካባቢ በተለይ ተፈናቃዮች ባሉበት አካባቢ ትምህርት ቤት ለመገንባት ቦታ ወስዳ በመንቀሳቀስ ላይ ናት። አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ዘንድሮ ከክሊኒኩ ቀጥሎ የሚጀመር ይሆናል።

የእርሻ ስራዋን የምታከናውንበት አንዱ በሆነው አርሲ ዞን፣ ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ አንዶዴ ቀበሌ የሚገኙ ለ680 ተማሪዎች በሙሉ ወደ ስምንት ሺ ደብተር፣ አንድ ሺ እስክሪብቶና አንድ ሺ እርሳስ ገዝታ የሰጠች ሲሆን፣ የትምህርት ቁሳቁስ በመትረፉም ለጎረቤት ቀበሌዎች ሊሰጥ ችሏል።

## አካባቢ ጥበቃ

የእርሻን ስራ በፍቅር የምታከናውነው ገበሬዋ በረከት፣ አካባቢን ለመጠበቅና የአየር ንብረቱ መልካም ይሆን ዘንድ ለአፍታም ቢሆን ተዘናግታ አታውቅም። ከ300 ሺ በላይ ችግኝ ተክላ እርሱኑ በመንከባከብ ላይ ትገኛለች። ችግኞቹን በቀን ከ30 እና 40 ሊትር በላይ ናፍጣ በመመደብ እንዳይደርቁባት ታጠጣለች። ችግኙን ብቻ በቋሚነት ወራዊ ደመወዝ እየተከፈላቸው የሚንከባከቡ 12 ሰራተኞች አሏት። እነዚህ ሰራተኞች የምግብ ወጪያቸው ሙሉ በሙሉ ተችሏቸው የሚሰሩ ናቸው።

## የሴቶች ተሳትፎ

እርሻ ስራዋ ላይ የምታሳትፈው አብዛኛውን ጊዜ ሴቶችን ነው፤ በረከት ሴት ከወንድ ይልቅ አትክልት የመንከባከብ ዝንባሌ አላት ትላለች። በእርግጥ በእርሻ ስራዋ ላይ ወንዶችም የሚሳተፉ ቢሆንም ብዙን ጊዜ ወደሱስ ስለሚያመዝኑ ሱሳቸውን ለማስታገስ የሚባክነው ጊዜ እንደሚበልጥ ታምናለች።

ሴቶች ብዙዉን ጊዜ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንደ ደካማ ይቆጠራሉ። ይህ የማኅበረሰቡ አስተሳሰብ የመጣው ዛሬ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ነው። በትምህርት ቤት ደረጃ እንኳ የሴቷ ውጤት ላቅ ብሎ ከታየ ‹‹ሴት ሆና ሳለ ያመጣችውን ውጤት አያችሁ!!!›› ነው የሚባለው እንጂ ሴት ከፍ ያለ ውጤት እንኳ ታመጣለች ተብሎ ከፍ ያለ ሙገሳ አይሰጥም። በብዙዎች አዕምሮም ያለው የሴት ደካማነትን ጎልቶ ማሳየት ብቻ ነው፤ ገበሬዋ በረከት ግን ፈጽሞ እንዲህ አታስብም፤ ልክ እንደ ወንዱ ሁሉ ሴት የመስራት አቅም አላት ስትል በአርግጠኝነት ትናገራለች።

ሁሌ የትዳር አጋሯን የምትጠብቅን ሴት ብቻ ማየት የለብንም። እንኳን ራሷንና ቤተሰቧንም ጭምር ከጥቃት የመጠበቅ አቅም አላትም ባይ ናት።

በረከት ለዚህ ሁሉ አባባል ራሷን በአብነት ታስቀምጣለች። እርሷ የቻለችውን ‹‹ሌላዋ ሴት የማትችልበት ምንም ምክንያት የለም›› ስትል የሴቷ ጥንካሬ ከሰፈር እስከ አገር መለወጥ የሚያስችል ብርታት ነው። ሴቶች ጠንካራ ሲሆኑ በርካታ ነገር የመቀየር አቅም አላቸው ስትልም ታክላለች። የምንችለውም የማንለውጠውም ነገር የለም ስትል በራስ መተማመኗ ከፍ ያለ መሆኑን ትገልጻለች።

‹‹እኔ የለማ እርሻ ውስጥ ዘው ብዬ ያልገባሁት ለምቶ ስለተሰጣት ነው የሚለው እሳቤ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ እንዳይንገዋለል በማሰብ ነው። ምክንያቱም ሴትም ከምንም ነገር ከባዶ ተነስታ ቦታውን ምርታማ ማድረግ የሚችል አቅም እንዳላት ማሳየቷ ትልሟ ነውና›› ይህም ስኬታማ ሆኖ መታየት ጀምሯል ባይ ነች። ‹‹እኛ ሴቶች ከዜሮ መነሳት እንደምንችል ማስገንዘብ እፈልጋለሁ›› ትላለች። እንደሚቻል በማሳየቷም ሌሎቹ ሴቶች እንደሚከተሏትና እየተከተሏትም እንደሆነ ትረዳለች።

## ሴትነትና ተግዳሮት

በአገራችን ጾታዊ ጥቃት መኖሩ አይካድም፤ በረከትም ገና ወደ ኢንቨስትመንቱ ከመግባቷ ጀምሮ አሁንም ድረስ እንዲህ አይነቱ መሰናክሎች ያጋጥማታል። ይሁንና የገጠሟትን እና እየገጠሟት ያሉ ፈተናዎች ሁሉ ካሰበችው ግብ ለአፍታም አላስተጓጎሏትም። ፈተናው ከሙሰኛው ጀምሮ ሴትነትን የሚያንኳስስን ይጨምራል፤ ነገር ግን እነዚህ ተግዳሮቶች ይበልጥ አበረታቷት እንጂ ከመንገዷ አደናቅፈው አልጣሏትም።

እሷ ችግሮች ጠንከር ብለው ሲመጡባት ልትሸሸግበት የምትችለው ዘመድ ወይም ሊያስጥላት የሚችል ወገን የላትም። አቅሟን ከበቂ በላይ የሚፈታተናት ጉዳይ ሲገጥማት አሳልፋ የምትሰጠው ለአምላኳ ‹‹ለእግዚአብሔር›› ነው። የክፉ ቀኔ ብላ ለክፉ ቀን ከጎኗ ያስቀመጠችው አንድ ፈጣሪዋን ብቻ ነው። ብርቱዋ ገበሬ በረከት ወርቁ።

# ከሁመራ ሰሊጥ አራሚነት
## እስከ ጥበቃ ሠራተኝነት ለልጆች የተከፈለ ዋጋ

**በደግማዊት ግርማ**

በሰው ዘር ብቻ ሳይሆን በእንስሳቱ ዓለም ላይም እናትነት ባለ ከባድ ሚዛን ነው። በምድር ያሉ ሁሉ ሲሆኑት የሚገባቸው በመኖር የሚረዱት የህይወት ትልቁ መሰጠት ነው። የመኖር ጽዋ መሙያ የለጋስነት በአት የጥሩነት ዋሻ። እኔ ለእኔ ብቻ ባይነት በበረታበት ዘመን ግለኝነት ባስቸገረበት ስፍራ ልጄን የሚያስብል። እኔን ከሚሉት ቀንሶ ለራስ ሰው መልካም የሚሆንበት የገራሞች መንገድ ነው።

ክፉ የትዳር አጋር ጥፊው፣ የህይወት ብርቱ ክንድ ግፊው፣ የርሀብ ጥማቱ መበርታት ፣የችግሩ መደራረብ በእናትነት ውስጥ ትንሹ የሚቻል መከራ ነው። የፈጣሪ ጥልቅ ፍቅርና መቻል በእናትነት ውስጥ በብዙ ይገለጣል። የእናቶቻቸውን ያህል የሚሳሳ ወዳጅ ያጡ ብዙ ሰዎች አሉ። እናትነት ለሁሉም ጠሊቅ ቢሆንም ኢትዮጵያውያኑ እናቶች ጋር ሲደርስ ግን እናትነት በእልፍ መስዋዕትነት ተኩሎ ይሞሸራል። እናትነት ለኢትዮጵያውያን ከወለዱት ምንም ሳይጠብቁ ራስን እንደ ሻማ አቅልጦ ለልጅ ብርሀን የሚሰጥበት ህይወት ነው። ከማድጋው ውሀ ሲጠፋ እኔ አሁን ጠጣሁ የሚሉበት ከሌማቱ እንጀራ ሲታጣ ጠግቤያለሁ እያሉ ሆድን ባዶ ማሳደር እናቶች በየቤቱ ቢያንስ አንዴ የሚሏት ቃል ናት።

እናትነት ውስጥ አለመቻል በመሆን ሲረታ ራስ ወዳድነት በልጅ ፍቅር ሲበለጥ ማየት እንዳዘቦቱ ቀን ብዙ ነው። እናቶች በነጣ ፊታቸው ለልጆቻቸው ወዝ ይሆናሉ። የራሳቸውን የተጣበቀ አንጀት በብጣሽ ጨርቅ ሸፍነው ለልጆቻቸው ልባሽ ለመግዛት ለክፉ ቀን ያስቀመጧትን ጌጣቸውን ይሸጣሉ።

እናት ለልጇ አንድ ፈገግታ ስትል ልትከፍለው የምትችል እልፍ ዋጋ አላት። ለዚህም ይመስላል በተለምዶ እንኳን የእናትን ውለታ ይቅርና አንድ ቀን ልጇ ሲወድቅ እኔን ይድፋኝ ስትል የምትደነግጠውን ድንጋጤ ለመመለስ ራሱ የልጅ የእድሜ ልክ ምላሽ አይበቃም የሚባለው።

ዛሬ ስለ አንዷት ልጅን ለማሳደግ ሲሉ ብዙ የሆኑ እናትን ታሪክ ልናወጋችሁ ወደናል። ወይዘሮ ሽታዬ ወንድሙ ይባላሉ፤ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ውስጥ በጥበቃ ሰራተኝነት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። የአሁኑን ድርጅት የመጠበቅ ስራ ከመስራታቸው በፊት እልፍ የህይወት ዳገትና ቁልቁለቶች በእራሳቸው ወጥተው ወርደዋል። ከልጅነት ህይወታቸው ጀምሮ እስከ አሁን


ፎቶ-አሸናፊ ጉደታ
**ወይዘሮ ሽታዬ ወንድሙ**

ድረስ ስራን ሳይንቁ በመስራት ነው ያሳለፉት። ህይወት ምጣድ ላይ እንዳረረ ቂጣ ያላገለባበጠቻቸው ጊዜ የለም። የህይወትን መከፋትና መግፋት በበረታ ክንድ ነው ወርደው የወጡት።

ሌብነትና ባዕድ አምላኪነት አይሁን እንጂ ስራ ከተባለ ምንም ሳይንቁ ይሰራሉ። በረጅሙ ዞማው ጸጉራቸው ላይ በኩራት የተጀቦነው ሽበታቸው ሺህ ውበት ሆኖላቸዋል። በባለሞያ ሴት እጆች ደርበብ ብሎ የተቆላ ቡና የሚመስለው ጠይም የሰውነት ከለራቸው እንደ በረድ ከነጻው ፀጉራቸው ጋር አብሮ ሲታይ ልብ ይማርካል። አተኩሮ ላያቸው ሰው እናት ይህች ናት ተብለው በየሁሉም ቤት ሊሰቀል የሚገባው ምስል ባለቤት ናቸው። አይናቸው አወራራቸው አካሄድ አነሳሳቸው ሁሉ የእናትነት ነፋስ አለበት።

በኦሮሚያ ክልል ኖኖ ወረዳ ተወለዱ። ስፍራው የህይወታቸው አራት ዓመታት ብቻ የተኖረበት ነው። 1962 ዓ.ም በአራት ዓመታቸው በአጎታቸው አማካኝነት አዲስ አበባን ተዋወቁ። የእስከዛሬው ህይወታቸው ቀሪ ጊዜም በመዲናይቱ ቀጠለ። ከቄስ ትምህርት ቤት ዘልቀው ስድስት ወራትን ተማሩ። ቀጥለውም ከዜሮ ክፍል ጀምሮ እስከ አምስተኛ ተማሩ፤

በንጉሱ ዘመን በነበረው መፈንቅለ መንግስት ምክንያት ትምህርታቸውን አቋረጡ። ትምህርት እንደተቋረጠባቸው በአስራ አራት ዓመታቸው ህይወታቸው አጋር አገኙ። ተስፋዬ ውብሸት ከተባሉ ሰው ዘንድ ትዳር መሠረቱ። ለምለሙ ማህጸናቸው አራት ልጆችን አፍርቶላቸዋል። ልጆቻቸውን ለማኖር እርሳቸው ከመሞት ውጪ ሁሉንም ሆነው ኖሩ።

በዚሁ ጊዜ ሁመራ ሄደው ሰሊጥ አራሚ አጫጅ ሆነው ሰሩ። ከዚያ መልስም ህንዶች ቤት በጽዳት ለስድስት ዓመታት ሰሩ። ህንዶቹ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ሁርሶ በምድር ጦር ውስጥ ሁለት ዓመት ተቀመጡ። ብዙም አልቆዩ አባት ታመው ነበርና ተመልሰው ወደ አባታቸው ማስታመም ዘለቁ።

ያኔም በሰላምና መረጋጋት ተመርጠው ቀበሌ ሁለት ዓመት በመሳርያ ህዝብ የመጠበቅ ስራ ለአራት አመት ደግሞ የቀበሌ መስተዳድር ጸሀፊ በመሆን አገለገሉ።

ቤት የሚያስታምምላቸው ሰው ባለመኖሩ ምክንያት ስራውን አቆሙ፤ ያለአጋዥ ያስታመሟቸው አባት ከአራት ዓመታት በኋላ አረፉ። ከአባት ሞት በኋላ ህይወት ከባድ ሆነባቸው። መልክና ሁኔታን በቀያየረችባቸው ህይወት በብዙ ተሰቃዩ። ልጆቻቸውን ለማሳደግ ጥጥ እየፈተሉ መሸጥ ጀመሩ። ከዚያም መልስ ንግድ ምክርቤት ሁለት ዓመት ስራ ከሰሩ በኋላ አሁን ወዳሉበት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተቀጠሩ። በዚህ መስሪያ ቤት ዓለም አየሁ የልፋቴ ተከፈለኝ አሉ። በእድሜ ጀንበር ብዙ ቢያዩም ወጥተው ቢወርዱም ካለፈው ያለው ይሻላል እያሉ ለልጆቻቸው አባትም እናትም ሆነው አሉ።

# ከእቴጌ ጣይቱ እስከ አዝማሪ ፃዲቄ

**ሄርሞን ፍቃዱ**

ሴትነት ሲነሳ ጥበብ የተሞላበት ድል አድራጊነት እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ ከትላንት ታሪካችን ጀምሮ ዛሬም ድረስ በታላላቅ የስልጣን ደረጃ ተቀምጠው ኃላፊነታቸውን በትጋት የሚወጡ እልፍ ሴቶች ስለመኖራቸው ህያው ሥራቸው ምስክር ነው።

ሀገር ሚዛንዋን ጠብቃ እንድትቆም የሴቶች ሚና ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ወደ ትላንትና ታሪካችን መለስ ብለን ስንቃኝ ለሁሉም ነገር መነሻ የሆነው ሐሳብ ነው፤ ከሐሳብም የተመረጠና ድል የሚያጎናፅፍ ጥበብ የተሞላበት ሐሳብ በማመንጨት ታሪክ የሚዘክራቸው ዝነኛዋ እቴጌ ጣይቱ በመቀሌ ጦርነት ላይ ያቀረቡት የጦር ስልት ዋነኛው ጉዳይ ነው፡፡

እቴጌ ጣይቱ ከተለመደው የጦር ስልት ወጣ በማለት በጣልያኖች አጠገብ የነበረው የውኃ ኩሬ (ምንጭ) በቁጥጥር ስር እንዲውል በማዘዝ ጣልያኖች በውኃ ጥም ምክንያት እንዲማረኩና እንዲሸነፉ ማድረግ ችለዋል፡፡

ከእቴጌ ጣይቱ ጋር የዘመቱ በርካታ ሴቶች ለጦር ምግብ ከማቅረብ አልፈው የጦር መሳሪያ ያቀርቡ ነበር፤ በዚያ ጊዜ ታዲያ ሴቶች ‹‹ልብ ሳይቀር ያቀርቡ ነበር›› ሲል ፀሐፊ በእውቀቱ ስዩም ከአሜን ባሻገር በሚለው መፅሐፉ ላይ ይጠቅሳል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ ገድል ከፈፀሙት ከእቴጌ ጣይቱ በተጨማሪ በወቅቱ አብረዋቸው የዘመቱ በርካታ እህቶች፣ ሚስቶችና እናቶች ስለመኖራቸው ታሪክ ይነግረናል። ከእነዚህም መካከል በኪነጥበቡ ዘርፍ ብዙ ያልተነገረላቸው አዝማሪ ጻዲቄ ለዓድዋ ድል ባበረከቱት አስተዋጽኦ ድርሻቸው ከፍ ያለ ቢሆንም አልተዘመረላቸውም፡፡

ከዘማች አዝማሪዎች መካከል አንፀባራቂ የነበረችው አዝማሪ ጻዲቄ ዛሬ ተረስታለች፡፡ አዝማሪዋ በጦር ሜዳ የጀግኖች ልብ ትቆሰቁሳለች። የመቀሌ ውጊያ ላይ ጣልያኖች እርቅ ሲያስቡ እንዲህ ስትል ትችት አቅርባ ነበር፡፡

"አውድማው ይለቅለቅ፤ በሮችም አይለቁ
ቀድሞም ያልሆነ ነው፤ ውትፍትፍ ነው እርቁ"

አብዛኛው ዘማች ገበሬ ስለነበረ ጻዲቄ ጦርሜዳውን ባውድማ፤ አርበኞችን በበሬ መስላ መግጠሟ ነበር፡፡

ዋልተር ፐለውደን የተባለ በዘመነ መሳፍንት ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኘ የውጭ ዜጋ እንደመዘገበው፤ የወሎ ኦሮሞ ሴቶች ጦር ሜዳ ላይ ከወገን ጦር ጀርባ በመሆን ወኔ የሚቀሰቅሱ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፤ የጀግንነት ቅኔዎች ይቀኛሉ፤ የሚሸሽ ወታደር ሲያዩ ፊቱን ወደ ጠላቶቹ እንዲያዞር ይገስፃሉ፤ ይህ በወሎ ብቻ የተወሰነ አይደለም በሁሉም አቅጣጫ እንጂ፡፡

ዘመናዊ አዋጊ መኮንን ጠላቶቹ ወደፊት እንዲሄዱለት ሲፈልግ ከኋላ እየተከተለ ባቀባበለው ሽጉጥ እያስፈራራ ይገፋቸዋል፤ ሲሸሽ በተገኘ ወታደር የሞት ፍርድ የሚፈረድበት አጋጣሚም ነበረ፡፡ ይህ እንዳይሆን ቀላሉ መንገድ ሴቶች ከወንዶች ጀርባ እንዲሰለፉ ማድረግ ነው፡፡ ወታደር በሚስት ወይም በእህት እየታየ እንደሆነ ሲገባው የቆጠባትን ጉልበት ከለገመም ይበረታል፡፡

በወቅቱ እቴጌ ጣይቱ ከሴት ሰራዊቷ ጋር ሆና ጥቁር ጃንጥላ አስይዛ፤ በባዶ እግሯ እየተራመደች ከሰራዊት ጀርባ ትከተላለች፤ ድንገት ሰራዊቱ የጠላት ጦር ተጭኖት እንደ መሸሽ ሲል እቴጌ፤ አይዞህ አንተ ምን ሆነሃል ‹‹ድሉ የኛ ነው በለው›› ሲሉት ሰውየው የሰማው ቃልና እቴጌ ባያቸው ጊዜ ፀጥ ብሎ ይዋጋል፡፡ ወኔ እንደ ሰውነት ክፍላችን በተፈጥሮ ይዘነው አንወለድም፤ ጀግንነት የማህበራዊ ግኑኝነት ውጤት ነው፡፡

በዓድዋ ድል ማግስት ከተገጠሙ ግጥሞች መካከል የትኞቹ አዝማሪ ጻዲቄ እንደሆኑ ባይታወቁም ብዙ ቀስቃሽ ግጥሞችን በመግጠም ትታወቃለች፡፡ ከግጥሟ የተነሳም ሃኪም መሬብ የተባለ ፈረንሳዊ ጎብኚ ከዝነኛው የስፓርታ የጦር ሜዳ ገጣሚ ጋር አወዳድሯታል፡፡ አዝማሪዋ በዓድዋ ጦርነት ላይ ባደረገችው አስተዋፅኦ ሽልማትና የወይዘሮነት ማዕረግ ተቀዳጅታለች፡፡

በአጠቃላይ የሀገር ነፃነትና ፍትህ ለማስፈን እስከ ዛሬ ድረስ የሴቶች ሚና ትልቅ ቢሆንም እንደ ሰሩት ገድል እና ብዙ ልፋት የሚገባቸው ክብር መስጠት ላይ የሚቀር ብዙ ነገር አለ። ለአብነትም አሁን በከፍተኛ ስልጣን ሆነው ሀገር የሚመሩ ሴቶች ላይ አላስፈላጊ ትችቶች ይሰነዘራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ‹‹አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ›› እንደሚባለው የማህበረሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትንና ትልቅ ድርሻ ያላቸውን ሴቶች ማግለል በመሆኑ እንደ አገር ወደ ኋላ ያስቀረናልና ሊታሰብበት ይገባል፡፡

“እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ!”

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ልዩ ዕትም**

# የእናቶችን ድካም ለማቅለል ቆርጣ የተነሳችው ወጣት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ትውልዷና እድገቷ በውቢቷ ባህርዳር ከተማ ነው። የፊደልን ሀሁ የቆጠረችው እዚያው ባህርዳር በሚገኘው በባህርዳር አካዳሚ ሲሆን፤ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷንም በባህርዳር አካዳሚ ተከታትላለች። እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሴቶች ድካምና ዘርፈ ብዙ የሆኑ ጫናዎችን እያየች አድጋለች። ጊዜ ዑደቱን ጠብቆ ቢነጉድም የልጅነት አእምሯዋ መዝግቦ የያዘውን የእናቶችን ችግር፣ ድካምና እንግልት ቸል ማለት አልሆነላትም።

በአእምሯዋ ጓዳ የሚያንጎዳጎደው የእናቶችና የሴቶች ድካም እንዲሁም እንግልት እንዴት ማቅለል ይቻል ይሆን በማለት አውጥታለች አውርዳለች። ለጥያቄዋ ምላሽ እስከታገኝ ድረስ በውስጧ ማብሰልሰል አላቋረጠችም። ሀሳቧ ከሀሳብነት ተሻግሮ እውን እስኪሆን እረፍት ያልነበራት በመሆኑ ዛሬ እናቶችንና ሴቶችን ያግዛል ባለችው ተግባር እርምጃዋን አንድ ብላ ጀምራለች።

የእናቶችንና የሴቶችን ድካም እንዲሁም እንግልት ለመቀነስ ቴክኖሎጂን አጋዥ በማድረግ ‹‹ሞግዚት ዶት ኮም›› የተሰኘ መተግበሪያ በመፍጠር ‹‹ሀ›› ብላ ወደ ሥራ የገባችው እንግዳችን ወጣት ሳምራዊት ታረቀኝ ትባላለች። የወጣቷን የሥራ ፈጠራ፣ የሕይወት ልምድና ተሞክሮ የሴቶች ቀን በሚከበርበት በዛሬው ዕለት ያቀረብነው ለብዙ ሴቶች ተምሳሌት መሆን እንደምትችል በማሰብ ነው። መልካም ንባብ።

የእናቶችንና የሴቶችን ድካም ለማቅለል ቆርጣ የተነሳችው እንግዳችን ወጣት ሳምራዊት፤ ከአምስት ሴት እህቶችና ከአንድ ወንድሟ ጋር አብራ አድጋለች። ከአስተዳደጓ ጀምሮ በቅርበት የምታየው ነገር ሁሉ ለሴት ትልቅ ትኩረት እንዲኖራት አድርጓል። እናቷ ጠንካራ ሠራተኛ ስለነበረች የሥራ ትጋትና ብዙ ነገሮች ከሷ ተምራለች። ሆኖም ግን በአካባቢዋ የምታያቸው ሥራ ለመሥራት የሚወጡ እናቶች ልጅ ሲወልዱ ከልጅ የሚበልጥ ነገር የለም በሚል ሥራ ትተው ወደ ቤት ሲመለሱ አስተውላለች። ይህ ደግሞ ስለጉዳዩ አብዝታ እንድታስብበት አድርጓታል።

በአእምሯ ለሚመላለሰው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ጠንክራ መማር እንዳለባት የገባት ሳምራዊት፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ አቀናች። የመጀመሪያ ዲግሪዋን በኤሌክትሪካል እና ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ ትምህርት ተመርቃ በዩኒቨርሲቲ ለሁለት ዓመታት በረዳት መምህርነት አገልግላለች። ሁለተኛ ዲግሪዋን ለመማር ወደ ሕንድ ሀገር ባቀናችበት ቅጽበት ታዲያ የልጅነት አእምሯ የመዘገበው በውስጧ የተጸነሰው ሀሳብ ሊወለድ የሚችልበት አጋጣሚ ተፈጥረላት።

በሕንድ አገር በትምህርት ላይ በነበረችበት ጊዜ ሰዎች ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በቀላሉ ሕይወታቸውን እንዴት መምራት እንደሚችሉ መመልከቷ መንፈሳዊ ቅናት እንዳሳደረባት ትናገራለች። የሰው ልጆች ሕይወት ቀላል የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ውለው ብዙ ነገሮች ሲሰሩ ስትመለከት በእጅጉ ተገረመች። በዙሪያ ያሉ ወደ ውስጧ ያስገባቻቸው እናቶችን ውል አሉባት። ቁጭት ውስጧ ገብቶ ያንገበግባት ጀመር።

በሀገሯ ያሉ ብዙ ጠንካራ መሥራት እንዲሁም መማር የሚፈልጉ እናቶች በወሊድ ምክንያት የሚያግዛቸው ሰው በማጣት ሥራቸውን ሲለቁ በቅርበት እያየች ያደገችው ሳምራዊት፤ ይቺ እናት የሚያግዛት ብታገኝ ሥራዋን አትለቅም ነበር ትላለች። እናቶች ሠርተው የተሻለ ነገር መፍጠር ሲችሉ በዚህ መልኩ መገደባቸው በእጅጉ የሚቆጫት መሆኑን ትናገራለች።

‹‹ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ አንድ የሆነ ዘዴ (ሲስተም) ቢፈጠር እናቶች ከሥራ ውጭ አይሆኑም፣ ድርጅታቸውንም አይለቁም፤ ትምህርታቸውንም አያቋርጡም፣ ከህልማቸውም አይነጣጠሉም›› የምትለው ሳምራዊት፤ እሷን መርዳት ቢቻል ልጇቿን በአግባቡ ታሳድጋለች፤ ቤተሰቦቿንም ትረዳለች። ሥራዋን በአግባብ ትሰራለች፤ ሕልሟንም ትኖራለች የሚል ቁጭት አሳድሮባታል።

ሕንድ ሀገር ያየችው ዲጂታል ሲስተም በጣም አስደሳች እንደሆነ የምትናገረው ሳምራዊት፤ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ እንዲህ እንደአሁኑ በዲጅታል ሲስተም የሚሰሩ ሥራዎች እምብዛም እንዳልነበሩ ታስታውሳለች። በሕንድ ቆይታዋ የመጀመሪያው ቴክኖሎጂ ምን ያህል የሰዎችን ሕይወት ቀላል እንዳደረገላቸው ማስተዋል ችላለች።



ወጣት ሳምራዊት ታረቀኝ

ሁለተኛው ደግሞ ሲስተሙ በራሱ እምነትን መፍጠር መቻሉን ተመልክታለች።

በዚያ ያጋጠማትን አጋጣሚም አጫውታናለች። ‹‹እኔ የልብስ ብራንድ ለመስራት ፈልጌ ሎጎውን ዲዛይን አድርጌ የምፈልገው ልብስ በኦንላይን አዘዝኩ›› የምትለው ሳምራዊት፣ ትዕዛዙን ስፈጽም እከፍላቸዋለሁ በሚል ያዘዘችው ትዕዛዙ በታዘዘው መስፈርት መሠረት ተሰርቶ ያለችበት መምጣቱ አግራሞት ፈጥሮባታል። ‹‹ይህንን ትዕዛዝ ስልኬን ባላነሳ ወይም አልፈልግም ብላቸው ለሌላ ሰው የሚሸጡት ነገር አይደለም›› የምትለው ሳምራዊት፤ ይህ የሚያሳየው እምነት የተሞላበት በቀላል መንገድ መገበያየት የሚያስችል ስርዓት መፍጠር በመቻላቸው ነው ትላለች።

በአገር ውስጥም እንዲህ ያለ ስርዓት መፍጠር ባለመቻሉ ነገሮች መራዘማቸው፣ አድካሚና አሰልቺ መሆናቸውን ታነሳለች። ሳምራዊት፤ ለቴክኖሎጂ ቅርብ በመሆኗ ይህንን ሲስተም ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ብዙም አልከበዳትም። ሕንድ አገር እያለች በንድፈ ሀሳቡን (በፕሮፖዛል) አዘጋጅታለች። ወደ ሀገሯ ስትመለስም ሀሳቧን እውን ለማድረግ ቴክኖሎጂና ሙያውን አንድ ላይ ማስኬድ የሚያስችል ዘዴ ለመፈለግ ጥናት ማድረጓን ታወሳለች። እነዚህን ሁለቱን ሲስተሞች በአንድ የያዘ ፤ በደንብ ያልተነካ እና ብዙ ሰው ያላየው ዘርፍ የልጆች እንክብካቤ ሆኖ አግኝታዋለች። ያን ጊዜ ነበር በሀሳብ የነበረው ‹‹ሞግዚት ዶት ኮም›› መወለድ የቻለው።

ሳምራዊት የፈጠራ ሀሳቧን እውን ለማድረግ በምታደርገው ጥረት ብዙ መሰናክሎችን ማለፍ የግድ ሆኖባታል። ‹‹የቴክኖሎጂ እውቀቱ ቢኖረኝም የቢዝነስ እውቀት አልነበረኝም›› የምትለው ሳምራዊት፤ ለዚህም ስለቢዝነስ የሚያስለጥኑ አካላት መፈለግ የመጀመሪያ ሥራዋ ነበር። ያኔ ነበር በልጆች እንክብካቤ መሥራት እንደምትፈልግ በማሳወቅ ሀሳቧን ይዛ ‹‹ቡሉሙን ኢትዮጵያ›› የተሰኘ የቴክኖሎጂ ተቋም የተቀላቀለችው። በዚያም ለስድስት ወራት ቆይታ ካደረገች በኋላ በሀሳብ ያደገው ‹‹ሞግዚት ዶት ኮም›› 2014 ዓ.ም ተመሠረተ።

‹‹ሞግዚት ዶት ኮም›› ወላጆችን ከሞግዚት ጋር የሚያገናኝ የልጆች እንክብካቤ ላይ የሚሰራ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ሥራውን ሲጀምር ትልቁ ተግዳሮት የነበረው በቂ የሆኑና የሰለጠኑ ሞግዚቶች ማግኘት አለመቻል ነው። ይህ ደግሞ ድርጅቱ ሞግዚቶችን ከማገናኘት ባሻገር ሞግዚቶችን ማስልጠን ላይ ትኩረት እንዲያደርግ አስችሎታል። ከተለያዩ ስልጠና ተቋማት ጋር በአጋርነት በመስራት ለበርካታ ሞግዚቶች ስልጠና መስጠት ተችሏል። ስልጠናውም ለብዙ እናቶች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል።

ሳምራዊት እንደምትለው ‹‹በአንድ በኩል ብዙ ሥራ የሚፈልጉ ሴቶች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ልጆቻቸውን የሚንከባከቡላቸው ሞግዚት ፈላጊ ብዙ ሠራተኛ እናቶች አሉ›› እነዚህ ሁለቱን የማገናኘት ተመጋጋቢ ሥራዎች ናቸው። ሠራተኛ የሆኑ እናቶች የሚፈልጉት የሰለጠነች፣ ሥራውን የምታከብር እና ታማኝ ልጅ ተንከባካቤ ሞግዚት ነው። ለሞግዚቶችም የሥራ እድል በመፈጠሩ ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩበት እና ለእናቶች ደግሞ ሥራቸውን ከመተው ሙሉ እምነታቸውን የሚጥሉባቸው ሞግዚቶች ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ ተችሏል ትላለች።

‹‹በአገር ውስጥ ተሞክሮ ብዙ ስልጠናዎች ቢሰጡም ሥራ መፍጠር ላይ ግን ችግር አለ›› የምትለው ሳምራዊት፤ አንዷት ሞግዚት ሦስት ወይም አራት ሰርተፊኬት ሊኖራት ይችላል። ድርጅቱ ሥራ መፍጠር ላይ ያለውን ክፍተት እየሞላ መሆኑን ትናገራለች። ስልጠና የተሰጣቸው ሞግዚቶች ከወረዳ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ተመልምለው የሚመጡት እናቶች ናቸው። የስድስት ወር፣ የሦስት ወርና የአርባ አምስት ቀናት ስልጠናዎች ያለምንም ክፍያ በነጻ እንዲወስዱ መደረጉን ተናግራለች።

**ሞግዚት ዶት ኮም** በ20 ሞግዚቶች ሥራ መጀመሩን ያነሳችው ሳምራዊት፤ አሁን ላይ 600 መቶ ሞግዚቶች በፕላት/ፎርሙ ላይ ተመዝግበዋል። ከእነዚህ ውስጥ 300 ለሚሆኑ ሞግዚቶች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል። በአንድ አመት ጉዞ ውስጥም እጅግ አስደሳች ሥራዎችን ሰርቷል ትላለች። ድርጅቱ በርካታ ተግዳሮቶችን በማለፍ ለእናቶች እፎይታ መሆን እንዲሁም ለሞግዚቶች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ትናገራለች።

ሞግዚት ዶት ኮም የሚሰጠው አገልግሎት ዘርፍ ብዙ ሲሆን የመጀመሪያው 80 በመቶ የሚሆነው አገልግሎት በተመላላሽነት የሚሰሩ ሞግዚቶችን ማገናኘት ነው። ሁለተኛው በቋሚነት ቤተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ ሞግዚቶችን ማገናኘት ነው። ሦስተኛው የአዛውንት እንክብካቤ አገልግሎት ሲሆን፤ አራተኛው ደግሞ አስታማሚነት የሚሰጡ አገልግሎቶች ናቸው። አምስተኛ አራሶችን እንክብካቤ (ምትኬ የተባለ) አገልግሎቶች ያሉት ነው።

ድርጅቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ሲስተም አስተማማኝ የሆነ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ነው። አሁንም ለብዙ ወላጆች ተደራሽ ለመሆን ብዙ ሞግዚቶች በመቅጠር አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከሀገሪቱ ውስጥ ካሉ ዋና ዋና ከተሞችን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል።

ወደዚህ ሥራ ስትገባ የከበዳት ለሥራ ያለው አመለካከትና ለሥራ የሚሰጠው ክብደት እንደሆነ የተናገረችው ሳምራዊት፤ እኛ የምናስበው የሚከፈለንን እንጂ ከእኔ ምን ይጠበቃል የሚለው አናስብም ትላለች። አሁን ላይ ያሉን የሥራ ባህሪያት እንደሀገር ትልቁ ተግዳሮቶቻችን ናቸው። ሥራውን ለማገናኘት በሚደረገው ጥረት ወላጆች ወይም ሥራውን ፈላጊዋ ሞግዚት በተቀጠሩበት ሰዓትና ጊዜ አንዳቸው ላይገኙ እንደሚችሉ ትናገራለች። በዚህ የተነሳ ድርጅቱ የራሱን የሥራ ባህል መፍጠር ችሏል። የድርጅቱ ሠራተኞችም ሆኑ ተቀጣሪዎችም በእኔነት ስሜት ሥራዎችን እንዲሰሩ ሆኗል።

ድርጅቱ በቀጣይ ሦስት ዓመታት ውስጥ 10 ሺ ለሚሆኑ እናቶችና ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር አቅዶ እየሰራ ነው የምትለው ሳምራዊት፤ ሞግዚት ዶት ኮም የቴክኖሎጂ ድርጅት ብቻ ሳይሆን የስልጠና ተቋም እንዲሆን ራዕይ አስቀምጦ እየሰራ መሆኑን ትናገራለች። በዩኒቨርሲቲ እና በኮሌጅም ያሉ ተማሪዎች ጭምር ስልጠናዎች እንዲወስዱ በማድረግ በትርፍ ጊዜያቸው መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል ብላለች።

አሁን ላይ በዌብ ሳይት ብቻ የነበረው አገልግሎት የሞባይል መተግበሪያ እና የጥሪ ማዕከላት እንዲኖሩት ለማድረግም እየተሰራ እንደሆነ ያነሳችው ሳምራዊት፤ ድርጅቱ በአፍሪካ ቴክኖሎጂውንም ሆነ ሥነ ምግባርን የያዘ ጠንካራ የሆነ የእንክብካቤ ተቋም ለመፍጠር ራዕይ ሰንቆ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ነው የተናገረችው።

ሥራ በማጣት የተንገላቱ ወጣት ሴቶች ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ማሰብ አለባቸው የምትለው ሳምራዊት፤ የራስን ሕልም ለመኖር በርካታ ውጣ ውረዶችን ለማለፍ መገደድም እንዳለ ማወቅ ይገባል ትላለች። አንድ ደረጃ ሳይረገጥ አስረኛው ደረጃ ላይ አይደረስምና ፤ እራስ ላይ ኢንቨስት በማድረግ ዘመኑ የሚጠይቀውን እውቀት በመያዝ በሁሉም ቦታ ተፈላጊ መሆን ይቻላል ትላለች። አሁን መሥራት የማንፈልገው ነገር መሥራት ነገ የምንፈልገው ሕልማችን ላይ ለመድረስ እንደመሰላል ነው የምትለው ሳምራዊት፤ በራስ ተስፋ አለመቁረጥ፣ ችግሮች በሚደራረቡበት ጊዜ መጨረሻ ናቸው ብሎ አለማሰብ እና ወጣትነት በማሰብ በጣም ብዙ እድልና ተስፋ ከፊታችን እንዳለ በጥልቀት ማሰብ ይገባል ትላለች።

‹‹ሥራው ባልጀምረው ኖሮ ውስጤ ያለው ኃይል እኔን ይበላኝ ነበር›› የምትለው ሳምራዊት፣ ብዙ ልምዱ ሳይኖራት የራሷን ሥራ መጀመሯ በጣም እንዳስፈራትም አልሸሸገችም። ‹‹ዛሬ በወጣትነቴ ይህንን ኃላፊነት ካልወሰድኩ መቼም አልወሰድም በሚል ጽኑ መንፈስ መነሳቷን ትናገራለች። ዛሬ በሕይወት አድርገዋለሁ የምለው ነገር ዛሬ ካላደረግኩ መቼም አላደርገውም፤ ስለዚህ ማድረግ አለብኝ፤ ማየት ያለብኝ ማየት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ ካልተሳካ እማርበታለሁ። እግዚአብሔር ይረዳኛል፤ መወጣት እችላለሁ›› በሚል በድፍረት እንደገባችበት ትናገራለች።

በዚህም ያጋጥሙኛል ብላ ያልጠበቀችው ብዙ እድሎች እንዳጋጠሟት የምትናገረው ሳምራዊት፤ አንድን ሥራ ለመጀመር መወሰን፣ ማየትና መጀመር በጣም አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ትናገራለች። በዚያ መንገድ ውስጥ ደግሞ ሌሎች በሮች ይከፈታሉ፤ የተወሰነ ጭላንጭል ብርሃን ሲታይ ያንን እየተከተሉ መሄድ ያስፈልጋል ትላለች።

‹‹የመጀመሪያ ሴት ፕሮፌሰር፣ የመጀመሪያ ሴት ጠቅላይ ሚኒስትር እና የመሳሰሉት የመጀመሪያ የሚባለው ስሞች እስኪቀየሩ ድረስ መስራት አለብን›› የምትለው ሳምራዊት፤ ሁላችንም ሴቶች በተሰማራንበት የሥራ መስክ ጎልተን በመውጣት ለሚቀጥለው ትውልድ ነገሮች ቀላል ማድረግ እንችላለን ትላለች። በመጨረሻም ሴት ሆይ በርቺ! ስትል በአጽንኦት በመስጠት መልዕክቷን አስተላልፋለች።

# ልዩ ዕትም ስፖርት

## ሴቶች በአዝጋሚው የኦሊምፒክ ጉዞ

ብርሃን ፈይሳ

ከጥንታዊ የአትሌቲክስ ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የቦስተን ማራቶን፤ ከዘመናዊው ኦሊምፒክ ምስረታ አንድ ዓመት በኋላ (እአአ 1897) ነበር መካሄድ የጀመረው። በዚህ ሩጫ ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ግን ከ75 ዓመታት ቆይታ በኋላ ነው። ይህ ሁኔታ ያልተዋጠላት አሜሪካዊቷ አትሌት ካትሪን ስዊዘር ግን እአአ በ1967 የፈጸመችው ገድል ዛሬ ላይ ላለው የሴት ስፖርተኞች ተሳትፎ በር የከፈተ ነው ሊባል ይችላል። በወቅቱ አትሌቷ ርቀቱን ለመሸፈን ፈቃድ ሳታገኝ በሩጫው ላይ በመሳተፏ አቋርጣ እንድትወጣ በአዘጋጆቹ መገፍተርና መዋከብ ደርሶባት ነበር።

ይሁንና ዓላማዋ ሴቶች እንደሚችሉ ማሳየትና ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ በደረሰባት ሁኔታ ሳትደናገጥ አስደናቂውን ታሪክ በወርቃማ ቀለም ለማጻፍ ችላለች። የበርካታ ሴት ስፖርተኞች ተምሳሌት የሆነችው የቀድሞዋ አትሌት ስዊዘር ‹‹ብቃትና ተሰጥኦ የትም አለ፤ አስፈላጊው ነገር እድል ማግኘት ነው›› የሚል አባባል አላት። በእርግጥም ባመነችበት ነገር ወደኋላ አትልምና ሌሎችም ይህንኑ መተግበር እንዳለባቸው መሰሎቿን ታስገነዝባለች። በእርግጥ ይህ ሁኔታ የአትሌቷ ገጠመኝ ብቻም አይደለም፤ ይልቁንም ሴት ስፖርተኞች ባለፈው ዘመን የተጓዙበት ጎዳና ነው።

የዓለም ስፖርት ታሪክ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች የዘገየ መሆኑን ያትታል። የስፖርታዊ ውድድሮች ሁሉ ቁንጮ የሆነው ኦሊምፒክም ጭምር የሴቶችን እኩል ተሳትፎ ለማረጋገጥ ለዓመታት አዝግሟል። ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ መካሄድ የጀመረው ይህ ጥንታዊ ውድድር፤ ከአካላዊ እንቅስቃሴና የፉክክር መድረክነቱ ባለፈ የሰው ልጆችን በእኩልና በሚዛናዊነት ማሳተፍ መቋጫ ሃሳቡ ነው። ይሁንና በሴቶች ተዋጽኦ እና በሚወዳደሩባቸው ስፖርቶች ልዩነቶችን ማጣጣም የቻለው በቅርቡ ነው።

ከሁለት ዓመት በፊት ጃፓን በታሪኳ ለሁለተኛ ጊዜ ያዘጋጀችው የቶኪዮ ኦሊምፒክ በታሪካዊነቱ ከኦሊምፒክ የክብር መዝገብ ላይ ሊሰፍር ችሏል። ይህ ከሆነበት ምክንያት አንዱ ደግሞ ከተወዳዳሪ አትሌቶች መካከል 49 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች በመሆናቸው የጾታ ምጣኔው ለመጀመሪያ ጊዜ ለእኩልነት የቀረበ በመሆኑ ነው። ይህም ማለት በኦሊምፒኩ ተካፋይ ከነበሩት 206ቱ ብሄራዊ የኦሊምፒክ ኮሚቴዎች፤ ሴት ስፖርተኞችን ያላካተተ አልነበረም። ተስፋ ሰጪ የሆነው ይህ ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው ግን እጅግ ረጅምና አስቸጋሪ ርቀትን ተጉዞ መሆኑ ግን ሊዘነጋ አይገባውም።

የታሪክ መዛግብት እንደሚያትቱት ከሆነ ጥንታዊው ኦሊምፒክ የሚከወነው ግሪካውያኑ አማልዕክቶቻቸውን ለመዘከር በመሆኑ ሴቶች መሳተፍ አይችሉም ነበር። ክልከላው ከተሳትፎ ባለፈ በክብረበዓሉ የሚከወኑ ውድድሮችን ሲመለከቱ ቢገኙ ከባድ ስቃይን አልፎም ሞትን ሊያስፈርድባቸው የሚችል ነው። የሴቶች ብቸኛው ተሳትፎ በፈረስ ስፖርት እንዲሁም የአማልክቶቻቸው አምላክ የሆነው ዜውስ ባለቤት በሆነችው ሄሪያ በተሰየመው የሴቶች ኦሊምፒክ የተገደበ ነበር። ለዘመናት በዚህ ሁኔታ አንዳቸው ለሌላኛቸው ባእድ ሆነው የዘለቁት ሴቶች እና የኦሊምፒክ ተሳታፊነት በዘመናዊው ኦሊምፒክም መንጸባረቁ አልቀረም። ምክንያቱ ደግሞ እአአ በ1896 የተጀመረው ዘመናዊው ኦሊምፒክ የተካሄደው በወንድ ስፖርተኞች መካከል በመሆኑ ነው።

በእርግጥ በመካከለኛው ዘመንም ከግሪክ ባለፈ ባሉ ሀገራት የሴቶች ስፖርታዊ ተሳትፎ ከአካላዊ ብቃት እና ከጉልበት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። በሮማውያን እንዲሁም በሌሎች አውሮፓውያን ዘንድም አልፎ አልፎ የሚታይ ቢሆንም ቀጣይነት ግን አልነበራቸውም። እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው ወቅትም ቢሆን የሴቶች ሚና በቤት ውስጥ ስራዎችና ቤተሰብን በመምራት ኃላፊነት ላይ የተገደበ በመሆኑ በስፖርቱ የነበራቸው እንቅስቃሴ እምብዛም ነበር። የነበሩትም ቢሆኑ በአካባቢ እንቅስቃሴ እና ፉክክር ላይ የተመሰረተ ከመሆን ይልቅ በተስተካከለ አቋምና



ከቀዳሚዎቹ ሴት የኦሊምፒክ አትሌቶች መካከል፤

ቁንጅና ጋር የተያያዘ እንደነበረም መዛግብቱ ያወሳሉ። ስፖርታዊ ውድድሮች በሚካሄዱባቸው ሜዳዎች ላይ ሴት ስፖርተኞች መታየት እንዲሁም በተለያዩ ስፖርታዊ ሁነቶች ውስጥ ተሳትፏቸውን እያረጋገጡ የመጡትም ከ19ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ ወዲህ ነው።

ዘመናዊው ኦሊምፒክ በወንዶች ብቻ የተጀመረ ቢሆንም ‹‹የዘመናዊው ኦሊምፒክ አባት›› በመባል የሚጠሩት ፈረንሳዊው ፒየር ደኩበርቲን ስህተቱን ወዲያው ነበር የተገነዘቡት። የወቅቱን ሁኔታም ‹‹አካታች ያልሆነ፣ የማይስብ፣ ውበት የጎደለውና ትክክል ያልሆነ›› ሲሉ ገልጸውታል። እኚህ ከዘመናቸው እጅግ የቀደሙት የስነትምህርት ጠቢብ ኋላ ላይ ‹‹ሁሉም ስፖርቶች ሊከወኑ የሚገባቸው እኩልነትን መሰረት አድርገው ነው›› በማለትም ተገቢ ያሉትን ሁኔታ በተግባር አንጸባርቀዋል።

ሴቶች በኦሊምፒክ መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩት በፈረንሳይ ፓሪስ በተካሄደው ቀጣዩ ኦሊምፒክ ሲሆን፤ የቴኒስ እና ጎልፍ ደግሞ በወቅቱ ውድድር ለማድረግ የተፈቀዱ ስፖርቶች ነበሩ። በኦሊምፒክ ታሪክ ውድድሯን በበላይነት በመፈጸም የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀችው እንስትም እንግሊዛዊቷ ቻርሎቴ ኩፐር እንደሆነችም ታሪክ ያወሳል። እአአ በ1912 ደግሞ በውሃ ዋና ስፖርት ሴቶች እንዲወዳደሩ ቢደረግም በወቅቱ ከጾታ ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ዘንድ የነበረውን ሁኔታ በግልጽ ሊያመላክት የሚችል አወዛጋቢ ሃሳብ ተነስቶ ነበር። ይኸውም ዋናተኞቹ ለውድድሩ ምቹ የሆኑ አልባሳትን ከመጠቀም ይልቅ ዘወትር እንደሚያደርጉት ቀሚስ ለብሰው ይወዳደሩ የሚለው ነበር።

ሌሎቹ ስፖርቶችም ቀስ በቀስ ወደ ኦሊምፒክ የተጠቃለሉ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በዚህ መድረክ በተለይ የምትታወቅበት ስፖርት አትሌቲክስ እንዲሁም ጂምናስቲክ እአአ ከ1928 አንስቶ የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖራቸው ተወስኗል። ይሁንና በጊዜው በተካሄደው የ800 ሜትር ሩጫ ውድድር በርካታ ተወዳዳሪዎች ራሳቸውን በመሳታቸው እአአ እስከ 1960 በዚህ ርቀት እንዳይሮጡ ታግዶ ነበር የቆየው። በቀጣይ ዓመታትም የተለያዩ ስፖርቶች በጥቂቱ ከመካተት ባለፈ እአአ በ1996 የሴቶች ብቻ የሆነ ውድድር ተጀምሮም ነበር በኦሊምፒክ። ነገር ግን ይህ ‹‹ሶፍትቦል›› የተባለና ከ‹‹ቤዝቦል›› ጋር ተመሳሳይነት ያለው ውድድር ብዙም ሳይቆይ ከመድረኩ ሊሰረዝ ችሏል።

በባህሪያቸው የተለዩት የፈረስ ግልቢያ እንዲሁም የጀልባ ቀዘፋ ስፖርቶች ደግሞ ለአሸናፊነት የሚደረገው ፍልሚያ በወንዶችና ሴቶች መካከል የሚከወን ነው። የቴኒስ እና ባድሚንተን ስፖርቶችም በቀደመው ዘመን በተመሳሳይ ሁለቱም ጾታዎች በድብልቅ ይወዳደሩባቸው ነበር።

ሴቶች በኦሊምፒክ ውድድር እንዲያደርጉበት የተደረገው የመጨረሻው ስፖርት ቦክስ ሲሆን፤ እአአ በ2012 ለንደን አዘጋጅታ በነበረችበት ወቅት ነው። ከዚህም በኋላ ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ አልያም ሴቶች ያልተካተቱበት የኦሊምፒክ ስፖርት የለም። በሌላ በኩል በኦሊምፒክ ይታይ የነበረው አሉታዊ ጉዳይ ሀገራት ሁለቱንም ጾታዎች ያማከለ ተሳትፎ ያለማድረጋቸው ነበር። ለአብነት ያህል እአአ የለንደን ኦሊምፒክ እስከተካሄደበት ጊዜ ድረስ ሶስት ሀገራት (ኳታር፣ ብሩኔ እና ሳውዲ አረቢያ) በታሪካቸው ሴት ስፖርተኞችን በኦሊምፒክ መድረክ አሳትፈው አያውቁም ነበር። ነገር ግን ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ባደረገው ጥረት ሀገራቱ ሁለቱንም ጾታ ያማከለ ተሳትፎ ማድረግ ጀምረዋል። ይኸውም የለንደኑን ኦሊምፒክ በመድረኩ የሴት ስፖርተኞች ተሳትፎን አንድ እርምጃ ያራመደ በሚል እንዲመዘገብ አድርጓል።

ከተሳትፎ ባለፈ ሴት ስፖርተኞች ብቃታቸውን በማስመስከር ሀገራቸውን ማስጠራትና ለመሰሎቻቸውም ተነሳሽነትን በመፍጠር ስኬታማ ሆነዋል። እአአ በ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ ከተዘጋጁ ሜዳሊያዎች መካከል 44 ከመቶ የሚሆነው በሴት አትሌቶች የተወሰደ ሲሆን፤ ይኸውም በታሪክ ከፍተኛው ነው። በግለሰብ ደረጃ አራት ሜዳሊያዎችን በአንድ ኦሊምፒክ በመውሰድ ባለ ክብረወሰን የሆነው ወንድ አትሌት ታሪኩን ካጻፈ 12 ዓመታት በኋላ ጀርመናዊቷ ፋኒ ብላንከርስ-ኮን ስኬቱን መጋራት ችላለች። ሩሲያዊቷ ማሪያ ጎርኮቪስኪያ ደግሞ በአንድ ኦሊምፒክ 2 የወርቅ እና 5 የብር በጥቅሉ 7 ሜዳሊያዎችን ለብቻዋ በመሰብሰብ ተጠቃሽ ናት። በዚህ ወቅት መሰል ስኬትን የግላቸው ያደረጉ በርካታ እንስት ስፖርተኞች ስለመኖራቸው ልብ ይሏል። ሊታሰቡ የማይችሉ አስደናቂ ተሳትፎ ካደረጉት መካከል እንግሊዛዊቷ የፈረስ ግልቢያ ተወዳዳሪ ሎርና ጆንስቶን ቀዳሚዋ ስትሆን የ 1972ቱ ኦሊምፒክ ላይ ስትሳተፍ እድሜዋ 70 ዓመት ከ5 ቀን ነበር።

ሴት ‹‹አትችልም›› በሚል የምትገለጽበት ጉዳይ በተለይ ከጉልበት ጋር የተያያዘ መሆኑ እሙን ነው። ይሁንና አቅምንና ብልሃትን በሚጠይቀው ስፖርት በሁለቱም ጾታ ተመሳሳይ ደረጃ በሁለቱም ጾታዎች በመከወን እኩል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ዘርፍ ነው። ይህም በርካታ ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ በመሪነት፣ በብቃት ኃላፊነትን በመውሰድ፣ … እያሳየ ይገኛል። ለርካታ ሀገራትም የኦሊምፒክን ሜዳሊያ ባጠለቁ ሴቶች ተጨማሪ ክብር ሊያገኙ ችለዋል። በዚህ ረገድ ማሳያ ከሆኑት ሀገራት መካከልም ኢትዮጵያ ተጠቃሽ ናት። እንደ ሌላው ዓለም ሁሉ የሴቶች ተሳትፎ የዘገየ ቢሆንም ባስቆጠሯቸው ሜዳሊያዎች ግን ከወንዶቹ የላቁ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

ይህንን ሁኔታ የተረዳውና ሴቶችን ማበረታታት የዘወትር ተግባሩ የሆነው ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴም የሴቶች ስፖርት ላይ እንደ ዩኔስኮ እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ኦሊምፒክ ኮሚቴ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ለጉዳዩ በሰጠው አትኩሮት በማማከር ከሚሰሩ ኮሚሽኖች መካከል የጾታ እኩልነትን በሚመለከት የተቋቋመ ኮሚቴ አለው። በየአራት ዓመቱም አዳዲስ የኮሚቴ አባላትን በመምረጥም ቀጣጥነት ያለውን ስራ ይሰራል።